ቴዎድሮስ

ታሪካዊ ድራማ



Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ቴዎድሮስ

ታሪካዊ ድራማ

ተጻፈ

ከደጃዝማች ፡

ግርማቸው ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ።

አዲስ አበባ ።

Scanned with CamScanner

ለማሳተም ፡ ወይም ፡ ለመተርጐም ፡
አለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ በሕግ ፡ ተከልክሏል ።

Tous droits réservés

Copyright

አራተኛ ፡ ኤዲሲዮን ፡ ፲፱፻፷ ዓ. ም.

ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

መቅድም ።

ስለ ፡ ምግባር ፡ መደርጀትና ፡ መታረም ፡ በተለየ ፡ የቴያትር ድርሰት ፡ ጥቅም ፡ መስጠቱን ፡ በማወቅ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባገራችን ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ እንዲለመድና ፡ እንዲስፋፋ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምረው ፡ ለደራሴዎች ፡ የሚያደርጉትን ፡ ድጋፍ ፡ መዠመሪያ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ።

ይህ ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ታሪክ ፡ የሚያሳይ ፡ ቴያትር ፡ ስለ ፡ አገር ፡ ፍቅርና ፡ ስለ ፡ ወገን ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ አንድነት ፡ ጥቅም ፡ ለኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ የሆነውን ፡ ስሜት ፡ እንዲያስገኝ ፡ ዋና ፡ ምኞቱ ፡ ነው ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሀሳባቸው ፡ ከዘመናቸው ፡ የቀደመ ፡ በመሆኑ ፡ ብዙ ፡ ተቀባይና ፡ ረዳት ፡ ባለማግኘት ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ እንቅፋቶች ፡ ተፈጥረውባቸው ፡ በብርታትና ፡ በኀይል ፡ ሲታገሉ ፡ ዘመን ፡ ንግሣቸው ፡ በምሬት ፡ ተፈጸመ ።

እንዲሁ ፡ እንደርሳቸው ፡ ላገር ፡ ጥቅምና ፡ ለሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ የሚበጁ ፡ አዲሶች ፡ አሳቦች ፡ የወጠኑና ፡ የማሻሻል ፡ ሥራ ፡ የሞከሩ ፡ መሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ እንቅፋቶች ፡ ገጥመዋቸው ፡ ብርቱ ፡ ትግል ፡ እንዳስፈለጋቸው ፡ ሰፊ ፡ በሆነው ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አስረጂዎች ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሳባቸውን ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ለመፈጸም ፡ የቻሉት ፡ መሪዎች ፡ ኀይልን ፡ ከዘዴ ፡ ጋራ ፡ ብርታትን ፡ ከትዕግሥት ፡ ጋር ፡ አድርገው ፡ እምነትንና ፡ ተስፋን ፡ ፍቅርንም ፡ ጨምረው ፡ የሠሩት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

በብዙ ፡ ድካምና ፡ በብዙ ፡ መከራ ፡ የተገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ እንዲሁም ፡ በስንት ፡ ተጋድሎና ፡ ፈተና ፡ ጸንቶ ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነትና ፡ ክብር

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ሁል ፡ ጊዜም ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቶቿ ፡ ከፍተኛ ፡ ምግባርና ፡ ባርበኞቿ ፡ ልባዊነት ፡ በሕዝቡም ፡ ብርታትና ፡ ታማኝ ነት ፡ ተጠብቆ ፡ እንደሚኖር ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ያለፈው ፡ ያሯት ፡ ዓመታት ፡ ፈተና ፡ በቀድሞ ፡ ታሪክ ፡ ከሚገኙት ፡ አያሌ ፡ ማስረጃዎች ፡ ጋራ ፡ ተጨምሮ ፡ ለዘለዓለም ፡ ምስ ክር ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

በወገኖቼ ፡ ሙያና ፡ ባባቶቼ ፡ ምግባር ፡ በሚገባ ፡ ለመ መካት ፡ የሚችል ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ የኋላውን ፡ እያስተዋለ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በማሰብ በደጉም ፡ ሆነ ፡ በክፉም ፡ ዕድሉ ፡ ቢሆን ፡ እርምጃውን ፡ በተስፋና ፡ በእምነት ፡ ይቀጥላል ። ቁም ፡ ነገርንና ፡ ትውል ድን ፡ አብልጦ ፡ በማሰብ ፡ መሠረት ፡ ይዞ ፡ ስለሚጓዝ ፡ መጭውን ፡ ጊዜ ፡ በተስፋና ፡ በእምነት ፡ ለማስተዋል ፡ ከመ ቻሉ ፡ በላይ ፡ ከተመልካቾቹም ፡ ፍቅርና ፡ ከበሬታን ፡ እንደ ሚያገኝ ፡ አይጠረጠርም ።

ግ ፡ ተ ፡ ሐ ።

የታሪኩ ፡ መግቢያ ።

ከብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ነፃነቱንና ፡ ክብሩን ፡ ጠብቆ ፡ ባፍሪካና ፡በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ መንግሥት ታት ፡ መካከል ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስም ፡ የነበረው ፡የኢት ዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ባ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ አንድነቱን ፡ አጥቶ ፡ ነበር ፡፡ በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለስሙ ፡ ዘውዱን ፡ ጭኖ ፡ ተቀምጦ ፡ ሥልጣኑ ፡ ግን ፡ በመሳፍንቶች ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ አንድ ፡ አካልና ፡ ኀያል ፡ የነበረው ፡ የቀድሞ ፡ የኢ

Scanned with CamScanner

ትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ የመከፋፈልና ፡ የመለያየት ፡ የመድከምም ፡ መልክ ፡ ይዞ ፡ በመታየቱ ፡ ያገሪቱ ፡ ነፃነት ፡ በታላቅ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ነበር ።

በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከዙሪያው ፡ የሚጠባበቁት ፡ ያገሪችን ፡ ጠላቶች ፡ ይልቁንም ፡ በሰሜንና ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል የወረራ ፡ ሥራ ፡ በመሞከራቸው ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ወሰን ፡ እያለፉ ፡ አገር ፡ መያዝ ፡ ገዞምረው ፡ ነበር ።

መሳፍንቶቹም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አገሩን ፡ በሙሉ ፡ ፀጥ ፡ አድርገው ፡ ለመግዛት ፡ ባይችሉ ፡ የውጭን ፡ ጠላት ፡ ለመከልከል ፡ በተቻላቸው ፡ አልቦዘኑም ፡ ነበር ። ስለ ፡ ሆነም ፡ በዚህ ፡ ባደገኛ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ የሚመራውና ፡ ጠላትንም ፡ የሚያሳፍር ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ይታወቅ ፡ ነበርና ፡ እነሆ ፡ ካሳ ፡ የተባለ ፡ የቋራ ፡ ተወላጅ ፡ ሰው ፡ በውልደት ፡ ቀጥታ ፡ በተለየ ፡ ላልጋው ፡ ወራሽነት ፡ የታጨ ፡ ሳይሆን ፡ በተማላ ፡ ስጦታውና ፡ በጀብዱው ፡ ስሙን ፡ አስነሥቶ ፡ ድል ፡ በድል ፡ እየተራመደ ፡ ዘውዱን ፡ ጨብጦ ፡ በዳግማዊ ቴዎድሮስ ፡ ስም ፡ ነገሠ ። ላልቶ ፡ የነበረውን ፡ አንድነት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አድሶ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ፀንቶ ፡ ያለውን ፡ ያንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ አቋቋመ ።

የቴያትሩ ፡ ክፍሎች ፡ አጭር ፡ ማስረጃዎች ።

ደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ ሽፍትነትን ፡ ትተው ፡ የእቴጌ ፡ መነንን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ አግብተው ፡ በሰላማዊነት ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገብተው ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ድኅነታቸውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የቀድሞውን ፡ ጠብና ፡ ቂም ፡ ባለመርሣት ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ በየጊዜው ፡ ክብራቸውን ፡ በማ ኰሰስ ፡ ስላስቀጪቸው ፡ ምሬት ፡ ገብቷቸው ፡ ሚስታቸ ውን ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሸፈቱ ፡ ይባላል ።

፩ኛ ፡ ክፍል ። በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ።

የደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ መሸፈት ፡ እንደ ፡ ተሰማ ፡ የንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ ስም ፡ የነበረውን ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ አግብተው ፡ እቴጌ ፡ የነበሩት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ (የራስ ፡ ዐሊ ፡ እናት) ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ጨምረው ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይማ ከራሉ ፡ ካሳን ፡ እንዲይዝ ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ ይታ ዘዛል ። እርሱም ፡ ትእዛዙን ፡ በመመካት ፡ ይቀበላል ።

፪ኛ ፡ ክፍል ። በደጃዝማች ፡ ካሳ ፡ ሰፈር ።

(ሀ) ደጃች ፡ ካሳ ፡ ሸፍተው ፡ በሠፈራቸው ፡ ከባለቤታ ቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ተዋበችና ፡ ከታማኝ ፡ አሽከሮቻ ቸው ፡ ከገብርዬ ፡ ከገልሞ ፡ ከዓለሚ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ይመካከራሉ ።

(ለ) የደጃች ፡ ወንድይራድን ፡ መምጣት ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ አርበኞቻቸውን ፡ በጋለ ፡ ቋንቋ ፡ ካበረታቱ ፡ በኋላ ፡

ለመግጠም ፡ ቈርጠው ፡ ይነሣሉ ።

(ሐ) ከሚስታቸው ፡ ሲሰነባበቱ ፡ ሴቷ ፡ በዚህ ፡ ባባትና ፡ በባል ፡ አጋጣሚ ፡ ጠብ ፡ ኀዘናቸውን ፡ እየገለጡ ፡ ሁለቱም ፡ ይወያያሉ ።

(መ) ወንድይራድ ፡ ይማረካል ።

(ሠ) በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወሬው ፡ እንደ ፡ ተሰማ እቴጌይቱ ፡ ይዘምታሉ ፡ እርሳቸውም ፡ ይማረካሉ ።

(ረ) ደጃች ፡ ካሳ ፡ ድል ፡ በድል ፡ እየገሠገሡ ፡ በደምቢያ ፡ በጐርጐራ ፡ በደረስጌ ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ሁሉንም ፡ በተራ ፡ ድል ፡ መትተው፡ ዳግማዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተብለው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘውድ ፡ ይጭናሉ ።

(ሰ) የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዐዋጅ ፡ ይነገራል ።

፫ኛ ፡ ክፍል ። በሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ።

(ሀ) ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ታመዋል ፡ ያዔ ፡ ቴዎድሮ ስን ፡ መምጣት ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ ከሸዋ ፡ ባላባቶችና ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይመካከራሉ ። ለመመከት ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ ያደርጋሉ ።

(ለ) ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ማርከው ፡ ይዘዋ ቸው ፡ ይሄዳሉ ።

፬ኛ ፡ ክፍል ። ዘመነ ፡ ንግሥ ።

(ሀ) ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመላ ፡ አስገብረው ፡ የጥንቱን ፡ አንድ ፡ የን ፡ ነ ፡ መንግሥት ፡ ካቋቋሙ ፡ በኋላ ፡ ስላስተዳደር ፡ ያቀዱትን ፡ አሳባቸውን ፡ ይደረ ድራሉ ።

(ለ) ይህን ፡ አሳባቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ዠመሩ ፡ አውራጆቹ ፡ ሁሉ ፡ የመሸፈታቸው ፡ ወሬ ፡ እየተከታተለ ፡ ይመጣላቸዋል ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ብስ ጭት ፡ ገብቷቸው ፡ የጭካኔ ፡ መንፈስ ፡ ያድርባቸዋል ።

(ሐ) የጋረድና ፡ የቢል ፡ ሞት ፡ ይታያል ።

(መ) አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ሥቃይና ፡ ስለ ፡ ጭካኔያቸው ፡ በድፍረት ፡ አነጋገር ፡ ይወቅሳቸ ዋል ፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ምክሩን ፡ ሳይቀበሉ ፡ የባሰ ውን ፡ ይጨክናሉ ።

(ሠ) ከእንግሊዝ ፡ ቆንሲል ፡ ከካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ ጋራ ፡ ይጣላሉ ፡ ፈረንጆቹንም ፡ ሁሉ ፡ ያስሯቸዋል ።

፩ኛና ፡ ፪ኛ ፡ ክፍል ። መቅደላ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ።

(ሀ) በመቅደላ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከታማኝ ፡ አሽከሮቻ ቸው ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ዐቅድ ፡ እየተመካከሩ ፡ ምሬታቸውንም ፡ ይገልጻሉ ።

(ለ) ፊታውራሪ ፡ ገብርዬ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ሚስታቸው ፡ እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ እርቅ ፡ እንዲጠይቁ ፡ ይመክሯ ቸዋል ።

(ሐ) ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አልማረክም ፡ ብለው ፡ ሕይወታቸ ውን ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ያጠፋሉ ።

(መ) እንግሊዞችም ፡ ለሬሳው ፡ ሰላምታ ፡ ይሰጣሉ ። እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ያለቅሳሉ ። ጄኔራል ፡ ናፒየ ፡ አጭር ፡ ንግግር ፡ ያደርግና ፡ ቴያትሩ ፡ በዚሁ ፡ ይፈጸማል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ማስገንዘቢያ ።

ይህ ፡ የቴያትር ፡ ጽሑፍ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መሠረቱ ፡ ታሪክ ፡ ቢሆን ፡ ለቴያትር ፡ እንዲስማማ ፡ ዋናዎቹን ፡ ምዕራፎች ፡ ይመለከታል ፡ እንጂ ፡ ታሪኩን ፡ በሙሉ ፡ የሚናገርና ፡ በትክክል ፡ የሚከተል ፡ አይደለም ። የቴያትር ፡ ድርሰትና ፡ የታሪክ ፡ ድርሰት ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ ታሪክ ፡ በተለየ ፡ የሚያስገድደውን ፡ ጥልቅ ፡ ምርመራና ፡ እርግጠኛነትን ፡ ቴያትር ፡ እንደማይጠይቅ ፡ አንባቢ ፡ አይስተውም ።

አጻጻፉንም ፡ በግጥም ፡ ስልት ፡ ያደረግሁት ፡ ለቴያትሩ ፡ መልክ ፡ ለመስጠት ፡ ስሜትና ፡ ቅልጥፍና ፡ ያለው ፡ አነጋገር ፡ በመፈለግ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የግጥሙ ፡ አካሄድና ፡ ዜማው ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያልተተካከለ ፡ ሆኖ ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

የተጫዋቾች ፡ ዝርዝር

፩ ፡ እቴጌ ፡ መነን (የራስ ፡ ዐሊ ፡ እናት) ፡
፪ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡
፫ ፡ መኳንንት ፡
፬ ፡ መነኩሴ ፡
፭ ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡
፮ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ (በኋላም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ) ፡
፯ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብርዬ ፡
፰ ፡ ባላምባራስ ፡ ገልሞ ፡
፱ ፡ ደጃዝማች ፡ ዓለሜ ፡
፲ ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ (በኋላም ፡ እቴጌ) ፡
፲፩ ፡ » ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ (እቴጌ)
፲፪ ፡ ባሕታዊ ፡
፲፫ ፡ ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡
፲፬ ፡ አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡
፲፭ ፡ አቶ ፡ ዳርጌ
፲፮ ፡ » ሰይፉ ፡
፲፯ ፡ » ሀብቱ ፡
፲፰ ፡ » እንዳርጋቸው ፡
፲፱ ፡ » ሀብተ ፡ ማርያም ፡ (የመራው) ፡
፳ ፡ አቶ ፡ ገርማሜ ፡
፳፩ ፡ » በዛብህ ፡
፳፪ ፡ » ናደው ፡
፳፫ ፡ » አገብጊ ፡
፳፬ ፡ » ሸዋ ፡ ዘረፋ ፡
፳፭ ፡ » ጄኔራል ፡ ናፒየር ፡
፳፮ ፡ » ካፕቴን ፡ ካሜሮን ፡
፳፯ ፡ » የልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡
፳፰ ፡ » ገረድ ፡
፳፱ ፡ » ወታደሮች ፡
፴ ፡ መልእክተኞች ፡
፴፩ ፡ እስረኞች ፡
፴፪ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡
፴፫ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮች ፡
፴፬ ፡ ልጅ ፡ ገረድ ፡
፴፭ ፡ ሚስተር ፡ ዜል ፡
፴፮ ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡
፴፯ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ (የሰሜን ፡ ገዥና ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ) ፡
፴፰ ፡ ልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ ቴዎድሮስ ፡

ልብሱና ፡ መጋረጃው ፡ የዚያው ፡ ዘመን ፡ ነው ፡፡

Scanned with CamScanner

ቴዎድሮስ ።

ታሪካዊ ድራማ

ክፍል ፡ አንደኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእቴጌ ፡ መነን ፡ እልፍኝ እቴጌ ፡ መነን ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ አንድ ፡ መነኮሴ ፡ መኳንንቶች ፡ አንድ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከር ።

እቴጌ ፡ መነን ፡ (የራስ ፡ ዐሊ ፡ እናት) ።

ኧረ ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ አሳቡ ፡
ሽፍቶ ፡ የሄደው ፡ ከንቤተ ፡ ሰቡ ።

ራስ ፡ ዐሊ ።

ሰውዬው ፡ ኵሩ ፡ ነው ፡ የተነፋ ፡ ልቡ ፡
ይዞ ፡ ማዋረድ ፡ ነው ፡ ይበርዳል ፡ ጥጋቡ ።

ከመኳንንቱ ፡ አንዱ ።

አንዴ ፡ ከተያዘ ፡ ከገባ ፡ በጃችን ፡
እንጨክንም ፡ ከቶ ፡ በገዛ ፡ አማቻችን ።
እርሱም ፡ በበኵሉ ፡ በኛ ፡ ያዝን ፡ ይሆናል ፡
እርቅ ፡ ሰላም ፡ እርጎ ፡ መተው ፡ ይገባናል ።

መነኵሴው ።

ሰውዬው ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ ስሙ ፡ የተጠራ ፡
ጕበዝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ኀይልን ፡ የማይፈራ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አንደኛ ።

በዘዴ ፡ በትስማሥት ፡ ማባበል ፡ ይሻላል ።
በኀይል ፡ ብንለው ፡ በጣም ፡ ያውክናል ።

እቴጌ ፡ መነን ።

እንዲህ ፡ ስትሉ ፡ ነው ፡ ስሙ ፡ የገነነው ፡
የፈራነው ፡ መስሎት ፡ አገር ፡ የሚያብጠው ።
ዘዴ ፡ መላ ፡ አታብዙ ፡ ጦር ፡ ይታዘዝና ፡
በኀይል ፡ ተገድዶ ፡ ይምጣ ፡ ይያዝና ፡
እምቢም ፡ካለ ፡ ይሙት ፡ በገዛ ፡ ጥፋቱ ፡
ላንድ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ አይሥጋ ፡ መንግሥቱ ።

ራስ ፡ ዐሊ ።

እናቴ ፡ ለሚሉት ፡ እኔም ፡ ነኝ ፡ ደጋፊ ፡
መጣጣት ፡ አያሻም ፡ ለዚህ ፡ ለተጋፊ ።
ይገባዋል ፡ ለርሱ ፡ ጭካኔ ፡ እንዳመሉ ፡
መቀጣጫ ፡ እንዲሆን ፡ ላመፀኛ ፡ ሁሉ ።

ከመኳንንት ፡ አንዱ ።

እኔም ፡ ዐውቀዋለሁ ፡ ጅግና ፡ እኮ ፡ ነው ፡ ካሣ ፡
ኩሩ ፡ እንዳይመስላችሁ ፡ ሳይቈርጥ ፡ የተነሣ ።
አሳቡ ፡ ረዥም ፡ ነው ፡ አይደለም ፡ የዋዛ ፡
ዐመፀኛ ፡ አይደለም ፡ ከቶውም ፡ ወንበዴ ፡
ከኀይል ፡ የተሻለ ፡ ሌላ ፡ እንፈልግ ፡ ዘዴ ።
ቱርክን ፡ ያኽል ፡ ጠላት ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋ ፡
ሊዋጋን ፡ ተነሥቶ ፡ ሳለብን ፡ አደጋ ፡ (*)
እንዴት ፡ እርስ ፡ በራስ ፡ እኛው ፡ እንዋጋ ።

* በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በቱርክ ፡ መሪነት ፡ ግብጽና ፡ ደርቡሽ ፡ በሰሜንና ፡ በምሥራቅ ፡ (ሐረር) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የወረራ ፡ ሥራ ፡ ይዘው ፡ ነበርና ፡ የጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ካሣን ፡ ማስደሰት ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ማባበል ፡
የመጣውን ፡ ጠላት ፡ እንዲከላከል ።

እቴጌ ።

ይህን ፡ ዐይነት ፡ አሳብ ፡ እኔ ፡ እቃወማለሁ ፡
ፈርታችሁት ፡ እንደሁ ፡ እኔው ፡ እዘምታለሁ ።
ደግሞ ፡ ላንድ ፡ ሽፍታ ፡ ይኸን ፡ ያኽል ፡ ጣጣ ፡
እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ጠላትም ፡ ቢመጣ ፡
አንለማመጥም ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ።
ፈርተውኛል ፡ ብሎ ፡ ልቡ ፡ ሳይበረታ ፡
ጦር ፡ ይታዘዝና ፡ በቶሎ ፡ ይመታ ።

ራስ ፡ ዐሊ ።

እናቴ ፡ የሚሉት ፡ ቢሆንም ፡ ትክክል ፡
ጉዳት ፡ ሳያገኘን ፡ ለመጉዳት ፡ እንድንችል ።
አይከፋም ፡ መመካከር ፡ ማማረጥም ፡ ዘዴ ፡
ጠላት ፡ አይናቅም ፡ ቢሆንም ፡ ወንበዴ ።

መነኩሴው ።

በየአድባራቱ ፡ በየባላገሩ ፡
የሚወራው ፡ ወሬ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ነገሩ ።
ካሳ ፡ የተባለው ፡ ሽፍታና ፡ አሸባሪ ፡
ኀያል ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ ላልጋውም ፡ አስፈሪ ።
እርሱ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ዘውዱን ፡ የሚወርስ ፡
ቴዎድሮስ ፡ ተብሎ ፡ በኀይሉ ፡ የሚነግሥ ፡
ይህን ፡ እየሰማ ፡ አድሮበት ፡ ትዕቢት ፡
ልቡ ፡ በጣም ፡ ኮርቷል ፡ በሀሰት ፡ ትንቢት ።

Scanned with CamScanner

ክፍል ፤ አንደኛ ።

እቴጌ ።

ይህ ፡ የቀን ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ መጨበጥ ፡ ይመና ፡
በጣም ፡ ተጭኖታል ፡ ክፉ ፡ ድንቁርና ።
በጣሙን ፡ ይገርማል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትዕቢት ፡
ወገኛ ፡ ነው ፡ ለካ ፡ ያውም ፡ ባለትንቢት ።
ከዳዊት ፡ ሰሎሞን ፡ ትባት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡
ወይም ፡ ከመሳፍንት ፡ ዘር ፡ ውልደት ፡ የሌለው ፡
አይቻለውም ፡ መንገሥ ፡ ምን ፡ ሞያ ፡ ቢኖረው ።
የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ እርሱ ፡ መቼ ፡ አጠና ፡
በጣም ፡ ያልበሰለ ፡ ጥሬ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ገና ።
ሀሰት ፡ እያወራሁ ፡ እኔ ፡ ልብላ ፡ ባይ ፡
የሚያወራለትን ፡ እንዳንድ ፡ እታላይ ፡
እየሰማ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ የያዘው ፡ ትዕቢት ፡
እኛን ፡ አስለቅቆ ፡ ሊሆን ፡ ባለቤት ።
በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ድፍረት ፡
ወሬው ፡ መወራቱ ፡ ለእኛኮ ፡ ነው ፡ እፍረት ።
ቅባት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ለመንገሥ ፡ ማሰቡ ፡
እንዴት ፡ ቢንቀን ፡ ነው ፡ ሰነፍ ፡ ቢሆን ፡ ሕዝቡ ።
ይሁን ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ እርሱም ፡ ይንጠራራ ፡
ልቡን ፡ ያሳብጠው ፡ ያድርገው ፡ ተራራ ፡
እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ባገሩ ፡ ሲያስወራ ፡
ይመስለው ፡ ይሆናል ፡ እኛም ፡ የምንፈራ ።
በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ልቡ ፡ ቢደነድን ፡
ተዋርዶ ፡ ከመቅረት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይድን ።
በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ትዕቢት ፡ ልቡን ፡ የሞላው ፡
ተይዞ ፡ ይሰቀል ፡ በመጨረሻው ።
ይታዘዝ ፡ በቶሎ ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡
ከነሠራዊቱ ፡ ገሥግሦ ፡ ይሂድ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

ደጃች ፡ ወንድይራድን ፡ አሁን ፡ ቶሎ ፡ አስጠራው ፡
ትእዛዙን ፡ አጥብቀን ፡ እኛው ፡ እንንገረው ።

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

እቴጌ ፡ መንን ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ መኳንንት ፡ መነሳሴው ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡
የልፍኝ ፡ አሽከር ።

እቴጌ ፡ ለደጃች ፡ ወንድይራድ ።

ወንድይራድ ፡ ወታደርህን ፡ ይዘህ ፡ ነገ ፡ እንድትነሣ ፡
ቢቻል ፡ ከነነፍሱ ፡ ተይዞ ፡ ይምጣ ፡ ካሣ ።
እምቢም ፡ካለ ፡ ይሙት ፡ እንደሚገባው ፡
እዚያው ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሬሳው ፡
ከያለበት ፡ መጥቶ ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲያየው ።
ዐመፅ ፡ ላለበት ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ መድኀኒቱ ፡
ይሁን ፡ መቀጣጫ ፡ ይታወቅ ፡ ጥፋቱ ።

ደጃች ፡ ወንድይራድ ፡ (በመመካት) ።

የመቤቴን ፡ ትእዛዝ ፡ እፈጽመዋለሁ ፡
ለዚህ ፡ ለወንበዴ ፡ እኔ ፡ አሳየዋለሁ ።
እኔ ፡ አመጣዋለሁ ፡ ማርኬ ፡ በኀይል ፡
አሻፈረኝ ፡ ካለም ፡ እዚያው ፡ ይሞታል ።
እንኳን ፡ አንድ ፡ ሽፍታ ፡ ቀማኛ ፡ ወንበዴ ፡
ብዙ ፡ እመልሳለሁ ፡ በጦር ፡ በጐራዴ ።
እኔ ፡ ነኝ ፡ ወንድይራድ ፡ ታማኝ ፡ አሽከርሽ ፡
ያን ፡ የኮሶ ፡ ሻጭ ፡ ልጅ ፡ የምቀጣልሽ ።

ራስ ፡ ዐሊ ።

ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ በጣሙ ፡ ተጠንቀቅ ፡
ካሣ ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በዋዛ ፡ የማይለቅ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አንደኛ ።

እንዳይመስልህ ፡ ላንተ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሽፍታ ፤
ጦር ፡ መጣብህ ፡ ሲሉት ፡ በወሬ ፡ እሚፈታ ።
በጣም ፡ ያስፈልጋል ፡ አስልቶ ፡ መሄድ ፤
ቀድሞ ፡ ማደራጀት ፡ የድሉን ፡ መንገድ ።

(ወንድይራድ ፡ በመመካት ፡ እነጋገር) ።

አይስሙ ፡ ጌታዬ ፡ ሰው ፡ የሚለውን ፤
አያስፈራም ፡ ካሣ ፡ ይንዛ ፡ ጉራውን ።
ገና ፡ መጣ ፡ ሲሉት ፡ አገር ፡ ጥሎ ፡ ይሸሻል ፤
ወይም ፡ ካንዱ ፡ ደብር ፡ ገብቶ ፡ ይደውላል ።
ምንም ፡ ጀግና ፡ ቢመስል ፡ ቢሆን ፡ ቀበጥባጣ ፤
ደፍሮ ፡ እኛን ፡ ለመውጋት ፡ ምን ፡ ቢሆን ፡ አይቃጣ ።
ልክ ፡ ሳላገባ ፡ አልተወውም ፡ እኔ ፤
ዓለም ፡ በቃኝ ፡ ብሎ ፡ እስኪሄድ ፡ ምናኔ ።
በተሻለኝ ፡ ነበር ፡ አርፌ ፡ ብቀመጥ ፤
እያለ ፡ እንዲቆጨው ፡ ዳግመኛም ፡ እንዳይቀብጥ ።

እቴጌ ፡ (ሳቅ ፡ እያሉ) ።

እንዳነጋገርህ ፡ ሥራህ ፡ እንዲቃና ፤
አንጠራጠርም ፡ ታማኝነህና ።
ይህንን ፡ ዐውቀን ፡ ነው ፡ እኛም ፡ የመረጥንህ ፤
በጦር ፡ ሞያህና ፡ በታማኝነትህ ።

(ለልፍኝ ፡ አሽከር) ።

አሳየው ፡ እንግዲህ ፡ ጥጋብ ፡ እንደማይበጅ ፤
ለደጃች ፡ ወንድይራድ ፡ አጠጣው ፡ ደጎና ፡ ጠጅ ።

(ወንድይራድ ፡ እጅ ፡ ይነሣል) ።

መጋረጃ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ ደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ገብርዬ ፡ ዓለሚ ፡ ገልሞ ፡ ደበጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ሰፈር ፡ ይመካከራሉ ።

ደጃች ፡ ካሣ ።

እግዜር ፡ ያለው ፡ ላይቀር ፡ አንዴ ፡ የወሰነው ፡
መሥጋትም ፡ መጨነቅ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለው ።
ፍርሃት ፡ ምንድርነች ፡ ራሱን ፡ ላመነ ፡
ሞት ፡ እንዲሁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡
ላዳም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ የማይቀር ፡ ዕዳ ፡
አይገባም ፡ ከቶ ፡ ሊመስለን ፡ እንግዳ ።

ወይዘሮ ፡ ተዋበች ።

እንኳንስ ፡ ለወንዱ ፡ ቢሆንም ፡ ለሴቲ ፡
ታዞለት ፡ የለምን ፡ የማይቀረው ፡ ሞቲ ።
ታላቅ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፡ ለሰውም ፡ ዕፍረት ፡
ሞትን ፡ እየፈሩ ፡ መኖር ፡ በውርደት ።

ገልሞ ።

እመቤቴ ፡ ያሉት ፡ ይገባኛል ፡ እኔ ፡
አልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይ ፡ የለበት ፡ ነፍነኔ ።
ዘላለም ፡ በግ ፡ መስሎ ፡ ከሚገኘው ፡ ኑሮ ፡
እንዳንበሳ ፡ ሁኖ ፡ መሞት ፡ ነው ፡ ተከብሮ ።
ደግሞም ፡ በውነቱ ፡ ዕድሉን ፡ ላወቀው ፡
እንኳንስ ፡ ጦርነት ፡ ቢሆን ፡ ያፈቀደው ፡
ምኞቱን ፡ መለወጥ ፡ አይገባውም ፡ ሰው ፡
እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ልቢም ፡ እንደሚያምነው ፡
ቁራጥነት ፡ ያለው ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ እሱ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ይልቅም ፡ እንደኛ ፡ ቈርጦ ፡ የተነሣ ፡
ከብሩ ፡ እንዳይጐድልበት ፡ በጣም ፡ የሚሣሣ ፡
አይጠረጠርም ፡ ድል ፡ እንደሚነሳ ።

ደጃች ፡ ካሣ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካለው ፡ ከመልካሙ ፡ ነገር ፡
ከሁሉ ፡ ይበልጣል ፡ መኖር ፡ በመከበር ፡
ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ሁኖ ፡ ከሞት ፡ ጋራ ፡ሲቀበር ፤
መልካም ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለትውልድ ፡ የሚቀር ።
ገልሞም ፡ እንደሚለው ፡ ለክብሬ ፡ እቆጫለሁ ፡
ስሜን ፡ ለማስነሣት ፡ አንዴ ፡ ቈርጫለሁ ።
ኢትዮጵያን ፡ ለመግዛት ፡ እኔም ፡ እመኛለሁ ፤
እግዜርም ፡ ከኔው ፡ ጋራ ፡ መሆኑን ፡ አምናለሁ ።
እየደጋገመ ፡ ሕልም ፡ አሣይቶኛል ፡
ቴዎድሮስ ፡ የምትባል ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ብሎኛል ።
ለኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ ተጋደል ፡ ተዋጋ ፤
ሐሳብህ ፡ ሲፈጸም ፡ እንድታገኝ ፡ ዋጋ ።
ለመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ብርቱ ፡ ስለ ጠፋ ፡
ቱርክ ፡ ከያለበት ፡ መጥቷል ፡ እየገፋ ።
ኢትዮጵያን ፡ እግዜር ፡ በጣም ፡ ይወዳታል ፡
አንተ ፡ መሪ ፡ እንድትሆን ፡ አስቦ ፡ ሰጥቷታል ።
እንደዚህ ፡ እያለ ፡ መልአኩ ፡ ሲነግረኝ ፡
የነገሩ ፡ አመጣጥ ፡ በጣም ፡ አስገረመኝ ።

(ብድግ ፡ ብሎ ፡ በኃይል ፡ እነጋገር) ።

እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የእግዜር ፡ መልክተኛ ፤
ትእዛዙን ፡ ሳልፈጽም ፡ እንቅልፍ ፡ የማልተኛ ።
ራስ ፡ ዐሊ ፡ ሲንቁኝ ፡ ድኻ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡
ተንቄ ፡ እንደማልቀር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ያያሉ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ይመስለዋል ፡ ለርሱ ፡ እንዲህ ፡ የሚዘለቅ ፡!
ሙያ ፡ ሳያሳዩ ፡ እንዲያው ፡ መንደላቀቅ ።!!

ገብርዬ ።

አሁን ፡ ያልከው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ትክክል ፡ ነው ፡
እኛም ፡ ዕድልህን ፡ ቈይቷል ፡ ካመነው ።
ስማኝ ፡ የኔ ፡ ካሣ ፡ አድምጠኝ ፡ ጌታዬ ፡
የልቤን ፡ ልናገር ፡ ላንተ ፡ ላለኝታዬ ።
ትሆናለህ ፡ መሪ ፡ ለመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡
ለጐበዞች ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ አርአያ ፡
ለኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፡ የዘላለም ፡ መኩሪያ ።
መልክህ ፡ የሰው ፡ ቢሆን ፡ ልብህ ፡ ነው ፡ ያንበሳ ፡
ፈረስህም ፡ ጐበዝ ፡ ታጠቅ ፡ ነው ፡ መይሳ ፡
ስምህም ፡ ይሆናል ፡ ላገር ፡ መከበሪያ ፡
ለጐበዝ ፡ ለጀግና ፡ ምሳሌ ፡ መጠሪያ ።
ግፋበት ፡ ጌታዬ ፡ ግንባርክን ፡ አትጠፍ ፡
ተሰጥቶሃልና ፡ ዕድልክን ፡ አትለፍ ።
ዳዊት ፡ ጐልያድን ፡ ሲገጥመው ፡ በድፍረት ፡
ሕዝቡን ፡ ለማውጣት ፡ ነው ፡ ከክፉ ፡ ባርነት ።
አንተም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ካሣ ፡ እንድትሆንላት ፡
ቀብቶሃል ፡ እግዜር ፡ የለብህም ፡ ሥጋት ።
ታሪክ ፡ ዐዋቂና ፡ የሚለው ፡ ንግርቱ ፡
ካሣ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሆኖ ፡ ይመራል ፡ መንግሥቱ ።
ስምህ ፡ ለዘለዓለም ፡ ከቶ ፡ የማይረሣ ፡
ትባላለህ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዕጓለ ፡ አንበሳ ።
እንግዲህ ፡ በከንቱ ፡ ጊዜህን ፡ አታጥፋ ፡
ዕጣችን ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንግፋ ።
ቅድሙንም ፡ ቢሆን ፡ ብላሃለች ፡ ታጠቅ ፡
ማመንታት ፡ አያሻም ፡ መንፈስህ ፡ ይጠንቀቅ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ቋራ ፡ ላይ ፡ የበራው ፡ የሰደድ ፡ እሳት ፡
ለትግሬ ፡ ላማራ ፡ ይሆናል ፡ መብራት ።

(በኃይል ፡ እነጋገር) ።

በል ፡ ምራን ፡ እንሂድ ፡ በድል ፡ ወደ ፡ ክብር ፡
ካንተ ፡ ጋራ ፡ ለመሞት ፡ ገብተናል ፡ እድር ።
ያገራችን ፡ ጠላት ፡ መክረው ፡ ተማምለው ፡
በየጠረፉ ፡ ላይ ፡ ሲሰለፍ ፡ ጦራቸው ፡
በሰሜን ፡ በምሥራቅ ፡ ሲሰማ ፡ ድምፃቸው ፡
መይሳው ፡ ካሣ ፡ ነው ፡ የሚበትናቸው ።!!
ሰው ፡ ሐሳቡን ፡ ቈርጦ ፡ ዐላማ ፡ ካበ፻ ፡
የሚያግደው ፡ የለም ፡ ልቡ ፡ ከደረ፻ ።
እኔ ፡ ነኝ ፡ ገብርዬ ፡ የ.ኸንን ፡ የምልህ ፡
እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቴ ፡ የማልለይህ ።!

ደጃች ፡ ካሣ ።

ገብርዬ ፡ ነገርህ ፡ ለልቤ ፡ ተሰምቷል ፡
ክብርን ፡ ለመከተል ፡ ልቦናዬ ፡ ቈርጧል ፡
እውነትም ፡ እንዳልከው ፡ እግዜር ፡ ያለው ፡ ላይቀር ፡
ማመንታትን ፡ ትቶ ፡ መታገል ፡ ነው ፡ ላገር ።
ምኞቴ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ አንተ ፡ እንደምታውቀው ፡
ለኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ ላገሬ ፡ ልማት ፡ ነው ።
ወንዶቹ ፡ ተቀምጠው ፡ ሴቶቹ ፡ ሲነግሡ ፡
ደርቡሾች ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ሊዘምቱ ፡ ተነሡ ።

(ተነሥቶ ፡ እየተንጐራደደ) ።

የነአብርሃ ፡ አጽብሓ ፡ የነካሌብ ፡ አገር ፡
እንዴት ፡ በቁማችን ፡ በደርቡሽ ፡ ትወረር ።?
የጐንደር ፡ ጐበዞች ፡ ወዴት ፡ ደረሳችሁ ፡
የሸዋስ ፡ ጐበዞች ፡ ምን ፡ አሰነፋችሁ ፡

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፬ኛ ፡ ትርኢት ።

የትግሬስ ፡ ጐበዞች ፡ ማነው ፡ ያስተኛችሁ ፤
አውራ ፡ ብታጡ ፡ ነው ፡ ኑማ ፡ እኔ ፡ ልምራችሁ ።
ባንድነት ፡ ሰብስቤ ፡ አውራጆቼን ፡ ሁሉ ፡
እንድትተባበር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሙሉ ።
ሕግ ፡ ደንብ ፡ አውጥቼ ፡ ሕዝቡንም ፡ ሳልበድል ፡
ተፈርተን ፡ ተከብረን ፡ እንድንመሰገን ፡
ስንፈት ፡ ፍርሃትን ፡ ተንከልንም ፡ ትተን ፡
ባንድ ፡ አሳብ ፡ ተመርተን ፡ ብርታት ፡ ከተመላን ፡
ለመጪ ፡ ትውልዶች ፡ ክብር ፡ እናስገኛለን ።
ነጮች ፡ ያገኙትን ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡
የልጅ ፡ ልጆቻችን ፡ እንዲራቀቁበት ።
ያንድነትን ፡ ጕዳይ ፡ እኛው ፡ አደራጅተን ፡
ጠረፍን ፡ ፀጥ ፡ አርገን ፡ አጥርም ፡ አበጅተን ፤
ለኋላ ፡ ብናቈይ ፡ ታላቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡
ይሆንልን ፡ ነበር ፡ የዘለዓለም ፡ ሞ ያ ።
እነዚያም ፡ ልጆቼ ፡ ኋላ ፡ የሚመጡት ፡
ጥበብን ፡ አግኝተው ፡ በዘዴ ፡ እሚሠሩት ፡
ተከብረው ፡ ለመኖር ፡ ምንም ፡ አይሳናቸው ፤
እኛ ፡ ያቀድነውን ፡ ሲያውቅ ፡ ልቦናቸው ።
ብልሆች ፡ ንጉሦች ፡ አገር ፡ የሚያከሩ ፡
ከጐንደር ፡ ቢጠፉ ፡ ከሸዋ ፡ ከሥሩ ፡
ይነግሡ ፡ ይሆናል ፡ ከእኔም ፡ የሚፈሩ ።
ከትግሬም ፡ ይገኛል ፡ ሃይማኖት ፡ አጥባቂ ፤
ጠረፍ ፡ አስከባሪ ፡ ጠላት ፡ አስጨናቂ ።(*)
እግዜር ፡ ነው ፡ የላከኝ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አብነት ፤
ባንድ ፡ ሕግ ፡ አግብቼ ፡ ላኖራት ፡ ባንድነት ።

* አፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ነው ።

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

(በኃይል ፡ እነጋገር) ።

ቃሊን ፡ የማይሰማ ፡ ውጉዝ ፡ አርዮስ ፡ ነው ፡!!
በካራና ፡ በሴፍ ፡ በእሳትም ፡ ጠፊ ፡ ነው ፤!!
የጐንደር ፡ የጐጃም ፡ የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡
የሸዋ ፡ የወሎ ፡ እስላም ፡ ክርስቲያኑ ፡ አረመኔው ፡ ቅሉ ።!
እኔ ፡ ነኝ ፡ ገዥያችሁ ፡ እግዜር ፡ የመረጠኝ ፤
ርኅራኄ የማላውቅ ምሕረትም የሌለኝ ። !
ሜዳውን ፡ ፈፋውን ፡ ዳገቱን ፡ ሮጬ ፡
እኔ ፡ እመራዋለሁ ፡ መንገዱን ፡ መርጬ ።!
እኔ ፡ እገዛዋለሁ ፡ ራሴን ፡ ረግጬ ።!!

ገልሞ ፡ (ወጣ ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ ይገባል) ።

ፈረሰኛ ፡ መጥቷል ፡ ወሬ ፡ የሚሰጠን ፡
እስቲ ፡ ይቅረብና ፡ አሳቡን ፡ ይንገረን ።

ካሣ ።

አስጠራው ፡ ቶሎ ፡ በል ፡ የሚለውን ፡ ልስማው ፤
ከጐንደር ፡ ይሆናል ፡ ተልኮ ፡ የመጣው ።

መልክተኛው ።

ከጐንደር ፡ ተልኬ ፡ ስገሠግሥ ፡ ደረስኩ ፡
ሌቱንና ፡ ቀኑን ፡ እንዳውሬ ፡ እየሮጥኩ ፡
የጐንደር ፡ ከተማ ፡ መላው ፡ በጌምድር ፡
የርስዎን ፡ ጀግንነት ፡ ሁሉም ፡ ሲናገር ፡
እጅዎን ፡ ለመያዝ ፡ እነሆ ፡ ጦር ፡ ታዟል ፡
ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ በፉከራ ፡ መጥቷል ።
የቋራውን ፡ ሽፍታ ፡ አመጣለሁ ፡ ብሎ ፡
በታማኝነቱ ፡ ተገዝቶ ፡ ምሎ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

እስከ ፡ ጥቂት ፡ ቀናት ፡ እዚሁ ፡ ይደርሳል ፡
አሁኑን ፡ ዘዴውን ፡ ማደራጀት ፡ ያሻል ፡
ብለህ ፡ ንገር ፡ ብለው ፡ አባ ፡ ልከውኛል ፤
ብዙዎችም ፡ ጀግኖች ፡ አደራ ፡ ብለውኛል ።

ካሣ ።

ጭምጭምታውን ፡ እንኳን ፡ ቀድመን ፡ ሰምተነዋል ፡
የላከህ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ።
ወንድይራድ ፡ ቢመጣ ፡ ቢሳደብ ፡ ቢዝት ፡
ከቶም ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ቢመጡ ፡ ንግሥት ፡
የቋራው ፡ አንበሳ ፡ የለውም ፡ ሥጋት ።
እግዜር ፡ ያለው ፡ ላይቀር ፡ አንዴ ፡ የጻፈው ፡
በከንቱ ፡ ይሠጋል ፡ ይጨነቃል ፡ ሰው ።
ተው ፡ ዝም ፡ በለው ፡ ይምጣ ፡ ይሁን ፡ እንዳሻው ፡
ፊቱን ፡ አይመልስም ፡ ካሣ ፡ መይሳው ።

ገልሞ ።

ወንድይራድ ፡ ቢፎክር ፡ ቢሰማ ፡ ዛቻው ፡
አያስፈራም ፡ ለኛ ፡ የርሱ ፡ ዘመቻው ።
እግዜርን ፡ ታምነን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በቅን ፡
እንገጥመዋለን ፡ ሌትም ፡ ቢሆን ፡ ቀን ።
ድል ፡ ለተጻፈለት ፡ አንዴ ፡ ለቀባው ፡
ማንም ፡ አያግደው ፡ እስኪደርስ ፡ ቦታው ።
አሁንም ፡ እቴጌ ፡ በከንቱ ፡ ይደክማሉ ፡
ድሉን ፡ ላያገኙ ፡ እንዲያው ፡ ይጓጓሉ ።

ገብርዬ ።

መቼም ፡ በነርሱ ፡ ቤት ፡ እኛ ፡ ደካሞች ፡ ነን ፡
ላንድ ፡ ሽፍታ ፡ አይሰጉም ፡ እቴጌይቱ ፡ መነን ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

እንተ ፡ እንደምትለው ፡ ልባችንን ፡ ቢያውቁት ፡
በቃኝ ፡ ዓለም ፡ ብለው ፡ አልጋውን ፡ በሰጡት ።

ዓለሚ ።

ጠላት ፡ እንዳይደፍረን ፡ እንዳይዘን ፡ ባዕድ ፡
ሰላም ፡ እንድትገኝ ፡ ለመፈጺውም ፡ ትውልድ ።
የሚገዛት ፡ ያሻል ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጠቅሎ ፡
እቴጌን ፡ ማን ፡ ይምከር ፡ ተዉ ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ።

ወ ፡ ተዋበች ።

እንኳንስ ፡ እንደኛ ፡ ገና ፡ ላልታወቀው ፡
አለቅለት ፡ ይሏል ፡ ጃኖ ፡ ለለበሰው ።
ስለዚህ ፡ በእቴጌ ፡ መፍረድ ፡ ያስቸግራል ፡
እንዲያው ፡ ለወጉ ፡ እንኳ ፡ ቢዋጉ ፡ ይሻላል ።

ገልሞ ።

እረ ፡ እንዳይመስላቸው ፡ እኛን ፡ የገመቱን ፡
ወንድራይድስ ፡ ቢሆን ፡ መቼ ፡ አሰበ ፡ ሞቱን ።
እየተሳደበ ፡ እንደዚህ ፡ መምጣቱ ፡
ኀይል ፡ ቢሰማው ፡ ነው ፡ ቢመካ ፡ መንግሥቱ ።
እኛም ፡ አንታለል ፡ እንሁን ፡ ጥንቁቅ ፡
አይገባም ፡ ከቶ ፡ ጠላትን ፡ መናቅ ፡
እነሱም ፡ ይመኩ ፡ በገዛ ፡ ኀይላቸው ፡
እኛም ፡ ሃይማኖትን ፡ ልብ ፡ እናሳያቸው ።

መጋረጃ ።

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

ደጃዝማች ፡ ካሣ ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ ይጐበኛሉ ።

ካሣ ።

እንተ ፡ ማነህ ፤ ?
ባቋቋምህ ፡ ሁሉ ፡ ጐበዝ ፡ ትመስላለህ ።

ወታደር ።

አዎን ፡ ጀግና ፡ ነበርኩ ፡ በረሃ ፡ የለመድሁ ፡
ዝናህን ፡ ሰምቼ ፡ ልከተልህ ፡ መጣሁ ።

ካሣ ።

ይኸኛውስ ፡ ማነው ፤ ?
ቦታው ፡ ጠፍቶብኛል ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የማውቀው ። ?

ወታደር ።

ጊዜው ፡ አያሌ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ ሲያውቁኝ ፡
ከቋራ ፡ ስንወጣ ፡ ጋሜ ፡ ነበርኩኝ ።
በክፉም ፡ በደጉም ፡ ከርስዎ ፡ አልተለየሁ ፡
ታማኝ ፡ አሽከርዎ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ገበየሁ ።

ካሣ ።

ስሙኝ ፡ አርበኞቼ ፡ በኔ ፡ እምነት ፡ ያላችሁ ፡
ተስፋችሁን ፡ ሁሉ ፡ በኔ ፡ የጣላችሁ ።
ልባችሁ ፡ ከፍ ፡ ይበል ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ መሪያችሁ ፡
ሲጠራ ፡ ይኖራል ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ስማችሁ ።

(ካሳ ፡ ሁሉንም ፡ እየዞሩ ፡ ካስተዋሉ ፡ በኋላ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ቆመው ፡ ጦራቸ ውን ፡ ተመርከዘው ፡ ይናገራሉ) ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ሃይማኖትን ፡ ይዘን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡
ለታዘዝነው ፡ ሥራ ፡ እንድከም ፡ በውነት ።
ሞትን ፡ መናቅ ፡ ያሻል ፡ ክብርን ፡ ለማግኘት ፡
አለመንገት ፡ ነው ፡ ለከንቱ ፡ ሕይወት ።
ልባችሁ ፡ ከፀና ፡ካላችሁም ፡ እምነት ፡
አስገኛችኋለሁ ፡ የማያልፍ ፡ ክብረት ።
ኢትዮጵያስ ፡ እንድትሆን ፡ ዘለዓለም ፡ ተፈሪ ፡
እኔ ፡ እሆናታለሁ ፡ ኀይልና ፡ አስከባሪ ።
ሕግ ፡ ደንብ ፡ አውጥቼ ፡ በደንብ ፡ አሳዳሪ ፡
እግዚአብሔር ፡ መረጠኝ ፡ ለርሷ ፡ አስተናባሪ ።
ወየው ፡ ባልተረዱት ፡ ለሚቀወሙኝ ፡
ይሻላቸው ፡ ነበረ ፡ አሁን ፡ ቢያደምጡኝ ።
በከንቱ ፡ ይለፋሉ ፡ መንገዴን ፡ ለማጠር ።
አምላክ ፡ የመረጠኝ ፡ ቅድሙን ፡ ስፈጠር ፡
ልጆቿን ፡ ሰብስቤ ፡ ስሟን ፡ ለማስከበር ።
አሳቤ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይበገር ፡
እንቅልፍም ፡ አይወስደኝ ፡ አንድ ፡ እስኪሆን ፡ አገር ።
ከሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡
የቀድሞ ፡ ነገሥታት ፡ ያቀኑትን ፡ ሁሉ ፡
ሰብስቤ ፡ ባንድ ፡ ዘውድ ፡ እንዲቀላቀሉ ፡
መታገል ፡ መጋደል ፡ አናገኝም ፡ ፋታ ፡
በገደል ፡ በሜዳው ፡ ውጊያ ፡ ጧት ፡ ማታ ።
ለዚህ ፡ ዐይነት ፡ ኑሮ ፡ ቈርጠን ፡ ተነሥተናል ፡
የመረጠኝ ፡ አምላክ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይረዳናል ።
ኃይለኛ ፡ ለመሆን ፡ ድልን ፡ ለማግኘት ፡
በጣም ፡ ያስፈልጋል ፡ ጽኑ ፡ ሃይማኖት ።
ራስንም ፡ አምኖ ፡ ልቡናን ፡ ማጽናት ፡
በገርመሩት ፡ አሳብ ፡ መቀጠል ፡ በምንት ።
ያርበኞች ፡ ተግባር ፡ ነው ፡ የሚሞቱበት ።

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

እምነትና ፡ ተስፋ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ጥላችሁ ፡
አደርሳችኋለሁ ፡ አይጠፋም ፡ ስማችሁ ፤
እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ካላችሁ ።
ፈተናው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ትግላችን ፡ ጠንካራ ፡
ሜዳ ፡ ወንዝ ፡ ማለፍ ፡ መውጣትም ፡ ተራራ ።
ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሆና ፡ በኛ ፡ እስክትመራ ፡
ብዙ ፡ ድካም ፡ አለ ፡ እስኪያልፍ ፡ መከራ ።
በጐጃም ፡ በትግሬ ፡ በሸዋ ፡ በጐንደር ፡
እንሄዳለን ፡ ጐበዝ ፡ ሕዝብን ፡ ለማስገበር ።
አንድነት ፡ ተፈጥሮ ፡ ሁሉም ፡ ሲተባበር ፡
ኀይል ፡ እናገኛለን ፡ ቱርክን ፡ ለማባረር ።
ባንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ሁነን ፡ ሰላምን ፡ ስናገኝ ፡
ትዳር ፡ እንዲቃና ፡ ሀብትም ፡ እንድትገኝ ፡
ላገር ፡ የሚጠቅም ፡ ብዙ ፡ አሳብ ፡ አለኝ ።
አሳቤ ፡ እንዲፈጸም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስመኝ ፤
እኔስ ፡ እሰጋለሁ ፡ ሰይጣን ፡ እንዳይመቀኝ ።
ድንቁርና ፡ በዝቶ ፡ ክፋት ፡ ካሸነፈ ፡
ተቃዋሚ ፡ በዝቶ ፡ ሕዝቡም ፡ ከሰነፈ ፡
ክብሬን ፡ ሳላስነካ ፡ መሞት ፡ ይሻለኛል ፡
ድካምና ፡ አሳቤን ፡ ትውልድ ፡ ያውቅልኛል ፤
ምኞቴንም ፡ ሌሎች ፡ ይፈጽሙልኛል ።

ገብርዬ ።

ሰድልህን ፡ በማመን ፡ ኮከብህን ፡ አይተን ፡
መጣን ፡ ከያለበት ፡ ጀግኖች ፡ ለመሆን ።
እኛ ፡ እንደምንወድህ ፡ አንተም ፡ ካመንከን ፡
መሪያችን ፡ አንተነህ ፡ ማንም ፡ አይነካን ።
እዘዝ ፡ ዝግጁ ፡ ነን ፡ ቃልህን ፡ ለመፈጸም ፡
ላገር ፡ ለክብር ፡ ነው ፡ የምናፈሰው ፡ ደም ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ገልሞ ።

እንሂድ ፡ እንበለው ፡ በሴፍ ፡ በጐራዴ ፡ !
ተብለን ፡ እንተርም ፡ የቋራ ፡ ወንበዴ ።
አሁን ፡ ይረዱታል ፡ መሆኑን ፡ የዋዛ ፡
ካሣ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉንም ፡ ሲገዛ ።!!

ሦስት ፡ መልክተኞች ፡ ይደርሳሉ ።

ካሣ ።

ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ የት ፡ ደረሰ ፡ ይላሉ ፡ ?
ወሬስ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ። ?

፩ኛ ፡ መልክተኛ ።

እንዳካሄዳቸው ፡ እንደ ፡ ገመትነው ፡
እስከ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ የሚደርስ ፡ ነው ።
ወሬም ፡ አያሌ ፡ ነው ፡ መሣሪያም ፡ አብዝቷል ።
ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ በጣሙን ፡ ይዝታል ።
«ይህንን ፡ ወንበዴ ፡ አባቴ ፡ ያልቀጣው ፡
«እጄን ፡ ጐትቼ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የማመጣው ።
«ደርሶ ፡ ላንድ ፡ ሽፍታ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዋጋ ፡
«እንሰው ፡ ወይም ፡ ለሱ ፡ ካሽከሮች ፡ ቢዋጋ ።
ይሻለው ፡ በነበር ፡ አርፎ ፡ ቢቀመጥ ፡
ከናቱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ኮሶ ፡ መሸምጠጥ ።
እንደዚህ ፡ እያለ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ያጠፋል ፡
አዝማሪ ፡ አቁሞ ፡ ብዙ ፡ ይለፈልፋል ።

ካሣ ።

ሕዝቡስ ፡ ምን ፡ ይለኛል ፡ ከተማው ፡ መንደሩ ። ?

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

፪ኛ ፡ መልክተኛ ።

ከተማውም ፡ ሆነ ፡ መላው ፡ በጌምድሩ ፡
ካህናቱም ፡ ቢሆን ፡ ሕዝቡ ፡ ባላገሩ ፡
የሚመካከረው ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ነገሩ ።
ንግርት ፡ አለ ፡ እያለ ፡ ነቅቷል ፡ ወታደሩ ።
መቼም ፡ ወታደሮች ፡ ጀግና ፡ ይወዳሉ ፡
ቴዎድሮስ ፡ የሚባለው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡
እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ይንሾካሾካሉ ።
ንግሥቲቱም ፡ ቢሆን ፡ ይህንን ፡ ሰምተው ፡
እዘምታለሁ ፡ ብለው ፡ ቈርጠው ፡ ተነሥተው ።
ራስ ፡ ዐሊም ፡ ከተው ፡ ለጦር ፡ ሲመቻቹ ፡
ወንድይራድ ፡ ይበቃል ፡ አሉ ፡ መካሮቹ ።

ገብርዬ ።

እንግዲህ ፡ ከመጡ ፡ እኛም ፡ ቦታ ፡ እንያዝ ፡
ቃፊሮች ፡ ይድፈጡ ፡ ካፋፍና ፡ ከወንዝ ።

ካሣ ።

የሁለት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ገና ፡ ከቀራቸው ፡
ወደኛ ፡ ሲመጡ ፡ እኛ ፡ እንሂድባቸው ። !
ያን ፡ ተረተር ፡ አልፈን ፡ ከሜዳው ፡ ስንደርስ ፡
በካራና ፡ በጦር ፡ በእግርም ፡ በፈረስ ፡
እንገጥማቸዋለን ፡ ግምባር ፡ ለግንባር ፡
እንዲያጠኑ ፡ ከኛ ፡ የጦርን ፡ ተግባር ።

መጋረጃ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ካሣና ፡ ተዋበች ፡(ካሣ ፡ ከውጭ ፡ ይገባል) ።

ካሣ ።

ደኅና ፡ ሁኝ ፡ ተዋበች ፡ በጸሎትሽ ፡ እርጂኝ ፡
አያትሽ ፡ ጦር ፡ ልከው ፡ ፈለጉ ፡ ሊወጉኝ ።
ቅድሙንም ፡ ቢሆን ፡ እኔን ፡ አልወደዱኝ ፡
ምን ፡ ይሆን ፡ ምክንያቱ ፡ እንደዚህ ፡ የጠሉኝ ።?

ተዋበች ።

ምክንያቱንማ ፡ አንተስ ፡ መች ፡ አጣኸው ፡
በሞያህ ፡ በዕድልህ ፡ ተመቅኝተውህ ፡ ነው ።
አባቴም ፡ ከርሳቸው ፡ መቼም ፡ አይለዩ ፡
ልባቸው ፡ አያርፍም ፡ ያንተን ፡ ሞት ፡ካላዩ ።
ግን ፡ እኔ ፡ እማስበው ፡ በጣሙን ፡ የማዝነው ፡
የሰጠኝን ፡ ዕድል ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።
ባንድ ፡ ፊት ፡ አባቴ ፡ ባንደኛው ፡ ለባሌ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ኀዘኔ ።
የሁለታችሁ ፡ ጠብ ፡ መከራ ፡ ነው ፡ ለኔ ።
ያንዳችሁ ፡ ማሸነፍ ፡ ኀዘን ፡ ይሆነኛል ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሳላይ ፡ ብሞት ፡ ይሻለኛል ።

ካሣ ።

ተዋበች ፡ ታውቂያለሽ ፡ እኔ ፡ እንደምወድሽ ፡
በውነት ፡ ከልቤ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ የምወቅስሽ ።
በጣም ፡ መገፋቴን ፡ ልብሽ ፡ እያወቀው ፡
የምታመነኝ ፡ ላባት ፡ አድልተሽ ፡ ነው ።
ታጠቅ ፡ ብለሽኝ ፡ ነው ፡ የተነሣሁት ፡
ይኸው ፡ ታጥቂያለሁ ፡ ገድዬ ፡ ልሞት ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፲ኛ ፡ ትርኢት ።

ተዋበች ።

እንዳይመስልህ ፡ አንተ ፡ አሳቤን ፡ የለወጥኩ ፡
ላባቴ ፡ ሳስቼ ፡ ውርደትን ፡ የመረጥኩ ።
አንተም ፡ ታውቀዋለህ ፡ የሴት ፡ ሆድ ፡ ቡቡ ፡ ነው ፡
አይችልም ፡ ሊጸና ፡ እንዴ ፡ በቈረጠው ።
ስለዚህም ፡ እኔ ፡ በፊት ፡ ቀሰቀስኩህ ፡
ራሴ ፡ መልሼ ፡ አታሸንፍ ፡ አልኩህ ፡
ምናባቴ ፡ ላድርግ ፡ ግራ ፡ ቢገባኝ ፡ ነው ፡
ለወንዶች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ መቁረጥ ፡ የተሰጠው ።

ካሣ ።

ለኔም ፡ ይሰማኛል ፡ ይኸ ፡ ሥጋትሽ ፡
ካባት ፡ ከዘመድሽ ፡ ሲዋጋ ፡ ባልሽ ።
እንኳንስ ፡ ለሴቶች ፡ ያስቸግራል ፡ ለወንድ ፡
በቈረጡት ፡ አሳብ ፡ መሄድ ፡ ባንድ ፡ መንገድ ።
ብርታት ፡ ያስፈልጋል ፡ መሆን ፡ እንደ ፡ ብረት ፡
ምኞት ፡ እስኪፈጸም ፡ መታገል ፡ መቃተት ።
አንቺም ፡ ታውቂዋለሽ ፡ የልቤን ፡ ምኞት ፡
ልብሽ ፡ ከኔ ፡ ይሁን ፡ ይተው ፡ ማመንታት ።
አንቺ ፡ ትተረያለሽ ፡ ለዘርሽ ፡ አሥራት ፡
እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ያባ ፡ ታጠቅ ፡ ሚስት ፡
በባልዋ ፡ የምትወርስ ፡ ያባትዋን ፡ መንግሥት ።

ተዋበች ።

ድኻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ንቀት ፡ ስላሳዩህ ፡
በጣም ፡ ተቈጭቼ ፡ ታጠቅ ፡ ተነሥ ፡ አልኩህ ።
አባቴን ፡ ነቅፌ ፡ አንተን ፡ መከተሌ ፡
ልቤ ፡ ቢነግረኝ ፡ ነው ፡ መሆንኽን ፡ ዕድሌ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ሆኖም ፡ ምን ፡ ብወድህ ፡ በጣም ፡ ብቈጭልህ ! ፡
የልቢን ፡ መጨነቅ ፡ ምንም ፡ አልሰውርህ ።

ኮሚ ።

ምንድርነው ፡ ጭንቀቱ ፡ ከቈረጠ ፡ ልብሽ ፡
ክብር ፡ ለማግኘት ፡ ነው ፡ የሚዋጋው ፡ ባልሽ ።
በእውነት ፡ ልንገርሽ ፡ አድምጪኝ ፡ ተዋበች ፡
ቈርጠን ፡ ተነሥተናል ፡ እንግዲህ ፡ አታመንች ።
ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ትግል ፡ የጀመረ ፡
ተበደልኩም ፡ ብሎ ፡ ከልብ ፡ ያመረረ ፡
እውነት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ የተከራከረ ፡
አይገባውም ፡ ኩቶ ፡ ከመንገድ ፡ መመለስ ፡
ስንፍና ፡ አስገብቶ ፡ መንፈስን ፡ ማለስለስ ።
ቊርጠኛውን ፡ አሳብ ፡ አጥብቆ ፡ መከተል ፡
ፈተናውን ፡ ሁሉ ፡ ጨክኖ ፡ መቀበል ።
ይህ ፡ ነው ፡ ሕግጋቱ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተግባሩ ፡
ፈተናውን ፡ ሲያልፈው ፡ እንዲታወቅ ፡ ክብሩ ።
ሁለት ፡ ወዶ ፡ አይሆንም ፡ ለተጥቃት ፡ ኑሮ ፡
ከንቱን ፡ መናቅ ፡ ያሻል ፡ ለመኖር ፡ ተከብሮ ።
በቈረጡት ፡ አሳብ ፡ ይሉኝታን ፡ ካስገቡት ፡
ልብን ፡ ሰውነትን ፡ ምክር ፡ ከጠየቁት ።
ዘዴ ፡ ምክር ፡ ትዕግሥት ፡ ፍርሃትም ፡ ይግሞ ፡
መንፈስን ፡ ሲወሩት ፡ ይወድቃል ፡ ተዳክሞ ።
ስለዚህም ፡ እኛ ፡ ቈርጠን ፡ በሚገባ ፡
ማመንታት ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ሆድሽ ፡ እንዳይባባ ።

ተዋበች ።

አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ሆዳችን ፡ ቢቈርጥም ፡
ያጋጣሚው ፡ ክፋት ፡ መሰማቱ ፡ አይቀርም ።

፲ኛ ፡ ትርኢት ።

ጥቅምን ፡ ሆነ ፡ ክብርን ፡ አንዱን ፡ ከፈቀዱት ፡
የንደኛውን ፡ መንገድ ፡ መርጠው ፡ ቢከተሉት ።
ይሉኝታን ፡ ጨምሮ ፡ ልብን ፡ ካልመከሩት ፡
ስሜትን ፡ ምኞትን ፡ በምን ፡ ይመጥኑት ።
ማናቸውም ፡ ነገር ፡ መጠን ፡ ከሌለበት ፡
ምንም ፡ መልካም ፡ ቢሆን ፡ ሚዛን ፡ ካልገባበት ፡
የሰው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መነቀፍ ፡ አለበት ።
ስለዚህም ፡ ልብን ፡ ቢሰሙት ፡ አይከፋም ፡
ልቡን ፡ ያዳመጠ ፡ ሰውነት ፡ አያጣም ።
ልቢ ፡ ተሸብሮ ፡ በዕድሌ ፡ ቢያዝንበት ፡
ስንፍና ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ አንተ ፡ አትፍረድበት ።
ኀዘኔ ፡ ላባቴ ፡ ላንተም ፡ ለባሌ ፡ ነው ፡
በንዲህ ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ እንዴት ፡ ይስ ፡ ይበለው ።
ከማንም ፡ አብልጨ ፡ እኔ ፡ እንደምወድህ ፡
አትጠራጠርም ፡ ይረዳሃል ፡ ልብህ ።

ካሣ ፡ (በትካዜ) ።

እኔም ፡ ቅሬታዬን ፡ ባፈ ፡ ብሰውረው ፡
ስሜቴን ፡ ጨቁኜ ፡ አልሰማህም ፡ ብለው ።
ምን ፡ እንኳን ፡ ብጨክን ፡ ባስገድደው ፡ ልቢን ፡
ማሰቢኮ ፡ አልቀረም ፡ የምወዳት ፡ ሚስቴን ።
በገደል ፡ በሜካው ፡ ስኖር ፡ በሽፍትነት ፡
ነፃ ፡ ጎበዝ ፡ ሆኜ ፡ ስሄድ ፡ በያለበት ፡
በልቢ ፡ ሳልሠጋ ፡ አሳብ ፡ ሳይገባበት ፡
አንቺን ፡ ካጠትሁ ፡ ወዲህ ፡ ልቢን ፡ ገባው ፡ ስንፈት ።
ሞትና ፡ መከራን ፡ ማሰብ ፡ ዠምሬያለሁ ፡
ካንቺ ፡ እንዳልነጠል ፡ ውስጡን ፡ እሰጋለሁ ።
ይህ ፡ ከንቱ ፡ ስንፍና ፡ በልቢ ፡ካደረ ፡
በፈቃዴ ፡ ብቻ ፡ መመራቴ ፡ ቀረ ።

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ተዋበች ።

ፍቅር ፡ የሚባለው ፡ እንዲህ ፡ የሚያስጨንቅ ፡
ከሰው ፡ ስሜት ፡ ሁሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ እሚልቅ ።
ልብ ፡ ላለው ፡ ሁሉ ፡ የማይቀር ፡ ዕዳ ፡ ነው ።
ማነው ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እሱን ፡ ያላወቀ ፡
ለሚወደው ፡ ሰግቶ ፡ ልቡ ፡ ያልተጨነቀ ።
ሊገባው ፡ አይችልም ፡ የፍቅር ፡ ስሜቱ ።
ድካምና ፡ ልፋት ፡ ሆኖበት ፡ ሕይወቱ ፡
ደስታን ፡ ሳያውቃት ፡ ይደርሳል ፡ ከሞቱ ።

ካሣ ።

ፍቅር ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ቢሆንም ፡ መሪያቸው ፡
ጀብዱ ፡ ሙያና ፡ ጽድቅ ፡ ታምር ፡ ቢያሠራቸው ።
ከቶ ፡ ምን ፡ ቢጸና ፡ ስሜቱም ፡ ቢያይል ፡
ተግባርን ፡ ሊያስረሳ ፡ ምን ፡ ቢሆን ፡ አይችል ።
ስለዚህም ፡ እኛ ፡ ምንም ፡ ብንዋደድ ፡
ክብራችን ፡ እንዲድን ፡ ልባችን ፡ ይገደድ ።
ደኅና ፡ ሁኚ ፡ ተዋበች ፡ የልቤ ፡ ወዳጅ ፡
ሥጋት ፡ አሳብ ፡ ትተሽ ፡ ደስታን ፡ አዘጋጂ ።(ትቷት ፡ ይሄዳል)።

ተዋበች ፡ (ብቻዋን ፡ በትካዜ ፡ እንጋገር) ።

ከዚህ ፡ ከፈተና ፡ ከልብ ፡ ሥቃይ ፡
ምንቸገረው ፡ ነበር ፡ ፀሐይን ፡ ባላይ ።
ያኔ ፡ ተማርኬ ፡ ቱርክ ፡ ሲወስደኝ ፡
ካሣን ፡ እግዜር ፡ ልኮ ፡ ለምን ፡ አዳነኝ (*)

* ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከግብጾች ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ ተማርከው ፡ ሙሳ ጋሻ ፡ የሚባለው ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ ሊወስዳቸው ፡ ሳለ ፡ ራሳቸውን ፡ በመርዘኛ ፡ ጩቤ ፡ ወግተው ፡ ሊሞቱ ፡ ተዳርሰው ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ ምንም ፡ ሽፍታ ፡ ቢሆኑም፡ ከነገራቸው ፡ ጠላት ፡ ጋራ ፡ ይዋጉ ፡ ነበርና ፡ ማታውን ፡ በግብጾች ፡ ሰፈር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችንም ፡ አውጥተው ፡ የተወጉትንም ፡ መርዝ ፡ ደሙን ፡ መጥጠው ፡ አድነዋቸው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተዋድደው ፡ ተጋቡ ፡ ይባላል።

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

ሞቼ ፡ ተረስቼ ፡ መና ፡ ሆኜ ፡ ብቀር ፡
ከዚህ ፡ ከፈተና ፡ ባልደረስኩም ፡ ነበር ።
አዬ ፡ ጉድ ፡ ሴት ፡ መሆን ፡ ደካማ ፡ ፍጥረት ፡
ልቤኮ ፡ ስሜቱን ፡ መቻል ፡ አቅቶት ።
ሲሸበር ፡ ሲዋልል ፡ በከንቱ ፡ ስንፈት ፡
ወንዱንም ፡ ሞከረው ፡ ሊያስተምረው ፡ ፍርሃት ።
እሱስ ፡ በእውነት ፡ እንዴት ፡ ይታዘበኝ ፡
እንዲህ ፡ ሳመነታ ፡ እንዴት ፡ ይገምተኝ ።
ተነሥ ፡ ታጠቅ ፡ ብዬ ፡ አስቈጭቼ ፡ ልቡን ፡
ደግሞ ፡ እኔው ፡ መልሼ ፡ ላስለውጥ ፡ አሳቡን ።
ነዘኔን ፡ ፍርሃቱን ፡ ገልጬ ፡ ነገርኩት ፡
ይሉኝታ ፡ ሰውነት ፡ እያልኩ ፡ አባባሁት ።

ገረድ ፡ (ንግግርዋን ፡ ታዳምጥ ፡ የነበረች) ።

እመቤቴ ፡ አይዘኑ ፡ እንደዚህ ፡ አምርረው ፡
ልብዎ ፡ ቢባባ ፡ ከቶ ፡ ነውር ፡ የለው ።
ላባቱ ፡ ለባሉ ፡ የማይሣሣ ፡ ማነው ፡ ?
የነገሩ ፡ አኳኋን ፡ ሲታሰብ ፡ በውነቱ ፡
ልብዎ ፡ ቢሠጋ ፡ ቢጨነቅ ፡ ላባቱ ፡
ምን ፡ ከፋት ፡ አለበት ፡ ምንድርነው ፡ ጥፋቱ ።
ይልቅስ ፡ ልንገርዎ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡
ባልዎ ፡ ሸፍቶ ፡ ሲበጠብጥ ፡ አገር ፡
እንደዚህ ፡ ሲሠራ ፡ ተው ፡ ብለው ፡ ቢመክሩት ፡
መልካም ፡ አረጉ ፡ እንጂ ፡ ምንድርነው ፡ ያጠፉት ።
ይልቅስ ፡ በውነቱ ፡ የሚያስወቅስዎ ፡
ለባልዎ ፡ አድልተው ፡ ሲጣሉ ፡ ካባትዎ ።

ተዋበች ፡ (በቍጣ ፡ እንጋገር) ።

አመቴ ፡ ደፋር ፡ ነሽ ፡ ምላስሽ ፡ ረዝሞ ፡ !
እንዲህ ፡ ከመናገር ፡ ምነው ፡ ብትይ ፡ ዝም ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ቅድሙን ፡ ከጧቱ ፡ ባሌን ፡ መርጫለሁ ፡
ዕድልህ ፡ ዕድሌ ፡ ብዬው ፡ መጥቻለሁ ።
እስከ ፡ መጨረሻው ፡ እከተለዋለሁ ።

ገረድ ።

ሆኖም ፡ ካባትዎ ፡ ባልዎ ፡ ሲዋጋ ፡
ባልን ፡ ሲከተሉ ፡ ይወቅስኋል ፡ ሥጋ ።

ተቆበች ።

ሥጋን ፡ ከደመጡት ፡ ልብንም ፡ ካባቡት ፡
ምን ፡ ቢሆን ፡ አይቻል ፡ ለመድረስ ፡ ካሰቡት ።
ለሰው ፡ ልጅ ፡ ዕድሉን ፡ ለይቶ ፡ ሲሰጠው ፡
ራሱ ፡ መርምሮ ፡ ዐውቆ ፡ ካልገመተው ፡
ዕድልም ፡ መከራም ፡ የተያያዘ ፡ ነው ።
በመከራችን ፡ ላይ ፡ ዕድል ፡ አይታጣበት ፡
በዕድላችን ፡ ደግሞ ፡ እንከን ፡ አይጠፋበት ።
ዕድል ፡ ብለን ፡ ያልነው ፡ ኋላ ፡ ይቈጨናል ።
መከራ ፡ እሚመስለው ፡ ዕድል ፡ ይሆነናል ፡
ዐላማውን ፡ ዐውቆ ፡ ካልቈረጠ ፡ ልቡ ፡
በጣም ፡ ያስቸግራል ፡ ለመድረስ ፡ ከግቡ ።

ገረድ ።

ልብዎም ፡ ቢጨክን ፡ ቢጸና ፡ አሳብዎ ፡
የሚገባ ፡ አይደለም ፡ መራቅ ፡ ካባትዎ ።
በባል ፡ ከሚገኘው ፡ ማዕርግ ፡ ክብርዎ ፡
ይበልጥ ፡ የለምን ፡ ያለው ፡ በዘርዎ ።?

ተቆበች ።

ካባት ፡ ያገኘሁት ፡ ክብርና ፡ ማዕርግ ፡
በርግጥ ፡ ይረዳኛል ፡ ልቤን ፡ ከፍ ፡ እንዳደርግ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሁለተኛ ።

ይመክረዋል ፡ በጣም ፡ እንዲያስብ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ክብር ፡ እንዳትለየው ፡ ውርደትን ፡ እንዳያይ ።
ስለዚህ ፡ ያባት ፡ ክብር ፡ የዘርም ፡ ምስጋና ፡
ልብን ፡ እያኮራ ፡ ክብርንም ፡ ቢያስጠና ፡
ያስገድዳል ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ይበቃል ፡ ዝና ።
ዘር ፡ ውልደትን ፡ ቈጥሮ ፡ ባባት ፡ ቢመካበት ፡
እያስመሰግንም ፡ ሞያ ፡ ካልሠሩበት ።
ከትንሽ ፡ ተወልዶ ፡ ክብርን ፡ የፈጠጠ ፡
በምግባር ፡ በሥራ ፡ በሞያ ፡ የበለጠ ።
ባላባት ፡ ይሆናል ፡ በገዛ ፡ ምግባሩ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አለው ፡ መሠረተ ፡ ክብሩ ።

መጋረጃ ።

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

(የወንድይራድና ፡ የካሳ ፡ ወታደሮች ፡ ሲሸልሉና ፡ ሲፎክሩ ፡ ይሰማል ፡ የወንድ ይራድ ፡ ወገኖች ፡ አይታዩም ፡ ድምፃቸውና ፡ ንጋሪቱ ፡ እንቢልታው ፡ ሽለላው ፡ በሩቅ ፡ ይሰማል) ።

የወንድይራድ ፡ ሽላይ ።

ያመፀኛ ፡ ጠላት ፡ አባ ፡ ደፋር ፡ ወንዶ ፡
አንገቱን ፡ ቈራርጠው ፡ በሰፍ ፡ በጐራዶ ።

ካሣ ፡ (ለሽላይ) ።

እንኳንስ ፡ ደጃዝማች ፡ ቢመጣም ፡ ራሱ ፡
አይታገድ ፡ ካሣ ፡ ተነሥቷል ፡ ፈረሱ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

የወንድይራድ ፡ ወገን ።

ይሻልሃል ፡ ካሣ ፡ ኋላ ፡ ከመጸጸት ፡
አቅምህን ፡ ገምተህ ፡ ብትጠይቅ ፡ ምሕረት ።

የካሣ ፡ ወገን ።

እያንገራበደ ፡ ቢያሰማ ፡ ፊኡኸቱን ፡
ቈርጧል ፡ እንዴ ፡ ካሣ ፡ አይመልስም ፡ ፊቱን ።

የወንድይራድ ፡ ወገን ።

በለው ፡ በጠመንዣ ፡ በጐራዴም ፡ በለው ፡
ይገባዋል ፡ ቅጣት ፡ እንዲህ ፡ የቀበጠው ።

የካሣ ፡ ወገን ።

ወንድ ፡ ከቈረጠ ፡ ከበዛ ፡ ምሬቱ ፡
የሚያግደው ፡ የለም ፡ አይበርድም ፡ ንዴቱ ።

(የደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ ነጋሪት ፡ ይሰማል ፡ ፈረስ ፡ ሲያስካካና ፡ እንቢልታም ፡ ፉከራም ፡ ይሰማል) ።

(የደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ፡ መልክተኛ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ይናገራል) ።

መልክተኛ ።

እጃችሁን ፡ ስጡ ፡ በከንቱ ፡ እንዳታልቁ ፡
መንግሥት ፡ ማረ ፡ ነው ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቁ ፡
ይላሉ ፡ ደጃዝማች ፡ መልሱን ፡ ቶሎ ፡ አስታውቁ ።

(የካሣ ፡ ወታደሮች ፡ ይስቁበታል) ።

ካሣ ።

እንኳንስ ፡ ወንድይራድ ፡ ቢመጡ ፡ ንግሥት ፡
ይቅርታ ፡ አንጠይቅም ፡ ቢመጣብን ፡ ሞት ።
ይልቅስ ፡ ንገረው ፡ ለደጃች ፡ ወንድይራድ ፡
በስድብ ፡ አይደለም ፡ ጎበዝ ፡ የሚዋረድ ።

Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

ትምክትም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ልቡን ፡ ላመነው ፡
ቶሎ ፡ እንግጠምና ፡ ልኩን ፡ ይወቀው ።

መጋረጃ ።

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

(ካሣ ፡ ከጦላ ፡ ሥር ፡ ተቀምጧል ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ምርኮኞቹ ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ወታደሮቹ ፡ ቈመዋል ፡ ደጃች ፡ ወንድይራድ ፡ ተይዞ ፡ ይመጣል ፡ የካሣ ፡ አሽከሮች ፡ ይፎክራሉ ፡ የማረኩትንም ፡ ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ ያስቀምጣሉ) ።

ካሣ ።

(በመውቀስና ፡ በማፌዝ) ።

ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ መሳደብ ፡ መፎከር ፡
ድልን ፡ ሳያገኙ ፡ መመካት ፡ መወጠር ፡
ከውርደት ፡ ያደርሳል ፡ በጣምም ፡ ከማፈር ።
፩ግናን ፡ ፩ግና ፡ አውቆት ፡ ሲል ፡ እንወዳደር ፡
አይገባም ፡ ከቶ ፡ ጸያፍን ፡ መናገር ።
እናቴን ፡ ጨምረህ ፡ አንተ ፡ የምትሰድበኝ ፡
ያዋረድህ ፡ መስሎህ ፡ ድንጉጥ ፡ የምታገኝ ።
እኔ ፡ ግን ፡ አላፍርም ፡ ድኻ ፡ ነው ፡ ትውልዴ ፡
ድኽነት ፡ ይዞኝ ፡ ነው ፡ የቈረጠው ፡ ሆዴ ።
በኮሶ ፡ ያደገው ፡ መራር ፡ ነው ፡ መንፈሴ ፡
ችግርን ፡ ሳታውቂት ፡ እናንተ ፡ ፈሰሴ ።
ድኻ ፡ እያላችሁ ፡ ሰውን ፡ የምትንቁ ፡ (*)
ደርሶ ፡ ስትመኩ ፡ ስትንደላቀቁ ፡
ጌትነት ፡ አይዘልቅም ፡ በድኻ ፡ ከሳቁ ።

* በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገብተው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ መኳንንቱ ፡ ያደረጉባቸውን ፡ ሐሜትና ፡ ያሳዩዋቸውን ፡ ንቀት ፡ በማስታወስ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

(ብድግ ፡ ይላል) ።

እኢም ፡ እኮራለሁ ፡ በገዛ ፡ ድኸነቴ ፡
ግን ፡ ተሰድባ ፡ አትቀርም ፡ ያች ፡ ደጓ ፡ እናቴ ።
አንተም ፡ ለጥጋብህ ፡ እንዲሆንህ ፡ ትምህርት ፡
በቃህ ፡ አልከሀ ፡ ድረስ ፡ ማታና ፡ ጥዋት ፡
ትጠጣለህ ፡ ኮሶ ፡ መልካም ፡ መድኀኒት ፡
ጥቂት ፡ እንዲቀንስ ፡ የልብህ ፡ ትዕቢት ።

ኮማ ።

(እየተንጐራደደ ፡ ለወታደሮች) ።

ጎሽ ፡ እንዳልላችሁ ፡ አሁን ፡ ከጥዋቱ ፡
የምንወጣው ፡ ብዙ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ዳገቱ ።
ቢሆንም ፡ የዛሬው ፡ የሚያስመሰግን ፡ ነው ፡
አንድ ፡ ለመቶ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ የገጠምነው ።
ምርኮኛው ፡ ይቈጠር ፡ እሬሳም ፡ ቅበሩ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ንሴብሕ ፡ ለክብሩ ።

(ለምርኮኞቹ) ።

እናንተ ፡ ወታደሮች ፡ ስሙኝ ፡ ልንገራችሁ ፡
እኔን ፡ እንድትወጉ ፡ በትእዛዝ ፡ መጥታችሁ ፡
የሎሌነት ፡ ተግባር ፡ ፈጸማችሁ ፡ ከልብ ፡
ቂምም ፡ በናንተ ፡ የለኝ ፡ በቀልም ፡ አላስብ ።
አውቃለሁ ፡ ወታደር ፡ መታዘዝ ፡ ግብራችሁ ፡
ቀኙ ፡ ለኛ ፡ ሁኖ ፡ ከተማረካችሁ ፡
እኔን ፡ ተከተሉኝ ፡ ልምራችሁ ፡ ወደ ፡ ድል ፡
አሳያችኋለሁ ፡ እንደሚኖር ፡ በዕድል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

እጓለ ፡ አንበሳ ፡ ዳግማዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በጕልማሳነት ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከመቅደላ ፡ ምሽግ ፡ አፋፉ ፡ ላይ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

መቅደላ ፡ ያፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የጦር ፡ ሠፈር ።

Scanned with CamScanner



የአሮጌ ፡ ውጊያ ።

Scanned with CamScanner

የእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ የመቅደላን ፡ ምሽግ ፡ እንደወረረ ።

Scanned with CamScanner



አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንደሞቱ ፡ ካንድ ፡ ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡
በእጁ ፡ እንደሳላቸው ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner



በለንደን ፡ የሚገኘው ፡ የደጃዝማች ፡ ዓለማየሁ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መቃብር ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

(ወታደሮቹ ፡ እሺ ፡ እሺ ፡ ይላሉ) ።

ካሣ ፡ (ለገብርዬ) ።

በል ፡ ገብርዬ ፡ እያየህ ፡ ስንቅም ፡ አድላቸው ፡
መሣሪያቸውንም ፡ መልሰህ ፡ ስጣቸው ።
የቆሰሉትንም ፡ ሰፈር ፡ ውሰዷቸው ።
ለረፍትም ፡ ጊዜ ፡ የለ ፡ አሁን ፡ እንነሣ ፡
ራስ ፡ ዐሊ ፡ አለበት ፡ ከተፍ ፡ እንዳንበሳ ።
ድንጋጤው ፡ ሳይለቀው ፡ ሳይዘራ ፡ እሱ ፡ ነፍስ ፡
ዐሊን ፡ እናጣድፈው ፡ እንደ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ።
ደግሞም ፡ እንበራለን ፡ ወደ ፡ ቢጌምድር ፡
እቴጌን ፡ ልንማርክ ፡ ልንመልስ ፡ ብድር ። (*)

መጋረጃ ።

፬ኛ ፡ ትርኢት ።

(በእቴጌ ፡ መንን ፡ እልፍኝ) ።

መንነስ ።

ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ በልሜ ፡ ያየሁት ፡ አስግቶኝ ፡
ልነግርዎ ፡ መጣሁ ፡ ግርማዊት ፡ ያድምጡኝ ።
ካሣና ፡ ወንድይራድ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተጋጥመው ፡
ወንድይራድ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ካሣ ፡ ሲማርከው ፡
ሕዝቡም ፡ ተሰብስቦ ፡ አንተ ፡ ምራን ፡ ሲለው ።
ካሣ ፡ በነጭ ፡ ፈረስ ፡ ወደርስዎ ፡ ሲመጣ ፡
በርስዎ ፡ እየዛተ ፡ ሲፎክር ፡ ሲቆጣ ።
ከቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ሲገባ ፡ ስላየሁ ፡
ተደናገጥኩና ፡ ልነግርዎ ፡ መጣሁ ።

* እቴጌ ፡ ማን ፡ በንግርቱ ፡ ካሣን ፡ ድል ፡ የምታደርግ ፡ ሴት ፡ ነች ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ቀድመው ፡ ሄደው ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ ።

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

እቴጌ ፡ (በቍጣ) ።

ሕልምም ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ ከፍርሃት ፡ የመጣ ፡
ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢነገረኝ ፡ በርግጥ ፡ እንዲቀጣ ።
እርስዎም ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አይናገሩ ፡
በሕልም ፡ በወሬ ፡ አይሸበር ፡ አገሩ ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ (ከውጭ ፡ ይገባሉ) ።

የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ መጣሁ ፡ ልነግራችሁ ፡
ወንድይራድ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ተማረከላችሁ ።

እቴጌ ።

ይህን ፡ ዐይነት ፡ ወሬ ፡ ከወዴት ፡ ተሰማ ፡
ከባላገር ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ከከተማ ።

ራስ ፡ ዐሊ ።

እናቴ ፡ ይመኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡
ወንድይራድ ፡ ተማርኳል ፡ አይጠራጠሩ ።
ከጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሸሽቶ ፡ የመለጠ ፡
መጥቷል ፡ ሊነግርዎ ፡ ቀኛዝማች ፡ በለጠ ።

መንዡሲው ።

በሕልሜ ፡ ያየሁትን ፡ አሁን ፡ ስነግርዎ ፡
አላምንም ፡ ብለውኝ ፡ ሐሰት ፡ ሲመስልዎ ፡
ይኸውና ፡ ደረሰ ፡ ተረገጠልዎ ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ (ለልፍኝ ፡ አሽከር) ።

ሂድ ፡ ጥራው ፡ በለጠን ፡
ነገሩን ፡ ዘርዝሮ ፡ በሥራት ፡ ይንገረን ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

መነዙሴ ።

ቀኛዝማች ፡ በለጠ ፡ ሊያስረዳ ፡ ከመጣ ፡
እስቲ ፡ ወጣ ፡ ብዬ ፡ ተመልሼ ፡ ልምጣ ።

እቴጌ ፡ (በቊጣ) ።

ይቈዩ ፡ ይቀመጡ ፡ !
እርስዎም ፡ ነገሩን ፡ በሥራት ፡ ያድምጡ ።

እቴጌ ፡ (ለበለጠ) ።

አንድ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ መያዝ ፡ አቅቷችሁ ፡
እርሱ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ትማረካላችሁ ። !
እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ቢያይል ፡ ነው ፡ ?
ድል ፡ ለመንሣትና ፡ ሊማርክ ፡ የቻለው ። ?

በለጠ ።

ትላንት ፡ ላባቴ ፡ እንደነገርኳቸው ፡ (መነዙሴው ፡ ያፍራል) ፡
ርግጥ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ ድል ፡ የማድረጋቸው ።
ዐሥር ፡ ፊታውራሪ ፡ ኻያ ፡ ቀኛዝማቾች ፡
የተራ ፡ ወታደር ፡ ብዙም ፡ ባላባቶች ።
አምስት ፡ ሺህ ፡ ሆነን ፡ ወደ ፡ ቈላው ፡ ስንወርድ ፡
የሻለቃችንም ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድይራድ ።
ድል ፡ በማድረጋቸው ፡ ሆነው ፡ እርግጠኛ ፡
ከነነፍሱ ፡ ያዙት ፡ ያንን ፡ ዐመፀኛ ።
እያሉ ፡ በሰፈር ፡ ለሁሉም ሲመክሩ
በጣም ፡ እየዛቱ ፡ በጣም ሲፎክሩ ።
መለከት ፡ ሲነፋ ፡ ሲመታ ፡ ነጋሪት ፡
እርሱ ፡ ወደኛ ፡ መጣ ፡ እኛ ፡ ስንሄድበት ።
የተከተለው ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ በማነሡ
ዐውቆ ፡ ሊማረክ ፡ ነው ፡ ይፈራል ለነፍሱ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

እያሉ ፡ ይጀዝማች ፡ በጣም ፡ ተደሰተው ፡
እነርሱም ፡ ወደኛ ፡ መጥተው ፡ ተጠግተው ፡
ተማረኩ ፡ ብለን ፡ ብንልክበት ፡ ሰው ፡
በነገሩ ፡ ስቆ ፡ አፌዞ ፡ መለሰው ።
ወዲያው ፡ ግጥሚያ ፡ ሆኖ ፡ ገና ፡ ስንሟከር ፡
ወንድይራድ ፡ ተያዘ ፡ ጥቂት ፡ ሳይከራከር ፡
በፈረስ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲመካ ፡ ሲወጠር ።
ካሣ ፡ ተንደርድሮ ፡ በጦር ፡ ቢሰተው ፡
ጐራዴውን ፡ መዞ ፡ ተማረክ ፡ ቢለው ፡
ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ቶሎ ፡ እጁን ፡ ሰጠው ።

ራስ ፡ ዐሊ ።

ተጠንቀቅ ፡ እያልኩት ፡ ሰመከረው ፡ ወንድይራድ ፡
በራሱ ፡ ሲመካ ፡ ደርሶ ፡ ሲመስል ፡ ወንድ ።

እቴጌ ፡ (በምሬት) ።

ሆኖም ፡ ወንድይራድም ፡ ቢሸነፍ ፡ ቢዋረድ ፡
ካሣ ፡ ሳይበረታ ፡ እኛ ፡ እንዘመትበት ፡
ዐዋጅ ፡ ይመታና ፡ ሠራዊት ፡ ይከተት ።
አሁን ፡ ባገኘው ፡ ድል ፡ ኀይል ፡ ሳይሰማው ፡
ቶሎ ፡ እንሂድና ፡ እኛው ፡ እንግጠመው ።

መነቲሴው ።

ቅድሙንም ፡ ቢሆን ፡ ተናግሬ ፡ ነበር ፡
ካሣ ፡ ንግርት ፡ አለው ፡ በዋዛም ፡ አይበገር ።
በያድባራቱና ፡ በየባላገሩ ፡
ወሬው ፡ ስለ ፡ ጸና ፡ ታውቆለት ፡ ንግሩ ፡
አይጠረጠርም ፡ ተሰፋ ፡ አለ ፡ በልቡ ፡
ከቶ ፡ አይመለስም ፡ ሳይደርስ ፡ ከግቡ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

ይልቅ ፡ እንስማማ ፡ ጊዜ ፡ ከሰጠው ፡
በከንቱ ፡ መጋፋት ፡ ከቶ ፡ ጥቅም ፡ የለው ።

እቴጌ ።

በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ የርስዎ ፡ ንግግር ፡
ሽፍታ ፡ ይንገሥ ፡ የሚል ፡ ከየት ፡ አለ ፡ ንግር ።
እንዲህ ፡ ያለውንም ፡ ከንቱውን ፡ ውዳሴ ፡
እያጋነናችሁ ፡ ደብተራ ፡ መነኰሴ ፡ (*)
እብሪት ፡ ላጠገበው ፡ ላመፀኛ ፡ ሽፍታ ፡
ባነጋገራችሁ ፡ ሆናችሁ ፡ መከታ ።
ጽሕፈት ፡ ሕልም ፡ ንግር ፡ አለኮ ፡ እያላችሁ ፡
ዐመፀኛን ፡ ሁሉ ፡ ካበረታታችሁ ።
ጥጋብ ፡ የሚገፋው ፡ እብሪትም ፡ የያዘው ፡
ንግር ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ሊነግሥ ፡ ማለት ፡ ነው ።

መኳንንት ።

ትዕቢተኛ ፡ ሁሉ ፡ በንግር ፡ ቢነግሥ ፡
አይቻልም ፡ ከቶ ፡ መሆን ፡ እንደ ፡ ካሣ ።
ቅድሙን ፡ እናንተ ፡ በጣም ፡ ባታስቆጡት ፡
መች ፡ ይሸፍት ፡ ነበር ፡ ይልስ ፡ እኔ ፡ ልሙት ። ?
ልቡን ፡ የታመነ ፡ ኰራት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡
ምሕረት ፡ አያደርግም ፡ ንቆ ፡ ላኮሰሰው ።
ስለዚህም ፡ ካሣ ፡ በውነት ፡ አመረረ ፡
መመለሻው ፡ ጠፋ ፡ ነገሩ ፡ ከረረ ።
እኔ ፡ ልንገርዎ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡
ካሳ ፡ ማሸነፉ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይቀር ።

* በዚያን ፡ ዘመን ፡ ይልቁንም ፡ በጐንደር ፡ ቀሳውስትና ፡ መነኮሳት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ነበሩና ፡ በንግርትና ፡ በትንቢት ፡ ብዙ ፡ ፖለቲካ ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ በታሪክ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ሦስተኛ

ሕዝቡም ፡ ይኸንኑ ፡ በጣም ፡ ተረድቶታል ፡
ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ባሳብ ፡ ደግፎታል ።

እቴጌ ፡ (በቈራጥነት) ።

እንዲህ ፡ የምትሉ ፡ ፍርሃት ፡ ገብቷችሁ ፡
ያሸነፈ ፡ እንደሆነ ፡ የት ፡ ልግባ ፡ ብላችሁ ።
በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ እንደዚህ ፡ መዋለል ፡
ቍርጠኛው ፡ ሲመጣ ፡ ፈርቶ ፡ መወላወል ።
አያስመሰግንም ፡ ከቶ ፡ አይደለም ፡ ዘዴ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ አልፈራም ፡ ቈርጧል ፡ አንዴ ፡ ሆዴ ።
መስፍኖች ፡ እያሉ ፡ አይነግሥም ፡ ወንበዴ ፡
ታማኝ ፡ አሽከሮቼን ፡ ይዤ ፡ እኔ ፡ እዘምታለሁ ፡
ለክብሬ ፡ ሳልጋዩ ፡ እኔ ፡ እጋደላለሁ ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ (በንዴት ፡ እነጋገር) ።

ንግርትም ፡ ቢኖረው ፡ ሕልምም ፡ ቢታይለት ፡
ኢትዮጵያ ፡ ለርሱ ፡ ከቶ ፡ አትገዛለት ።
ለጊዜው ፡ ቢቀናው ፡ ቢመስል ፡ አሸናፊ ፡
ማን ፡ ይገዛለታል ፡ ለዚህ ፡ ለተጋፊ ።?
ከጐንደር ፡ ከጐጃም ፡ ከትግሬ ፡ ካማራ ፡
ባላባት ፡ መሳፍንት ፡ በቶሎ ፡ ይጠራ ።
ይህን ፡ አምባገነን ፡ ወንበዴና ፡ ሽፍታ ፡
ሁላችን ፡ ተባብረን ፡ ባንድነት ፡ እንምታ ። ! !

መጋረጃ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

የእቴጌይቱ ፡ መማረክ ።

በጦር ፡ ሰፈር ፡ ላይ ፡ እቴጌ ፡ ተማርከው ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ ዘንድ ፡ ይቀርባሉ ።
ካሣ ፡ (በማፌዝ ፡ አኳኋን) ።

የጠሉት ፡ ይወርሳል ፡ የሚሉት ፡ ተረት ፡
በርስዎ ፡ ደረሰ ፡ እቴጌ ፡ ይረዱት ።
እርስዎም ፡ ያውቁታል ፡ መኖሩን ፡ ንግርት ፡
በጣም ፡ አይዘኑ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ።
እንግዲህ ፡ ይበቃል ፡ የሴት ፡ ነገሥታት ፡
ኢትዮጵያ ፡ ወንድ ፡ አላት ፡ የሚጠብቃት ።
በመስፍኖች ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ ሞያ ፡ አልታየ ፡
ሕዝቡ ፡ በመሪ ፡ እጦት ፡ እንዲያው ፡ ተለያየ ።(*)
መንግሥትን ፡ ለመምራት ፡ ያስቸግራል ፡ በጣም ፡
እንደነራስ ፡ ዐሊ ፡ ሰው ፡ መናቅ ፡ አይበቃም ።
ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሁና ፡ ጠረፍዋ ፡ እንዲከበር ፡
ወንድ ፡ ያስፈልጋታል ፡ ልቡ ፡ የማይበገር ።

እቴጌ ፡ (በምሬትና ፡ በቍራት) ።

ይመስልሀ ፡ ይሆናል ፡ አንተ ፡ ያሸነፍኸን ፡
እግዜር ፡ ቢጣላን ፡ ነው ፡ ኀጢአት ፡ አበርክተን ።
ይሁን ፡ ከፈረደ ፡ ከመጣ ፡ ቅጣቱ ፡
እንለምነዋለን ፡ ይደርሳል ፡ ምሕረቱ ።
አንተ ፡ ግን ፡ ልምከርሀ ፡ አትኵራ ፡ በከንቱ ፡
ከቶ ፡ አትገዛም ፡ አንተ ፡ ሳለ ፡ መሳፍንቱ ።

* ሰባ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ መስፍኖች ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ አስቀምጠው ፡ በሥልጣኑ ፡ ይሠሩበት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የነበረው ፡ ሰፊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተከፍሎና ፡ ተዳክሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ።

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

እንደ ፡ ገለባ ፡ እሳት ፡ ላንዳፍታ ፡ ቢያበራ ፡
ስምህና ፡ ዘርህ ፡ ያልፋል ፡ ካንተ ፡ ጋራ ።
መንግሥት ፡ አቋቁሞ ፡ አልጋንም ፡ መውረስ ፡
እንዳይመስልህ ፡ አንተ ፡ መጋለብ ፡ ፈረስ ።
ካያት ፡ ከቅድማያት ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡
የንጉሥ ፡ ደም ፡ የሌለው ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ቢወጣ ።
ቢባልም ፡ ለጊዜው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቀሪ ፡ ነው ፡ ያቆመው ፡ መንግሥት ።
አንተም ፡ ባጋጣሚ ፡ ብትሆን ፡ ንጉሥ ፡
እምቢ ፡ ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ደሙን ፡ ብታፈስ ።
አንተ ፡ ከሞትክ ፡ ወዲያ ፡ ይሆናል ፡ ፈራሽ ፡
ለቀማኸው ፡ አልጋ ፡ የለህም ፡ ወራሽ ።!!

ኪሚ ።

በንግግርዎ ፡ ይሰማል ፡ ንዴት ፡
በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ መሆንዎ ፡ ሴት ።
አነጋገር ፡ ሲያውቁ ፡ መማትም ፡ ሲችሉ ፡
ሰውን ፡ ለማስቈጣት ፡ ተስፋውን ፡ ሲያስቆርጡ ።
ላመጡት ፡ ክርክር ፡ ባልመልስልዎት ፡
ተረትቼ ፡ ዝም ፡ ያልኩ ፡ እንዳይመስልዎት ።
ይህ ፡ የሚናገሩት ፡ ቢሆን ፡ በንዴት ፡
ነገር ፡ መሠረቱ ፡ አያጣም ፡ እውነት ።
እኔም ፡ ድኻ ፡ ብሆን ፡ አለኝ ፡ ዘር ፡ ውልደት ፡
ከነጋሢዎቹ ፡ ከነሩቢል ፡ ቤት ። (*)
ወደ ፡ ፊት ፡ ይገኛል ፡ የትውልዴ ፡ ቍጥሩ ።
ለኔ ፡ ዘር ፡ አይሶጉ ፡ እርስዎ ፡ አይቸገሩ ።

* መሳፍንቱና ፡ ነጋሢዎች ፡ ደጃች ፡ ኪሚ ፡ የነጋሢነት ፡ ተወላጅነታቸውን ፡ እንዳልተቀበሉ ፡ አድርገው ፡ ቢናገሩም ፡ እሷ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በእናታቸው ፡ የንጉሥ ፡ ትውልድ ፡ እንዳላቸው ፡ ተረጋግጧል ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፬ኛ ፡ ትርኢት ።

በመስፍኖች ፡ ዘመን ፡ መንግሥቱ ፡ ተዳክሞ ፡
ጠላት ፡ ከያለበት ፡ ባንድነት ፡ አድሞ ።
ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ ደፍሮ ፡ ሲሞክር ፡
ሂድ ፡ አድናት ፡ ብሎ ፡ ላከኝ ፡ እግዚአብሔር ።
ተባብረን ፡ ባንድነት ፡ እንድንከላከል ፡
ፈቃዴኮ ፡ ነበር ፡ ከናንተ ፡ ባልበደል ።
እኔ ፡ ግን ፡ ልንገርዎ ፡ የልቢን ፡ ምኞት ፡
አላስብም ፡ ከቶ ፡ ለዘሬ ፡ ምቾት ፡
በድሌ ፡ እንደወጣሁ ፡ በድል ፡ ይወጡት ።
እኔ ፡ ካለፍኩ ፡ ወዲያ ፡ ወራሽ ፡ ሥራዬ ፡ ነው ፡
ያቀድኩትን ፡ አሳብ ፡ የሚፈጽመው ፡ ሰው ፡
ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ አርጎ ፡ ጥበብን ፡ አስፋፍቶ ፡
እኔም ፡ ከሞትኩ ፡ ወዲያ ፡ ምኞቴን ፡ አስማምቶ ፡
የሚፈጽምልኝ ፡ ከመጣ ፡ ንጉሥ ፡
አያሳዝነኝም ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ባይነግሥ ።
ላሁን ፡ ይበቃናል ፡ ተናግረናል ፡ ብዙ ፡
እርስዎም ፡ በግዞት ፡ ሄደው ፡ ይተክዙ ።

(እቴጌ ፡ ይሄዳሉ) ።

ካሣ ፡ (ለወታደሮች ፡ በኃይል ፡ አነጋገር) ።

ታጠቁ ፡ ወታደር ፡ እንሂድ ፡ ተነሡ ፡
በትግሬ ፡ በጐጃም ፡ እስኪሰማ ፡ አዲሱ ።
ራስ ፡ ዐሊ ፡ አድሞ ፡ ከትግሬ ፡ ከጐጃም ፡
ሊወጋን ፡ አስቧል ፡ ተቆጭቶ ፡ በጣም ።
መቶ ፡ ካያ ፡ ሺ ፡ ሰው ፡ ሰብስቦ ፡ አሰልፏል ፡
መይሳው ፡ ደፋር ፡ ነው ፡ በርግጥ ፡ ያሸንፋል ።
እንሄዳለን ፡ እኛ ፡ በድላችን ፡ ተፈሪ ፡
ኢትዮጵያ ፡ እስክትሆን ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ተመሪ ።

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

ወንድነቱን ፡ ዐውቆ ፡ ዕድሉን ፡ ሲያምነው ፡
ዐላማውን ፡ አይቶ ፡ ከጸና ፡ ተስፋው ፡
ማመንታት ፡ መሥጋትም ፡ አይገባውም ፡ ሰው ።
ልባችን ፡ ጠንካራ ፡ ምኞታችን ፡ ሰፊ ፡
ካሰብነው ፡ እስክንደርስ ፡ እንሁን ፡ ተጋፊ ።
እኔን ፡ ተመልከቱኝ ፡ ፈረሴንም ፡ እዩት ፡
ከግንባር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከኋላ ፡ አታገኙት ።
ተከተሉኝ ፡ ጐበዝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ መሪያችሁ ፡
ድል ፡ በዕድል ፡ እንዳለች ፡ አሁን ፡ ላሳያችሁ ።
እንግዲህ ፡ ቈራርጠው ፡ በፈንዜ ፡ በካራ ፡
እጅህ ፡ እንዳይሣሣ ፡ ወታደር ፡ አትራራ ፡
ነፍጥና ፡ ጐራዴ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ይሥራ ።

(ወታደሩ ፡ ይፎክራል) ።

መጋረጃ ።

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከነመኳንንቶቻቸው ።

የጐርጐራ ፡ ጦርነት ።

አዝማሪ ፡

ጐርጐራ ፡ ጐርጐራ ፡ ጐርጐራ ፡ ጐርጐራ ፡
ገነት ፡ መሳይ ፡ አገር ፡ ስምሽ ፡ የተጠራ ፡
በላይሽ ፡ ያበራል ፡ የፀሓዩ ፡ ጮራ ፡
ጣና ፡ መስተዋት ፡ ነው ፡ ላንቺ ፡ የሚያበራ ።
ልምላሜ ፡ ሰጥቶሻል ፡ ውበት ፡ የሚያኰራ ፡
ያየሽ ፡ ሁሉ ፡ አድንቆ ፡ ለሰሚ ፡ እንዲያወራ ።
ባንቺ ፡ በመልካሚ ፡ በለምለሚ ፡ ሜዳ ፡
ድል ፡ በዕድል ፡ ተገኝታ ፡ አንዱን ፡ ስትከዳ ።

፳ኛ ፡ ትርኢት ።

ወንድነቱን ፡ ዐውቆ ፡ ቈርጦ ፡ የተነሣ ፡
ራሱን ፡ ተማምኖ ፡ አሸነፈ ፡ ካሣ ።
አንድ ፡ ለሺ ፡ ሆኖ ፡ ሲጋፈጥ ፡ አልፈራ ፡
የቈረጠ ፡ ልቡ ፡ ታየ ፡ በጐርጐራ ።
ባላባት ፡ መሳፍንት ፡ ከስሜን ፡ ከጐጃም ፡
ከትግሬ ፡ ከላስታ ፡ አብሮ ፡ ቢመጣም ፡
ዐውቆታል ፡ ዕድሉን ፡ መይሳው ፡ አልሠጋም ።
ዐላማውን ፡ ዐውቆ ፡ ቈርጦ ፡ በልቡናው ፡
ሰብሮ ፡ ሰብሮ ፡ ጣለው ፡ እያገሳ ፡ አንበሳው ።
የጐርጐራ ፡ ሜዳ ፡ ጠበበው ፡ ፈረሱ ፡
መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይርገጠው ፡ ራሱ ።
ከመቅደላ ፡ እስኪደርስ ፡ አይቈምም ፡ ትንፋሹ ።

ገብርዬ ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከሸሹ ፡ ከሞቱ ፡ እንጐሹ ፡
እንግዲህ ፡ ማናለ ፡ ከኛ ፡ ጠብ ፡ የሚሹ ። ?

ገለሞ ።

ማንም ፡ አያግደን ፡ ድል ፡ ያንተ ፡ ነችና ፡
ስምህን ፡ ንገረን ፡ እናንግሥህ ፡ እኛ ።

ካሣ ።

ስሜን ፡ ስሜን ፡ እነግራችኋለሁ ፡
ደረስጌ ፡ ማርያም ፡ ዘውዴን ፡ እጭናለሁ ።
ውቤ ፡ ከጐርጐራ ፡ በሽሽት ፡ አምልጧል ፡
መቼም ፡ ኀይላችንን ፡ ገምቶት ፡ ዐውቆታል ።
አልገዛም ፡ ካለ ፡ እንዘምትበታለን ፡
ዝም ፡ ብለን ፡ አንቈይ ፡ ባላንጣ ፡ እያለን ።
ውቤን ፡ ድል ፡ ስናደርግ ፡ ሸዋ ፡ እንዘምታለን ፡
ኃይለ ፡ መለኮትን ፡ እናስገብራለን ።

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

፯ኛ ፡ ትርኢት ።

(የደጃች ፡ ውቤ ፡ መግረክ ፡) ።

ደጃዝማች ካሣ ።

ዘውዱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ አቡን ፡ አስመጥቶ ፡
መንገሥ ፡ ያልደፈረ ፡ በዕድሉ ፡ አመንትቶ ።
ሊያገዝን ፡ አይገባውም ፡ ባለዕድል ፡ ቢቀማው ፡
ለደፋር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ዕድል ፡ የተሰጠው ።
ዕድሉን ፡ ተማምኖ ፡ በዕድሉ ፡ የገፋ ፡
አሸናፊ ፡ ሆኖ ፡ ድል ፡ አርጎ ፡ በተስፋ ።
እግዚአብሔር ፡ መርቆ ፡ ዕድል ፡ ለሰጠው ፡
አልገዛም ፡ ብሎ ፡ እሚቃወም ፡ ሰው ።
በከንቱ ፡ ይለፋል ፡ ድሉን ፡ ላያገድ ፡
መገዛቱ ፡ ላይቀር ፡ በውድም ፡ በግድ ።

ደጃች ፡ ውቤ ።

ዕድልን ፡ ተማምነው ፡ ድልንም ፡ ቢያገኙ ፡
ተሰጥቶኛል ፡ ብለው ፡ መግዛትን ፡ ቢመኙ ፡
እግዜር ፡ ካልፈቀደ ፡ አይረጋም ፡ መንግሥቱ ።
ነጋሢ ፡ ባላባት ፡ አይቀር ፡ መነሣቱ ፡
ልከራከር ፡ ብሎ ፡ ለገዛ ፡ መብቱ ።
ዕድሉን ፡ ያወቀ ፡ ራሱን ፡ ያመነ ፡
በራሱ ፡ ተነሥቶ ፡ በኃይል ፡ የገነነ ።
ጊዜ ፡ እሰጠው ፡ ድረስ ፡ ቢሆን ፡ አሸናፊ ፡
ጠላት ፡ ይበዛዋል ፡ በኃይሉ ፡ ተጋፊ ።
እርስዎም ፡ እንደዚህ ፡ ቢመኩ ፡ በዕድልዎ ፡
በፍርሃት ፡ በሥጋት ፡ ተገዛሁ ፡ ቢልዎ ፡
አይቀርም ፡ መክዳቱ ፡ ቀን ፡ ሲጐድልብዎ ።

ኃይልና ፡ ጭካኔ ፡ ብርታትና ፡ ጀብዱ ፡
አይበቁም ፡ ለመግዛት ፡ በዘዴ ፡ ካልሄዱ ።
ደግነት ፡ ጠብቆ ፡ በሚዛን ፡ የሄደ ፡
ተወዶ ፡ ተከብሮ ፡ ብዙ ፡ ተራመደ ።

ካሣ ።

ጥንቱን ፡ ከጧቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀባኝ ፡
ኢትዮጵያን ፡ግዛ ፡ ብሎ ፡ ፈጠረኝ ፡
ድፍረት ፡ ኃይል ፡ ብርታት ፡ ተሰፋንም ፡ ሰጠኝ ።
ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ አይቆሙም ፡ ከፊቴ ፡
እንዴ ፡ ቀብቶኛል ፡ አይቀርም ፡ መግዛቴ ።

መጋረጃ ።

የእጼ ቴዎድሮስ መንገሥ ።

ደጃች ፡ ካሣ ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ ዳግማዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተብለው ፡ ሕዝቡ ፡ እልል፡ ሲል ፡ ዘውድ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ አድርገዋል ፡ ጃንጥላ ፡ አሲዘዋል ፡ እንገብርዬና፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ አርበኞቻቸው ፡ አቡን ፡ ሰላማም ፡ አብረው ፡ ቆመዋል ፡ ነጋሪት ፡ ይመታል ፡ መለከት ፡ እምቢልታም ፡ ይነፋል ።

ፊታውራሪ ፡ ገብርዬ ፡ የእጼ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዐዋጅ ፡ ያነባል ።

ፊታ/ገብርዬ ።

ወታደር ፡ መኳንንት ፡ ካህናት ፡ ባላገር ፡
ነጋዴ ፡ ገበሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገር ።
ትግሬ ፡ ጐጃም ፡ ሸዋ ፡ ወሎና ፡ በጌምድር ፡
ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ነግሧል ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ነው ፡ ገዥህ ፡
አገር ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ፍርድን ፡ የሚሰጥህ ።
ፈላሻና ፡ ቅማንት ፡ ክርስቲያንና ፡ እስላም ፡
ተስማምተህ ፡ ተባብረህ ፡ እንድትኖር ፡ በሰላም ።

ክፍል ፡ ሦስተኛ ።

በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ቀርቷል ፡ መለያየት ፡
ሁሉም ፡ እኩል ፡ ይሁን ፡ በኢትዮጵያዊነት ።
ተለያይቶ ፡ መኖር ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለው ፡
አቅም ፡ እያነሰ ፡ ኋላም ፡ መውደቅ ፡ ነው ።
በዙሪያ ፡ የሚያስተውሉ ፡ ምቀኞችን ፡ ብዙ ፡
ጉልበት ፡ አሳጥተው ፡ ለያይተው ፡ ሊገዙ ።
ተባብረን ፡ እንሥራ ፡ አይግባን ፡ ስንፈት ፡
ኢትዮጵያ ፡ እንድታገኝ ፡ ክብርና ፡ ልማት ፡
ጥበብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሀብት ፡ እንዲሆናት ።
ሰላም ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዲታይ ፡ ለምልሞ ፡
በዘመኑ ፡ መስፍን ፡ መንግሥቱ ፡ ተዳክሞ ።
ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንድነቷ ፡ ጠፍቶ ፡
የቀድሞ ፡ ጠላቷ ፡ በያለበት ፡ መጥቶ ።
ያሰባል ፡ እስካሁን ፡ ገባር ፡ ሊያደርጋት ፡
ሃይማኖት ፡ አስክዶ ፡ ክብር ፡ ሊያሳጣት ።
ምን ፡ እንኳን ፡ አደጋው ፡ የሚያሠጋ ፡ ቢሆን ፡
ማንም ፡ አይደፍረንም ፡ ልብ ፡ ዙሩ ፡ ከሆን ።
ጠላት ፡ አያስብም ፡ ገባር ፡ ሊያደርገን ፡
በርግጥ ፡ እንችላለን ፡ መኖር ፡ ተከብረን ።
አሳቤ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ታዛዥ ፡ ከሆናችሁ ፡
እውነተኛውን ፡ ጥቅም ፡ ካመዛዘናችሁ ።
ላገር ፡ ለትውልዱ ፡ ካሰባችሁ ፡ በእውነት ፡
ምቀኝነት ፡ ተንኰል ፡ ከተዋችሁ ፡ ስንፈት ።
እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አባቶች ፡ ጀግኖች ፡ ከሆናችሁ ፡
ሰላም ፡ ጸጋና ፡ ክብር ፡ ጥበብ ፡ ላስገኛችሁ ።
እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሪ ፡ ያደረገኝ ፡
ይህን ፡ ዘውድ ፡ ሰጥቶ ፡ አደራህን ፡ ያለኝ ፡
ልቢን ፡ መርምሮ ፡ ነው ፡ በጣሙ ፡ ቢያውቀኝ ።

Scanned with CamScanner

፺ኛ ፡ ትርኢት ።

እኔም ፡ አደራዬን ፡ እጠብቃታለሁ ፡
ለኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ ከልብ ፡ እሠራለሁ ፡
ስሟን ፡ አስከብሬ ፡ እሞትላታለሁ ።
ይህን ፡ አደራዬን ፡ ለመፈጸም ፡ ስጥር ፡
ካላገኘሁ ፡ ከሕዝብ ፡ እርዳታና ፡ ምክር ፡
ቅንነት ፡ በማጉደል ፡ እንቅፋት ፡ ቢፈጠር ፡
እኔ ፡ ነኝ ፡ ጠላቱ ፡ በጣም ፡ የምፈልገን ፡
የደም ፡ እንባ ፡ ቢያለቅስ ፡ ጥቂት ፡ የማላዝን ።
አድምጠኝ ፡ አድምጠኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡
ተቈጣሁኸ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አሳቢህም ፡ ከልብ ።
ወደ ፡ ፊት ፡ እያደግህ ፡ እንድትራመድ ፡
እኔ ፡ አሳይሃለሁ ፡ የጀግና ፡ መንገድ ፡
ተከተለኝ ፡ በውድ ፡ ባትወድም ፡ በግድ ፡፡ !

አቡነ ፡ ሰላማ ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ዳግማዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይኸውና ፡ ንጉሥ ፡
ሃይማኖት ፡ ጠብቆ ፡ ጠላት ፡ ይደምስስ ።
ሁላችሁ ፡ አደራ ፡ ባንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ጽኑ ፡
ቴዎድሮስ ፡ ምኞቱ ፡ ነው ፡ ልባዊ ፡ እንድትሆኑ ፡
ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሆና ፡ እንድትሠለጥኑ ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡

(ለወታደሮቻቸው) ።

ጠላትን ፡ ማሸነፍ ፡ መንገሥም ፡ አይበቃም ፡
ትግላችን ፡ ገና ፡ ነው ፡ አለን ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡
ሕግ ፡ ደንብ ፡ አውጥቶ ፡ ሰላምን ፡ ማቋቋም ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ አስቸጋሪ ፡ በጣም ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አራተኛ ።

እስካሁን ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ደከማችሁ ፡
እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እርዱኝ ፡ ከልባችሁ ፡
አገር ፡ እስኪቀና ፡ አይተኛ ፡ አሳባችሁ ።
ጥቂት ፡ አረፍ ፡ ብለን ፡ ደግሞ ፡ እንነሣለን ፡
በወሎ ፡ በሸዋ ፡ እንገሠግሣለን ።
እዚያም ፡ ያለው ፡ ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡
ኀይል ፡ ብርታት ፡ አለው ፡ ጽኑ ፡ ሃይማኖት ።
ሕዝቡም ፡ ጠንካራ ፡ ነው ፡ ጌታውን ፡ ደጋፊ ፡
አይደለም ፡ ደካማ ፡ ዋዛ ፡ ተሸናፊ ።
ጐጃም ፡ ትግሬን ፡ ሸዋን ፡ ካረግነው ፡ ጥገኛ ፡
ሥጋት ፡ የለብንም ፡ የሚያስፈራ ፡ ለኛ ።

ዓለሜ ።

ከቋራ ፡ ዠምረን ፡ አብረን ፡ ስንዋጋ ፡
ጌታችን ፡ ሲነግሡ ፡ እኛ ፡ አገኘን ፡ ዋጋ ።
አሁንም ፡ ካንተው ፡ ጋር ፡ በድል ፡ እንገፋለን ፡
ትእዛዝህን ፡ ልንፈጽም ፡ እድር ፡ መሀላ ፡ አለን ።
እንኳንስ ፡ ድል ፡ በድል ፡ ክብር ፡ ለማይለው ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ላበላው ፡ ይሞትለታል ፡ ሰው ።

መጋረጃ ።

ክፍል ፡ አራተኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

በተጕለት ፡ አታክልት ፡ በሚባለው ፡ቦታ ፡ በንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ቤተ ፡
መንግሥት ፡ ንጉሡ ፡ ታመው ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

የልፍኝ ፡ አሽከር ።

የሸዋ ፡ ባላባት ፡ መኳንንቱ ፡ ሁሉ ፡ መጡ ፡ ከያገሩ ፡
ከግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲመካከሩ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ።

በል ፡ ይግቡ ፡ ጥሪቻው ፡
እንዲከላከሉ ፡ ትእዛዝ ፡ እንስጣቸው ።

(መኳንንቶቹ ፡ በተራ ፡ እየገቡ ፡ እጅ ፡ ይነሣሉ) ።

ኃይለ ፡ መለኮት ።

እንዴት ፡ ሰነበትክ ፡ ሰይፉ ፡ ዳርጌ ፡ እንዳርጋቸው ፡ ሀብተ፡
ማርያም ፡ በዛብህ ፡ ሀብቴ ፡ ገርማሜ ፡ ናደው ፡ አዝብጤ ።

ኃይለ ፡ መለኮት ፡ (ለጸሐፊያቸው) ።

ጸፋላት ፡ ለወርቂቴ ፡ ብትሰማ ፡ ምክር ፡
ቴዎድሮስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነግሦ ፡ በበጌምድር ፡
ታጥቆ ፡ መጥቷል ፡ አሉ ፡ እኛን ፡ ሊያስገብር ።
ሰውዬው ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ኀይል ፡ ያለው ።
እኔ ፡ ከግንባር ፡ ነኝ ፡ አንቺ ፡ ከኋላው ፡
እንበለው ፡ ባንድነት ፡ እንድናደክመው ።
ብትሰሚ ፡ መልካም ፡ ብትቀበይ ፡ ምክሬን ፡
እኔ ፡ ቈርጫለሁ ፡ ላላስነካ ፡ አገሬን ።
ይህንን ፡ ደብዳቤ ፡ ፈረሰኛ ፡ ይዞላት ፡
ለወይዘሮ ፡ ወርቂት ፡ ቶሎ ፡ ያድርስላት ።

ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ።

አሳብ ፡ ሥጋታችን ፡ ከቶ ፡ አይደለም ፡ ስውር ፡
እኛንም ፡ ሊያስገብር ፡ መጣ ፡ ከበጌምድር ።
ቴዎድሮስ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሪ ፡
በጐንደር ፡ በጐጃም ፡ በትግሬ ፡ አሸባሪ ።

(ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ባልጋ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ከሸዋ ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ ይመካከራሉ) ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አራተኛ ።

ዘውዱንም ፡ ቀምቷል ፡ ዐፄ ፡ በጉልበቱ ፡
ይረጋ ፡ ይመስል ፡ በርሱ ፡ እጅ ፡ መንግሥቱ ።
ጊዜና ፡ ሰውዬ ፡ በዕድል ፡ ተገናኝተው ፡
እስጊ ፡ ሆኗል ፡ ለኛም ፡ ገኗል ፡ የቋራው ፡ ሰው ።
እኔ ፡ እንኳ ፡ ብታመም ፡ በእግዜር ፡ እጅ ፡ ብያዝ ፡
በርቱና ፡ ተዋጉ ፡ ተጉለት ፡ ይፋት ፡ መንዝ ።
ዘውዱን ፡ በሽፍትነት ፡ ለቀማ ፡ በግድ ፡
መገዛት ፡ አይገባም ፡ ክብርን ፡ ማስወሰድ ።
የማህለ ፡ ሥላሴ ፡ እንዳይነካ ፡ አሊጋው ፡
ለልጆቹ ፡ አቈዩት ፡ ገና ፡ ገዥ ፡ ነው ።
አሁን ፡ ቢያስፈራችሁ ፡ የመጣው ፡ ከወዲያ ፡
በከንቱ ፡ ያስባል ፡ ሊነግሥ ፡ በኢትዮጵያ ።
ሕዝቡን ፡ በሴፍ ፡ በሳት ፡ የሚያሠቃየው ፡
ከሰሎሞን ፡ ትውልድ ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ሌለው ፡
በከንቱ ፡ ይለፋል ፡ ላይሆን ፡ ያሰበው ።
ያቀዳቸውንም ፡ የሚፈጽሟቸው ፡
የማህለ ፡ ሥላሴ ፡ የኔ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።
አገር ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ፡ ቴዎድሮስ ፡ በማሰቡ ፡
ያስመሰግነዋል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ግቡ ።
አገርም ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሕዝብ ፡ ወዶ ፡ እንዲገዛ ፡
ዘዴ ፡ ትዕግሥት ፡ ያሻል ፡ ከቶ ፡ አይደለም ፡ ዋዛ ።
ስለዚህም ፡ ቴዎድሮስ ፡ በጣም ፡ ተሳስቷል ።
ኃይልና ፡ ጭካኔን ፡ ተማምኖ ፡ ተነሥቷል ።
ዘዴ ፡ ካልጨመረ ፡ ካልለወጠ ፡ እርምጃ ፡
በውጥን ፡ ይቀራል ፡ መቈየቱን ፡ እንጃ ።
ሆኖም ፡ ባካሄዱ ፡ ቢማማት ፡ በጣም ፡
ሐሳቡን ፡ ለማቅለል ፡ አይቻለንም ።
ልጄን ፡ ምኒልክን ፡ አደራ ፡ ልስጣችሁ ፡
እሱ ፡ ነው ፡ ወራሼ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገዥያችሁ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

አንደኛ ፡ ትርኢት ።

አገርን ፡ አስማምቶ ፡ የሚያኖር ፡ በሰላም ፡
የኢትዮጵያንም ፡ ስም ፡ የሚያሳውቅ ፡ ላለም ።
ለማህለ ፡ ሥላሴ ፡ እንዲሆን ፡ ዕድል ፡
አለው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚጠቀልል ።
ሕግ ፡ አውጥቶ ፡ ገዥ ፡ በደንብ ፡ አሳዳሪ ፡
ጥበብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለሕዝቡ፡ አስተማሪ ፡
ብዙ ፡ ሙያ ፡ ያለው ፡ በስሙም ፡ ተፈሪ ።
ስማኝ ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ ይንቃ ፡ መንፈስህ ፡
ዕውቀትና ፡ብርታት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥህ ።
ተስማምቶ ፡ ለመኖር ፡ እንዳይሳንህ ።
ይወጣሉ ፡ ጀግኖች ፡ ከገደሎችህ ።
ከሕዝብ ፡ ከባላባት ፡ ደግሞም ፡ ከመስፍኑ ፡
ከነርሱ ፡ ተወልደው ፡ የሚመሰገኑ ።
የተባለው ፡ ሲሆን ፡ ንግርቱ ፡ ሲደርስ ፡
ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ጥበብ ፡ ሲለግስ ።
ባፍሪካ ፡ በእሲያ ፡ ባውሮፓም ፡ ጭምር ፡
ትወደድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ ትከበር ።

አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ።

ጌታችን ፡ ያሉትን ፡ ሰምተነዋል ፡ ምክሩን ፡
ማነው ፡ የማይረዳ ፡ ሲቻለው ፡ አገሩን ።
ለንጉሡ ፡ የማይሞት ፡ ለክብር ፡ የማይጋደል ፡
ሊኖር ፡ አይገባም ፡ ከወንዶች ፡ መካከል ።

አቶ ፡ ዳርጌ ።

ወንድሜ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡
ለክብር ፡ ላልጋችን ፡ ተዋግተን ፡ እንሙት ።
ቴዎድሮስ ፡ ቢመጡብን ፡ ኀይላቸውን ፡ ታምነው ፡
ሸዋን ፡ አይገዙትም ፡ ራሱ ፡ ገዥ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አራተኛ ።

አቶ ፡ ሀብቴ ።

እግዜር ፡ ካመጣብን ፡ የማንችለውን ፡
እንገብርም ፡ ብለን ፡ ከተከራከርን ።
ምን ፡ ያስፈልገናል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መጋፋት ፡
አቅምን ፡ መገዘኖ ፡ ነው ፡ ጠላትንም ፡ መጉዳት ።

አቶ ፡ አዝብጤ ።

አያ ፡ ሀብቴ ፡ ባለው ፡ እኔም ፡ እስማማለሁ ፡
ጊዜው ፡ ካልፈቀደ ፡ አይባልም ፡ እኔ ፡ አለሁ ።
ጊዜ ፡ የሰጠውን ፡ መልሶ ፡ እስኪክደው ፡
ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ ነው ፡ እንዲበርድ ፡ ቁጣው ።

አቶ ፡ አንዳርጋቸው ።

እኔ ፡ አልቀበልም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዘዴ ።
መከላከል ፡ ሲቻል ፡ በጦር ፡ በጎራዴ ፡
ባገሬ ፡ በሸዋ ፡ አይነግሥም ፡ ወንበዴ ፡
ተዋግቶ ፡ ለመሞት ፡ ቈርጧል ፡ አንዴ ፡ ሆዴ ።

አቶ ፡ ገርማሜ ።

ኀይልና ፡ ጭካኔ ፡ ሰውን ፡ አይገዛውም ፡
ፍቅርና ፡ ምሕረት ፡ ይበልጣል ፡ ከሁሉም ።
ትዕግሥት ፡ ደግነት ፡ ምሕረትም ፡ ያወቀ ፡
እውነትን ፡ ፍርድንም ፡ ከልብ ፡ የጠበቀ ፡
በፍትሑ ፡ እየገዛ ፡ በኋላም ፡ ጸደቀ ።
እግዚአብሔር ፡ መርቆ ፡ የቀባውን ፡ ገፍቶ ፡
እነግሣለሁ ፡ የሚል ፡ ጥጋበኛ ፡ መጥቶ ፡
ተገዙ ፡ ገብሩ ፡ ቢለን ፡ እንሰማውም ፡
ይህንን ፡ ግፈኛ ፡ ሸዋ ፡ አይቀበለውም ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

አቶ ፡ ሰይፉ ።

እንተም ፡ ብትታመም ፡ ጤና ፡ በ.ነሳህ ፡
ልጅ ፡ ወልደሃልና ፡ ማንም ፡ አይወርስህ ።
ከማህለ ፡ ሥላሴ ፡ ያለን ፡ በረከት ፡
ለመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይሆነዋል ፡ ሀብት ።
መንገዘ ፡ ተጉለት ፡ ይፋት ፡ ቡልጋና ፡ ሸንኮራ ፡
መረሐቤቴ ፡ ዶባ ፡ ይፍራታና ፡ ጠራ ፡
ግድም ፡ ወግዳ ፡ ጅሩ ፡ ሞረትና ይራ ፡
ይዋጋል ፡ ጠንክሮ ፡ በነፍጥ ፡ በካራ ።
ላባታችን ፡ አልጋ ፡ ላገራችን ፡ ክብር ፡
ሕይወታችን ፡ ያልፋል ፡ ስንከራከር ።

አቶ ፡ በዛብህ ።

እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ አልደፈረን ፡
እንዴት ፡ ለተጋፊ ፡ እንገብራለን ።
ለምንወደው ፡ ጌታ ፡ ላገራችን ፡ ንጉሥ ፡
ማገዝ ፡ መሐላ ፡ አለን ፡ ደማችን ፡ እንዲፈስ ።
በገደል ፡ በሜካው ፡ እንመክታለን ፡
ለጌታችን ፡ አልጋ ፡ እንጋደላለን ።
ላረግነው ፡ መሐላ ፡ ለሰጠነው ፡ ቃል ፡
እምነትን ፡ ጠብቆ ፡ መሞት ፡ ይገባል ።

አቶ ፡ ናደው ።

ቍርጠኛው ፡ ከመጣ ፡ የማይቀረው ፡ ግድ ፡
መጋፈጥ ፡ አለብን ፡ ክብር ፡ እንዳይወሰድ ።
በየተረተሩ ፡ በገደል ፡ በሜካ ፡
ይገባል ፡ መመከት ፡ አልጋው ፡ እንዳይነካ ።
እንዴት ፡ እኛ ፡ እያለን ፡ ታማኝ ፡ አሽከሮችህ ፡
ደማችን ፡ ሳትፈስ ፡ ይማረካል ፡ ልጅህ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አራተኛ ።

ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ።

የትግሬ ፡ የጐጃም ፡ የወሎ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡
ካሣ ፡ አይነግሥም ፡ ብለው ፡ ያከራከሩ ።
ኅብረት ፡ ሙያና ፡ ልብ ፡ ካላጓደላችሁ ፡
ምን ፡ ቢሆን ፡ አይትልም ፡ ሌላ ፡ ሊገዛችሁ ።
ቀድሞ ፡ አባቶቻችን ፡ ክብርን ፡ ያቈዩልን ፡
ላገር ፡ ለሃይማኖት ፡ ስለተሠዉልን ፡
መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ ልባችሁ ፡ ክፍ ፡ ይበል ።
መክቱ ፡ ባንድነት ፡ ትውልድ ፡ እንዳይበደል ።

መኃረጃ ።

(በመኃረጃ ውስጥ) ፡ አዝማሪ ፡ በገለሌ ።

ገለል ፡ ገለሌ ፡ ገለል ፡ ገለሌ ፡
ቈራጥ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አይወላውሌ ።
ዝም ፡ ትላለህ ፡ ወይ ፡ አገር ፡ ሲወረር ፡
ታጠቅ ፡ ተነሣ ፡ የንጉሥ ፡ ወታደር ።

ደፋሩ ፡ መጥቷል ፡ ቈርጦ ፡ በሞቱ ፡
አምጣ ፡ ወልዳ ፡ የጀግና ፡ እናቱ ።
ደሙ ፡ መራር ፡ ነው ፡ ኮስታራ ፡ አሞቱ ።

የማንን ፡ አገር ፡ ማን ፡ ይወርሳታል ፡
የማንን ፡ እርስት ፡ ማን ፡ ይመራታል ፡
የማንን ፡ እናት ፡ ያዋርዳታል ፡
ወንድ ፡ ልጅ ፡ እሳት ፡ ያስከብራታል ።

ባፋፍ ፡ በገደል ፡ እስቲ ፡ ተጣሩ ፡
ሸዋን ፡ ሊወረው ፡ መጥቷል ፡ ደፋሩ ።
መራር ፡ ቈለኛ ፡ ሞትን ፡ አይፈሬ ፡

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ቈራጥ ፡ ደገኛ ፡ እምቢ ፡ ላገሬ ፡
አይወላውልም ፡ አይስትም ፡ ጦሬ ።
ተው ፡ ሂድ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ግምባር ፡ ለግምባር ፡
እንደ ፡ ከመጣ ፡ ሞት ፡ እንደሁ ፡ አይቀር ፡
አያምርበትም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ማፈር ፡
ጠላት ፡ ሲመጣ ፡ እንገት ፡ ማቀርቀር ።

ካፋፉ ፡ ማዶ ፡ ከሚዳው ፡ ላይ ፡
ፈረስ ፡ ሲያስካካ ፡ አትሰማም ፡ ወይ ።
አይጠረጠርም ፡ እነሱ ፡ ናቸው ፡
ሽንጥህን ፡ ገትር ፡ ቁሙ ፡ በላቸው ፡
ግምባር ፡ ለግምባር ፡ ሂድ ፡ ግጠማቸው ።

(በሰንጎ) ፡ ምት ።

ፈሪ ፡ ሲደበቅ ፡ ከሞት ፡ አምልጦ ፡
ደፋር ፡ ሲመጣ ፡ ዐይኑን ፡ አፍጦ ፡
የሞተው ፡ ጀግና ፡ ልቡን ፡ አጋፍጦ ።
ጐበዝ ፡ ሲመክት ፡ ውርደትን ፡ ጠልቶ ፡
ይነግል ፡ እንጂ ፡ አይቀርም ፡ ሙቶ ።

(በገለሌ) ።

ለጌታው ፡ ታማኝ ፡ የማይወላውል ፡
የቁርጡ ፡ ለታ ፡ ይገኛል ፡ በውል ።
መጡብህ ፡ ሲሉት ፡ በፈረስ ፡ በግር ፡
ተው ፡ በለው ፡ አለ ፡ ፈረስክን ፡ አዞር ።

ጠላት ፡ አይወድም ፡ ዠርባ ፡ ሲያሳዩት ፡
ግምባር ፡ ለግምባር ፡ ዐይን ፡ ዐይኑን ፡ በሉት ።

አካኪ ፡ ዘራፍ ፡ ሞትን ፡ አይፈራ ፡
አመታት ፡ ያውቃል ፡ የጦር ፡ ገበሬ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አራተኛ ።

እምቢ ፡ አሻፈረኝ ፡ ሞት ፡ ይሻለኛል ፡
ያለንጉሤ ፡ ማን ፡ ይገዛኛል ።

በሰንጎ ።

አሽከሩ ፡ ሲወድቅ ፡ ጌታው ፡ ሲጋፈጥ ፡
ይገድላል ፡ እንጂ ፡ መች ፡ ይምራል ፡ ነፍጥ ።
ማን ፡ ይደፍራታል ፡ ያገሬን ፡ ልጅ ፡
ማን ፡ ይረግጣታል ፡ የቤቱን ፡ ደጅ ፡
ደምና ፡ ሬሳ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ።

(በሽለላ) ።

ተው ፡ ተው ፡ አትጨነቅ ፡ አታመንታ ፡ ጐበዝ ፡
አይቈርጥም ፡ ጐራዴ ፡ ገና ፡ ሳይመዘዝ ።
ተው ፡ ተው ፡ ተው ፡ ተው ፡ እያየህ ፡ ተራመድ ፡
እሳት ፡ ሳያቃጥል ፡ መች ፡ ይሆናል ፡ አመድ ።
ገብሩ ፡ ተገዙ ፡ ይለናል ፡ ደፋሩ ፡
አውራው ፡ካልተያዘ ፡ መች ፡ ይቀዳል ፡ ማሩ ።
በለው ፡ በለው ፡ አሳየው ፡ እንግዴህ ፡
ወትሮም ፡ ቈርጦ ፡ መጣል ፡ የቈየ ፡ ልማድህ ።

(ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆይቶ) ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ አልቃሽ ፡ (በዜማ) ።

አገሩን ፡ ለማዳን ፡ ሲያስብ ፡ በውነት ፡
እንደ ፡ ኮራ ፡ ሞተ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ።
ርስት ፡ መች ፡ አነሰው ፡ በመንገዘ ፡ በተጉለት ፡
ሬሳውን ፡ ወስደው ፡ የሚያንገላቱት ።
ዐፄ ፡ አላምንም ፡ ብለው ፡ ሞቷል ፡ ቢሏቸው ፡
ሬሳውን ፡ አውጥተው ፡ አዩት ፡ ባይናቸው ።
እንዴት ፡ ቢፈሩት ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡
ሞቱን ፡ ያላመኑት ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

የሸዋና ፡ የጐንደር ፡ መኳንንቶች ፡ አቤቶ ፡ ምኒልክ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በንጉሥ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አቶ ፡ ዳርጌ ፡ አቶ ፡ ገርማሜ ፡ አቶ ፡ አብቱ፡ አቶ ፡ እንዳርጋቸው ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ከቶ ፡ ለምን ፡ ይሆን ፡ ምኒልክ ፡ ያለው ፡ ?
ምን ፡ ይሆን ፡ ላባቱ ፡ በስሙ ፡ የታየው ።?

አቶ ፡ ዳርጌ ።

የምኒልክን ፡ ስም ፡ መርጠው ፡ የሰጡት ፡
ዘሩን ፡ ሲጠቅሱ ፡ ነው ፡ ከሰሎሞን ፡ ቤት ፡
ከጥንት ፡ የመጣውን ፡ ከሳባ ፡ ንግሥት ፡
ልጁ ፡ ይወርሳል ፡ ሲሉ ፡ ያባቱን መንግሥት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በማፌዝ) ።

ሞያ ፡ ሳያሳዩ ፡ በስም ፡ መመካት ፡
አጭር ፡ አስተያየት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ።
ዐዋቂ ፡ ሲመስለኝ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡
እንዴት ፡ ብሎ ፡ አመነ ፡ በስም ፡ በትንቢት ።
ይሁን ፡ ምን ፡ ቸገረ ፡ በስም ፡ ከደረሰ ፡
ምኒልክ ፡ በስሙ ፡ አልጋ ፡ ከወረሰ ፡
አባቱም ፡ የሰጠው ፡ ስሙ ፡ ይቈይለት ፡
መንግሥቱን ፡ ለመውረስ ፡ ተስፋ ፡ ከሆነለት ።

(ለአቤቶ ፡ ምኒልክ) ።

ለመሆኑ ፡ አባትህ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ሰጥቶሃል ፡ ?
በአንገትህስ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ አስረሃል ።?

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አራተኛ ።

አቤቶ ፡ ምኒልክ ።

አባቴ ፡ ሳይሞቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተጣርተው ፡
ብቻዬን ፡ ከጓዳ ፡ እጄን ፡ ይዘው ፡ ገብተው ፡
ይህን ፡ አሠሩልኝ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ብለው ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ኧረ ፡ እስቲ ፡ እኔ ፡ ልየው ፡ ይገባል ፡ መጠርጠር ፡
ውስጡም ፡ ታላቅ ፡ ምሥጢር ፡ ሳይኖርበት ፡ አይቀርም ።

ካንገቴ ፡ ላይ ፡ በሰንጢ ፡ በጥሰው ፡ ቆዳውን ፡ ቀደው ፡ ጽሕፈቱን ፡ ያወጡና ፡ ያነ ባሉ ።

«አንተ ፡ ነህ ፡ ምኒልክ ፡ የኔ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡
ብር ፡ ወርቅ ፡ መሣሪያ ፡ የሚቈጠር ፡ በሺ ፡
ከትልቁ ፡ ዋሻ ፡ ይገኛል ፡ ብትሸ» ።

(ለመኳንንቶቹ) ።

እያችሁ ፡ እያችሁ ፡ የሸዋ ፡ ብልጠቱ ፡
ክታብ ፡ አስመስሎ ፡ ያሰረው ፡ ባንገቱ ፡
ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ሲደብቅ ፡ አባቱ ።

(ለገብርዬ) ።

ገብርዬ ፡ መሪ ፡ ይዘህ ፡ ከዋሻው ፡ ገብተህ ፡
በቶሎ ፡ እንድትመጣ ፡ ያለውን ፡ አስጭነህ ።

(ለአቤቶ ፡ ምኒልክ) ።

አንተ ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ እኔ ፡ ልውሰድህ ፡
ብልህ ፡ ትመስላለህ ፡ ባስተያየትህ ፡
ብዙ ፡ ታጠናለህ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ከሆንህ ፡
አገሩም ፡ ይጠበቅ ፡ ባንዱ ፡ ባጐትህ ፡
ለወግ ፡ እስክትበቃ ፡ እኔ ፡ እስክሾምህ ።

መጋረጃ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ በጐናቸው ፡ ቆጭ ፡ ብለዋል ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ጐጃም ፡ ትግሬ ፡ ወሎ ፡ ሸዋም ፡ ከነበረ ፡
እንግዲህ ፡ ምናለ ፡ መንግሥቴ ፡ ከበረ ።
አገሩን ፡ በሰላም ፡ የማስተዳደሩን ፡
እንገርምር ፡ እንግዲህ ፡ ደንብ ፡ ማቋቋሙን ።
አገር ፡ እንዲረጋ ፡ ጠረፍ ፡ እንዲከበር ፡
መቅጠር ፡ ያስፈልጋል ፡ አያሌ ፡ ወታደር ።
ሕዝብ ፡ ተጨቁኖ ፡ በገዥ ፡ እንዳይበደል ፡
ገባር ፡ ሥራት ፡ ቀርቶ ፡ ደመወዝ ፡ እንዲቀበል ።
ባሪያም ፡ መሸጥ ፡ ይቅር ፡ በብርቱ ፡ ይከልከል ።
ቀሳውስቱ ፡ በዝቶ ፡ ወታደር ፡ እንዳያንስ ፡
በየደብሩ ፡ ያለው ፡ ካህኑ ፡ ይቀነስ ።
ጋብቻ ፡ እንዲጸና ፡ ይቅር ፡ መፋታት ፡
ክርስቲያን ፡ ይጋባ ፡ በሕግ ፡ ሥርዐት ።
መስፍን ፡ ባላባት ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ እንዳይበዛ ።
አውራጃ ፡ ቀበሊው ፡ በመንግሥት ፡ ይገዛ ።(*)
በእስላም ፡ በክርስቲያን ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡
እንዳይቀንስብን ፡ የሕዝቡን ፡ኅብረት ፡
በተቻለ ፡ ዘዴ ፡ እንፈልግለት ።
ሥልጣኔ ፡ እንዲገኝ ፡ ይስፋፋ ፡ ትምህርት ፡
ሕዝብን ፡ ማስተማር ፡ ነው ፡ ብረትን ፡ መሥራት ።

* ከዚሀ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በዐዋጅ ፡ እጽንተዋቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ ያረጋግጣል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

ለወጣቱም ፡ ሆነ ፡ ለሽማግሌው ፡
ካባት ፡ የወረሰው ፡ ሌላ ፡ ለሌለው ።
አስፈላጊ ፡ ይሆናል ፡ ማሳየት ፡ ብርታት ፡
በልቡ ፡ እንዲጸና ፡ የዘሩ ፡ ኵራት ፡
ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሁና ፡ ስትተባበር ፡
ኀይሏን ፡ አጠንክራ ፡ ራስዋን ፡ ታስከብር ።
እውቀት ፡ ባገር ፡ ሰፍቶ ፡ ሲኖር ፡ በሰላም ፡
እሄዳለሁ ፡ እኔ ፡ ኢየሩሳሌም ።
የጌታን ፡ መቃብር ፡ በክብር ፡ ላቆም ፡
ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ሄዶ ፡ እንዲሳለም ።
ንሴብሖ ፡ እያለ ፡ ለመድኀኔ ፡ ዓለም ።

መጋረጃ ።

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በዙፋናቸው ፡ ተቀምጠዋል ።

ገብርዬ ፡ (ከውጭ ፡ ይገባል) ።

ጌታዬ ፡ ሰማሁኝ ፡ የሚያሳዝን ፡ ወሬ ፡
ሸፍቷል ፡ ይላሉ ፡ ሸዋም ፡ ሆነ ፡ ትግሬ ፡

ዓለሚ ፡ (ከውጭ ፡ ይገባል) ።

ባማራ ፡ ልጅ ፡ ጋረድ ፡ ደግሞም ፡ ብሩ ፡ ኃይሉ ፡
እንዲሁም ፡ በጐጃም ፡ ደጃች ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡
ዐፄን ፡ ለመቃወም ፡ ተነሥተዋል ፡ አሉ ። !

ገልሞ ፡ (ከውጭ ፡ ይገባል) ።

በላስታና ፡ በዋግ ፡ ታቹን ፡ በተከዜ ፡
አገር ፡ አሳብሯል ፡ ያ ፡ ዋግሹም ፡ ጐበዜ ።
እንዲሁም ፡ በተንቤን ፡ ደጃች ፡ በዝብዝ ፡ ካሣ ፡
አልገዛም ፡ ብሎ ፡ ሸፍቶ ፡ ተነሣ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

በትግሬ ፡ በሺሬ ፡ ወልቃይትን ፡ ይዞ ፡
ሸፍቷል ፡ ጐበዜ ፡ የተባለው ፡ ጥርሶ ። !

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በምሬትና ፡ በቁጣ) ።

እኔም ፡ የፈራሁት ፡ ይህንኑ ፡ ነበር ፡
ምቀኛ ፡ በዝቶብኝ ፡ በውጥን ፡ እንዳልቀር ፡ (ብድግ ፡ ይላሉ)
ደንቆሮ ፡ ! ምቀኛ ፡ ! ተንኮለኛ ፡ ! ከንቱ ፡ ! !
እንግዲህ ፡ ምንድነው ፡ ለዚህ ፡ መድኀኒቱ ? ! ።
ተገዙ ፡ ብላቸው ፡ አንገዛም ፡ ካሉ ፡
በሳት ፡ ተለብልበው ፡ በሰይፍ ፡ ይቀጣሉ ።
መጨከን ፡ ነው ፡ በጣም ፡ እምቢ ፡ ለሚለው ፡
ዐውቆ ፡ ለሚያጠፋ ፡ መካርም ፡ የለው ።
በጦር ፡ በጐራዴ ፡ ይመታል ፡ አገሩ ፡
በኛ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ታዘው ፡ እስኪመሩ ።
ኀዘን ፡ ርኀራኄ ፡ እንዳታሳዩዋቸው ፡
መልሶ ፡ ይከዳል ፡ መልቲ ፡ ነው ፡ ልባቸው ።
ትእዛዜን ፡ አፍርሰው ፡ ዐመፅ ፡ ለሚያሳዩ ፡
ጥቂትም ፡ አልሳሳ ፡ እኔ ፡ አልተውም ፡ መዩ ።
አውራጆቹ ፡ ሁሉ ፡ በኔ ፡ ማደማቸው ፡
ገብቶኛል ፡ ነገሩ ፡ ያለው ፡ በልባቸው ።
ባላባት ፡ መሳፍንት ፡ እኛ ፡ አለን ፡ እያሉ ፡
እኔን ፡ ለማስወገድ ፡ ሁሉም ፡ ያስባሉ ።
እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ሕዝቡም ፡ የሚያስበው ፡
በሴፍ ፡ በጐራዴ ፡ በሳት ፡ ነው ፡ የምለው ።
እንድገዛ ፡ መርጦ ፡ እግዜር ፡ ነው ፡ የላከኝ ፡
ግፍ ፡ ሠራህ ፡ እያለ ፡ ማነው ፡ የሚወቅሰኝ ።
የፈቀደው ፡ ቢሆን ፡ እጄ ፡ ከቶ ፡ አይሳሳም ፡
የኔ ፡ ነፍሴ ፡ ቆማ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይገዛም ።
አሳቤን ፡ ሳልፈጽም ፡ ምን ፡ ቢሆን ፡ አልተኛም ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

በኀይል ፡ እንደ ፡ ነገሥኩ ፡ በኀይል ፡ እገዛለሁ ፡
ማንንም ፡ አልፈራም ፡ እንዴ ፡ ነግሻለሁ ።
እግዜር ፡ ምን ፡ አስቆጣው ፡ እንዴ ፡ ከሰጠኝ ፡
እኔው ፡ እገዛለሁ ፡ እንደመሰለኝ ።

(በትካዜ)

የሚያራራኝ ፡ ማነው ፡ ሙታለች ፡ ተዋበች ፡
ልቤን ፡ ያለመካር ፡ አስቀርታዋለች ።
እሷን ፡ ሲወስድብኝ ፡ ሲለየኝ ፡ ከሚስቴ ፡
በጣም ፡ ተሰምቶኛል ፡ ከእግዜር ፡ መጣላቴ ።

(በቁጣ)

እንግዲህ ፡ እንዳሻው ፡ ያፈቀደው ፡ ይሁን ፡
መይሳው ፡ ደፋር ፡ ነው ፡ ያደርጋል ፡ የልቡን ። ! !

(ጐራዴውን ፡ ይመዛል) ።

እምቢ ፡ ያሉትን ፡ ሁሉ ፡ እንዳትምሯቸው ፡
በጦር ፡ በጐራዴ ፡ በሳት ፡ አቃጥሏቸው ። ! !

(ገብርዬ ፡ ገልሞና ፡ ዓለሜ ፡ ሦስቱም ፡ ባንድነት ፡ ጐራዴያቸውን ፡ መዘው)

እዘዝ ፡ ! ዝግጁ ፡ ነን ፡ !
አገር ፡ አንድ ፡ እስኪሆን ፡ እንጋደላለን ። ! !

መጋረጃ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ ቤልና ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ይሄዳሉ ፡ ወታ ደሮቻቸው ፡ ተከትለዋቸዋል ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

(ላንድ ፡ ባላገር) ።

እንች ፡ ባላገር ፡ ወዴት ፡ አለች ፡ ጋረድ ፡?
እናገኛት ፡ ይሆን ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ብንሄድ ። ?

ባላገር ።

ተረተሩን ፡ አልፈው ፡ ከወንዙ ፡ ሲደርሱ ፡
ወንድሙንም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ራሱ ።
ሳያገኙት ፡ አይቀር ፡ ከጥሻው ፡ መካከል ፡
አድፍጦ ፡ ከጫካው ፡ ሊቃማና ፡ ሊገል ።

ቤል ።

ይህ ፡ ዐመፀኛ ፡ ሰው ፡ የቈረጠ ፡ ይመስላል ፡
እያየን ፡ በማስላት ፡ ብንሄድ ፡ ይሻላል ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

አዬ ፡ ጕድ ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ ለርሷ ፡ እንዳትሠጋ ፡
ማነው ፡ የሚሰጣት ፡ ይኸን ፡ ያኽል ፡ ዋጋ ፡
ይመስልሃል ፡ እንዴ ፡ ደፍራ ፡ እኛን ፡ ልትወጋ ?።

ቤል ።

ሆኖም ፡ እንጠንቀቅ ፡ ከጫካው ፡ ስንደርስ ፡
መንገዱ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ አያስኬድም ፡ ፈረስ ።
ዝግ ፡ ብለን ፡ እያየን ፡ አድምጠን ፡ እንሂድ ፡
ለሽፍታ ፡ ይመቻል ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ መንገድ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አም ስተኛ ።

ቤል ፡ ንግግሩን ፡ ሳይጨርስ ፡ በጫካው ፡ ሲያንኮሻኩሹ ፡ ይሰማሉ ። ወ ዲያው ፡ ጋረድ ፡ ፎክሮ ፡ ጦር ፡ ይወረውራል ። አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጐንበስ ፡ ሲሉ ፡ ከኋላ ፡ ያለውን ፡ አሽከር ፡ ይወጋዋል ፤ ቤል ፡ ሽጉጥ ፡ ይተኩስና ፡ ጋረድን ፡ ሲገድለው ፡ የጋረድ ፡ ወንድም ፡ ቤልን ፡ በጦር ፡ ይወጋዋል ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ የጋረድን ፡ ወንድም ፡ ይገድሉታል ፡ ጋረድንና ፡ ወንድሙን ፡ በጐራዴ ፡ ጨርሰው ፡ ሲመለሱ ፡ ቤል ፡ ሙቶ ፡ ያገኙታል ፡ ራሳቸውን ፡ ይዘው ፡ ያዝናሉ ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

እንዴት ፡ ብትወደኝ ፡ ብታስብልኝ ፡
የሳከለኝን ፡ ሞት ፡ ተቀበልክልኝ ።
ከሩቅ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ካገሩ ፡ ተሰዶ ፡
ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ከባሕሩ ፡ ማዶ ።
ሲረዳኝ ፡ ሲመክረኝ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ ወዶ ፡
ሞቴን ፡ ተቀበላት ፡ ከፊቴ ፡ ተጋርዶ ።
ከወንድም ፡ ከራሱ ፡ አብልጦ ፡ ወዶኝ ፡
ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ቤል ፡ ለኔ ፡ ሞተልኝ ።

(ለአሽከሮቻቸው ፡ በቁጣ ፡ ቃል) ።

የጋረድን ፡ ሰዎች ፡ ወገኖቹን ፡ ሁሉ ፡
አንድም ፡ ሳታስቀሩ ፡ ሁሉንም ፡ ግደሉ ።
ሬሳቸውንም ፡ እንዳትቀብሩት ፡
እጅ ፡ እግራቸውንም ፡ በሰፍ ፡ ቈራርጡት ።
ባንድ ፡ ከምራችሁ ፡ ላውሬ ፡ እንድትሰጡት ።
የታማኝ ፡ ወዳጁን ፡ የቤልን ፡ በቀል ፡
በመቶና ፡ በሺ ፡ ብድሩ ፡ ይከፈል ።

መጋረጃ ።

፬ኛ ፡ ትርኢት ፡፡

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በዙፋናቸው ፡ ተቀምጠው ፡ በገና ፡ ይደረድራሉ ፡፡
(በእባ ፡ ግራኝ ፡ ምት) ፡፡

ክፉ ፡ ነው ፡ ይሉኛል ፡ ይሉኛል ፡ ጨካኝ ፡ (*)
ምክሬን ፡ ሳይቀበሉ ፡ ቃሊን ፡ ሳይሰሙኝ ፡፡
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ፡

አገራችን ፡ ሰፊ ፡ የተዋበች ፡ ለምለም ፡
አይመለከታት ፡ አይመኛት ፡ የለም ፡፡

መጠንቀቅ ፡ አለብን ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ መሥራት ፡
ውድ ፡ አገራችንን ፡ ሌላ ፡ እንዳይወስዳት ፡፡
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ፡
አገር ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ፡ ደካማ ፡ እንዳይባል ፡
ሌት ፡ ተቀን ፡ ሲሠራ ፡ ሲጥር ፡ ሲታገል ፡
ተንኮል ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡ ያስተውላል ፡
ምቀኝነት ፡ ክፋት ፡ ይገላበጣል ፡፡
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ፡

ወንድሞቹ ፡ ሁሉ ፡ አውቀው ፡ ካልረዱት ፡
ብቻውን ፡ ሲታገል ፡ በተስፋው ፡ ይሙት ፡፡
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ?

ደግ ፡ ሲመክሯቸው ፡ ክፉ ፡ ያስባሉ ፡
ቀናውንም ፡ ነገር ፡ ያወላግዳሉ ፡
የተንኮልን ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ ያጠናሉ ፡

* አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ራሳቸው ፡ በገና ፡ መደርደር ፡ ይወዱ ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ የእርሳቸውም ፡ ግጥሞች ፡ ብዙዎች ፡ እንዳሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉና ፡ ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ ከሕዝብ ፡ የተገጠሙላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግጥሞች ፡ እንዳሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ነገር ግን ፡ የዚህ ፡ ቴያትር ፡ ደራሲ ፡ ራሱ ፡ ከጻፋቸው ፡ በቀር ፡ የሌሎችን ፡ ጣልቃ ፡ ማግባት ፡ ስላልፈቀደ ፡ በዚህ ፡ ቴያትር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ደራሲው ፡ የገጠማቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡፡

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

እንደዚህ ፡ ለጥፋት ፡ ለምን ፡ ይጥራሉ? ።
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ፡

አወይ ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡
መለያየት ፡ ትተህ ፡ ባንድ ፡ ካልሠራህ ፡
ተንቀህ ፡ ተዋርደህ ፡ በገዛ ፡ አገርህ ፡
ይመጣል ፡ ጨካኙ ፡ ባዕድ ፡ ሊገዛህ ።
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ፡

ከንቱን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አውቀው ፡ ካልለዩት ፡
ምግባርን ፡ ከሙያ ፡ ካላስተያዩት ፡
ምን ፡ ይገኝበታል ፡ ይህ ፡ ከንቱ ፡ ሕይወት? ።
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ፡

ቤቱን ፡ ተሸክሞ ፡ ጣራውን ፡ ይዞት ።
ከሥሩ ፡ የቆሙት ፡ አውቀው ፡ ካልረዱት ፡
አቅም ፡ እያነሰው ፡ ሸክም ፡ በዝቶበት ፡
ይወድቃል ፡ ምሰሶው ፡ ካልደገፉት ።
እኔ ፡ መዩ ፡ ቱርክ ፡ ባይ ፡ የምሸሽ ፡ ነኝ ፡ ወይ? ።

(አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ ከፊታቸው ፡ ቁሞ ፡ ይናገራል) ።

ባሕታዊ ።

መናኝ ፡ መነኩሴ ፡ ነኝ ፡ በበረሃ ፡ ኗሪ ፡
የሰው ፡ ኀይል ፡ አልፈራም ፡ ያላንድ ፡ ፈጣሪ ፡
ላለም ፡ የማልጓጓ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈሪ ።
ዓለም ፡ በቃኝ ፡ ብዬ ፡ ሄጃለሁ ፡ ሸሽቼ ፡
ካባት ፡ ከዘመዴ ፡ ከሰው ፡ ተለይቼ ።
ሱባዔ ፡ ገብቼ ፡ ስኖር ፡ በምናኔ ፡
ዘወትር ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ይታየኛል ፡ ለኔ ።
በምትሠራው ፡ ግፍ ፡ በሕዝቡ ፡ ሥቃይ ፡
በጣም ፡ ተቈጥቷል ፡ እግዜር ፡ ባንተ ፡ ላይ ።

፴ኛ ፡ ትርኢት ።

እሁን ፡ የመጣሁት ፡ ከእግዜር ፡ ተልኬ ፡ ነው ፡
አቤቱታው ፡ በገዟል ፡ ባንተ ፡ የሚሰማው ።
በጣም ፡ አብዝተሃል ፡ ግፍና ፡ ጭካኔ ፡
ልብህ ፡ ዘንግቶታል ፡ መኖሩን ፡ ኵነኔ ።
ከመሬት ፡ አንሥቶ ፡ ክብር ፡ ቢሰጥህ ፡
አይጠረጠርም ፡ እንዲጠይቅህ ፡
ለሕዝቢ ፡ ምን ፡ ሠራህ ? ብሎም ፡ እንዲልህ ።
በግፍ ፡ የፈሰሰው ፡ የንጹሓን ፡ ደም ፡
አቤት ፡ አቤት ፡ ይላል ፡ እየጠራ ፡ ስም ።
በቀድሞ ፡ ዘመናት ፡ ጨካኝ ፡ የተባሉ ፡
ጀንጅስካን ፡ ታሜርላን ፡ አቲላ ፡ ሲባሉ ።
እንዲሁም ፡ በሮሜ ፡ ኔሮን ፡ የተባለው ፡ (*)
ጨካኝ ፡ አረመኔ ፡ ስሙ ፡ የተጠራው ፡
ትዕቢትና ፡ ጥጋብ ፡ ልቡና ፡ ነስቷቸው ፡
እስካሁን ፡ ይነሣል ፡ በክፉ ፡ ስማቸው ።
ስምህ ፡ እንደነሱ ፡ በክፉ ፡ እንዳይጠራ ፡
ልብህን ፡ ምከረው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፍራ ።
እግዚር ፡ ነው ፡ የላከኝ ፡ እያልክ ፡ ስትል ፡
ቱርክን ፡ ለማባረር ፡ ነግሠሃል ፡ ሲባል ፡
የምታስጨንቀው ፡ ወገንህን ፡ ሆኗል ።
ጉዳቷን ፡ አውቆላት ፡ እንድትሆናት ፡ ካሣ ፡
በዋልከው ፡ ውለታ ፡ ስምህ ፡ እንዲነሣ ።
እግዚአብሔር ፡ እስቦ ፡ ለውድ ፡ ኢትዮጵያ ፡
እሟልቶ ፡ ቢሰጥህ ፡ ዕድልና ፡ ሞያ ።
ጭካኔና ፡ ትዕቢት ፡ ሊኖርህ ፡ አይገባም ፡
ሕዝቡንም ፡ ልትነግሠው ፡ ዕረፍትና ፡ ሰላም ።

* ኔሮን ፡ ክርስቲያናትን ፡ የፈጀ ፡ በጭካኔው ፡ ስሙ ፡ የተጠራ ፡ የሮማ ፡ ቄሣር ፡ ነው ። ጀንጂስካን ፡ አቲላ ፡ ታሜርላን ፡ የታርታርና ፡ የሞንጉል ፡ ንጉሦች ፡ ናቸው፥ አውሮፓንና ፡ እስያን ፡ ወረው ፡ ብዙ ፡ ጥፋትና ፡ ጭካኔ ፡ የሠሩ ፡ ናቸው ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

ሰውን ፡ በግፍ ፡ መግደል ፡ ማቃጠል ፡ መንደር ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ እብሪት ፡ ሳትከፈለው ፡ አትቀር ፡
እግዜር ፡ ደግ ፡ ቢሆን ፡ ግፈኛን ፡ አይምር ።
ለምትሠራው ፡ ግፍ ፡ ላለህም ፡ ጭካኔ ፡ (*)
የሚበቃ ፡ አይደለም ፡ ብትገባ ፡ ኰንኔ ።
ዕድልና ፡ ዕውቀት ፡ ብዙ ፡ ሙያ ፡ እያለህ ፡
መወደድ ፡ ስትችል ፡ እንዲያው ፡ ትጠላለህ ።
ለኢትዮጵያ ፡ የሰጣት ፡ የዘለዓለም ፡ ዕድል ፡
በጠላቶቿ ፡ ላይ ፡ የሚያስገኛትም ፡ ድል ።
የዳዊት ፡ በረከት ፡ በሳባ ፡ ተገኝቶ ፡
ተከብሮ ፡ የሚኖር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ጸንቶ ፡
በንጉሦቿ ፡ ጀብዱ ፡ በደግነታቸው ፡
ፍርድና ፡ ርኅራኄ ፡ ስላልተለያቸው ።
ከመላው ፡ አፍሪካ ፡ ከእስያም ፡ ጭምር ፡
እንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያን ብትኖር ።
ደርቡሽ ፡ እያበረ ፡ ሊያጠፋት ፡ ሲያስብ ፡
አንተን ፡ የመረጠህ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ።
ሕዝቤን ፡ ጠብቅልኝ ፡ ብሎ ፡ ቢልክህ ፡
ኀይልና ፡ ጭካኔ ፡ በጣም ፡ አብዝተህ ፡
ከሕዝብ ፡ ተጣላህ ፡ እግዜር ፡ ራቀህ ።
እንደዚህ ፡ እንዳንተ ፡ ከምድር ፡ የተነሡ ፡
በእግዜር ፡ ደጋፊነት ፡ ካሰቡት ፡ ሲደርሱ ፡
የነበሩበትን ፡ በቶሎ ፡ እየረሱ ።
አእምሮን ፡ ትተው ፡ በትዕቢት ፡ ሲመሩ ፡
ከንቱ ፡ መና ፡ ሆነው ፡ ያለዋጋ ፡ ቀሩ ።

* አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በብስጭት ፡ ዘመናቸው ፡ ብዙ ፡ ጭካኔ ፡ እንደሠሩና ፡ ሕዝብ ፡ እንዳለቀሰባቸው ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ይናገራል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፬ኛ ፡ ትርኢት ።

እንግዲህ ፡ ይበቃል ፡ ምክሩ ፡ ቢገባህ ፡
አምላክ ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ ልቡና ፡ ይስጥህ ።

(ይሄዳል) ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በቁጣ ፡ ቃል) ።

ዐይኔ ፡ እያስተዋለ ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይወስደኝ ፡
ጋኔል ፡ እየመጣ ፡ በቀን ፡ የሚያቃግርኝ ።
የተማሬ ፡ ተንኮል ፡ እንዳችም ፡ መተት ፡ ነው ፡
እኔ ፡ አልደነግጥም ፡ ጕዳይም ፡ አልለው ።
ይህን ፡ የምትሠራ ፡ ቂስና ፡ መንኰሲ ፡ (*)
በጣም ፡ ታስባለች ፡ እንድትጠፋ ፡ ነፍሴ ።
መይሳው ፡ አይፈራም ፡ ቢመጣም ፡ ጋኔሉ ፡
ተንኮል ፡ እያበዙ ፡ እናሳብድ ፡ ቢሉ ።
በመርዝ ፡ በድግምት ፡ ሊገድሉኝ ፡ ቢጥሩ ፡
ብልሃትና ፡ ዘዴ ፡ ሁሉን ፡ ቢሞክሩ ፡
ከእግዜርም ፡ ከሰይጣን ፡ ጥበብ ፡ ቢበደሩ ፡
እኔን ፡ ለማሸነፍ ፡ ካለም ፡ ጋር ፡ ቢያብሩ ፡
ምን ፡ ቢሆን ፡ አይችሉ ፡ ሐሳቤን ፡ ሊሰብሩ ።
ይሻላቸው ፡ ነበር ፡ አርፈው ፡ ቢቀመጡ ፡!
ከኔ ፡ ለመጋፋት ፡ አስበው ፡ ባይመጡ ።!(**)
ይሻላቸው ፡ ነበር ፡ ትእዛዜን ፡ ቢሰሙኝ ፡!
ደግነት ፡ እያለኝ ፡ ጨካኝ ፡ ባያደርጉኝ ።
ተማሪም ፡ ባላገር ፡ ብትሆንም ፡ ባላባት ፡
አልገዛም ፡ ካለች ፡ እኔ ፡ ከቶ ፡ አልምራት!! ።
እንዳስመረረችኝ ፡ እሷም ፡ ይመራታል ፡
መይሳው ፡ አይራራም ፡ አሳዶ ፡ ይፈጇታል ፡ !

* በብስጭት ፡ ብዛት ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ የተንኮልና ፡ የጋኔል ፡ ሥራ ፡ ይመ
ስላቸዋል ።
** ጠባቸው ፡ ይልቁንም ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

መቼውንስ ፡ ቢሆን ፡ ማን ፡ ወዶ ፡ ይገዛል ?!
ኀይልና ፡ ጭካኔ ፡ ሥልጣን ፡ ያስከብራል ።
ማዘን ፡ መሳሳትም ፡ የከንቱ ፡ ፈሊጥ ፡ ነው ፡
መጨከን ፡ መጨከን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ! !
ሰጥ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እንዲሽቈጠቈጥ! ! ፡
መግረፍ ፡ ነው ፡ መስቀልም ፡ እጅ ፡ እግሩን ፡ መቈረጥ ፡!
አቤት ፡ አቤት ፡ ብሎ ፡ እስኪንቀጠቀጥ! ! ! ።

መጋረጃ ።

፳፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ካፒቴን ፡ ካሜሮን ፡ መኳንንቶች ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ቱርኮች ፡ ቢያስቸግሩ ፡ ክርስቲያኖችን ፡
እናንተን ፡ አድርጌ ፡ ወዳጆቻችን ።
ንግሥትህን ፡ እምኜ ፡ ብጽፍላቸው ፡
እንዴት ፡ ቢንቁኝ ፡ ነው ፡ ዝም ፡ ማለታቸው ፡
መስሏቸው ፡ ይሆን ፡ እኔ ፡ እምፈራቸው ፡
ትሕትናና ፡ ሰላም ፡ ስላሳየኋቸው ?! ።
እንዴት ፡ ላንድ ፡ ንጉሥ ፡ መልስ ፡ ይከለከላል ፡
ለጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ ይባላል ።
በጣም ፡ ያሳዝናል ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡
ክርስቲያን ፡ ለሆነ ፡ በአሊጋው ፡ ለሚኮራ ።
አንተ ፡ ነህ ፡ ካሜሮን ፡ ይህን ፡ ያረግኸኝ ፡
ቤልና ፡ ፕላውዴን ፡ እንዴት ፡ በረዱኝ ፡(*)
ንግሥት ፡ ቢክቶሪያም ፡ ባላዋረዱኝ! ፡

* ቤልና ፡ ፕላውዴን ፡ የአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወዳጆች ፡ የነበሩ ፡ እንግሊዞች ፡ ናቸው ።
ሁለቱም ፡ እርሳቸውን ፡ ሲረዱ ፡ ቀድሞ ፡ ሞተዋል ።

፳ኛ ፡ ትርኢት ።

ይሁን ፡ ከመሰለህ ፡ መልካም ፡ የሠራህ ፡
እኔም ፡ አለቅህም ፡ ትታሠራለህ ።

(ለገብርዬ) ።

እንድም ፡ ነጭ ፡ ሳይቀር ፡ አቡኑንም ፡ ጭምር ፡
እመቅደላ ፡ ወስደህ ፡ በጥብቅ ፡ እንድታሥር! ።

ካሜሮን ።

በነለም ፡ ሕግጋት ፡ በሠለጠኑት ፡
አይቻልም ፡ ከቶ ፡ ቆንሲልን ፡ ሊያሥሩት ።
ሕግ ፡ አይሰጥዎትም ፡ የሰው ፡ ዜጋ ፡ ማሠር ፡
ይህን ፡ ግፍ ፡ ሳይከፍሉት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይቀር ።!

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

በገዛ ፡ አገሬ ፡ በያዝኩት ፡ መንግሥት ፡
ምንም ፡ ብትቈጣ ፡ ያገርህ ፡ ንግሥት ፡
ከቶ ፡ አይለወጥም ፡ የኔ ፡ ሕግጋት ።

ካሜሮን ።

ኀይለኛ ፡ ነች ፡ በጣም ፡ የኔኮ ፡ ንግሥት ፡
እሷን ፡ የሚጠላ ፡ አለበት ፡ ግዝት ፡
ክፉ ፡ እሚያስብባት ፡ ይጥፋ ፡ በመቅሠፍት ፡
ይላል ፡ ማኅተሙ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ። (*)

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

እርግማኑን ፡ ተወው ፡ ለኔ ፡ አያስፈራኝም ፡
የፈረንጅ ፡ እርግማን ፡ በኔ ፡ አይደርስብኝም ።
አውቃለሁ ፡ እንግሊዝ ፡ ኀይለኛነቱን ፡
ግዛቱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ መሆኑን ፡

* Honi soit qui mal y pense የሚለው ፡ ነው

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ አምስተኛ ።

ባሕር ፡ ውቅያኖስ ፡ አልፎ ፡ መግዛቱን ፤
ሻንቅላና ፡ ዐረብ ፡ ነጩንም ፡ ሕንዱን ፤
መግዛቱን ፡ ዐውቄ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡
ወዳጅ ፡ እንሁን ፡ ብዬ ፡ ጻፍኩኝ ፡ ለንግሥት ።
ኢየሩሳሌምን ፡ ከቱርክ ፡ ለማዳን ፡
እንችላለን ፡ ብዬ ፡ ከተረዳዳን ።
በቅንነት ፡ ነበር ፡ እኔ ፡ የጻፍኩት ፡
የሚገባ ፡ አይደለም ፡ እኔን ፡ ዝም ፡ ማለት ።
ይህ ፡ ታላቅ ፡ ስድብ ፡ ነው ፡ ለሚገባውም ፡ ሰው ።
ለኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ነው ።
ባታውቁት ፡ ይሆናል ፡ የሕይወት ፡ ታሪኬን ፡
ክብሬን ፡ በመጠበቅ ፡ እዚህ ፡ መድረሴን ።
ለክብሬ ፡ ታግዬ ፡ በክብር ፡ እኖራለሁ ፡
ክብር ፡ ሳትለየኝ ፡ በክብር ፡ እሞታለሁ ። ! !

ካሜሮን ።

የእንግሊዝን ፡ ቆንሲል ፡ እርስዎ ፡ ሲያሥሩት ፡
መንግሥቱ ፡ ይሰማዋል ፡ እንዳዋረዱት ።
ስለዚህ ፡ አይተውም ፡ ሳይመልስ ፡ ብድሩን ፡
እንግሊዝ ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ለሚነካ ፡ ክብሩን ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በቍጣ ፡ ቃል) ።

ክብሩን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ የሰው ፡ ክብር ፡ አይነካም ፡!
የፈቀደው ፡ ይሁን ፡ ማንንም ፡ አልፈራም ። ! !

(ለአሽከር) ።

ውሰድልኝ ፡ ከዚህ ፡ ፊቱን ፡ አልየው ፡!
እግዜር ፡ የተጣላው ፡ ክፉ ፡ ደፋር ፡ ነው ። ! !

(ካሜሮን ፡ ተይዞ ፡ ይሄዳል) ።

መጋረጃ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

(አገማሪ ፡ ከመጋረጃ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በዘለሰኛ ፡ ወይም ፡ መዲና ፡ ወይም ፡
በበገና ፡ ምት) ።

መቅደላ ፡ መቅደላ ፡ አንቺ ፡ ከፉ ፡ ጐራ ፡
ሲቱን ፡ ሁሉ ፡ ንቆ ፡ ሲኮራ ፡ ሲኮራ ፡
ወንዱ ፡ አንቺን ፡ ወደደ ፡ ተኛ ፡ ካንቺ ፡ ጋራ ።
ከቋራ ፡ ተነሥቶ ፡ ሲጋልብ ፡ ሲጋልብ ፡
መቅደላ ፡ ላይ ፡ ቆመ ፡ ፈረሱ ፡ ገዝቶ ፡ ልብ ።
ይምጡ ፡ ከየሚዳው ፡ ከጐራው ፡ ከወንዙ ፡
ባይናቸው ፡ እንዲያዩት ፡ ተኝቶ ፡ ጐበዙ ።
ሚዳው ፡ ሸለቆውም ፡ ተራራው ፡ ጫካው ፡
አራዊት ፡ ሠራዊት ፡ ሰማይ ፡ ደመናው ።
ምን ፡ ይሆን ፡ ነገሩ ፡ የተጨነቀው ።
መቅደላ ፡ አፋፉ ፡ ላይ ፡ ወድቋል ፡ አንበሳው ፡
መቆሚያ ፡ ጠፍቶበት ፡ መሬት ፡ ብትከዳው ፡
ትከሻ ፡ ባያገኝ ፡ የሚደገፈው ፡
እጁን ፡ የሚጨብጥ ፡ ጠፍቶ ፡ እሚይዘው ፡
ራሱን ፡ በራሱ ፡ ይዞ ፡ አሳረፈው ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብርዬ ፡ ደጃች ፡ ዓለሚ ፡ ባላምባራስ ፡ ገልሞ ፡
ወታደሮች ፡ በመቅደላ ፡ ምሽግ ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

በግራም ፡ በቀኙም ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡
መድፎች ፡ አስጠምደን ፡
ከወንዙ ፡ ሲደርሱ ፡ እንላቸዋለን ።
ገብርዬ ፡ በሯን ፡ ያዝ ፡ ጠብቅ ፡ በሰላምጌ ፡
አንተ ፡ ደግሞ ፡ ዓለሚ ፡ ተሰለፍ ፡ ከራስጌ ፡
ገልሞ ፡ ተከላከል ፡ ጠላትን ፡ ከግርጌ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

እኔ ፡ ከመቅደላ ፡ ካፋፍ ፡ ስጠባበቅ ፡
በርቱና ፡ ጠብቁ ፡ በጣም ፡ በመጠንቀቅ ።
ጠላታችን ፡ ብርቱ ፡ በኀይሉ ፡ የተመካ ፡
ባሕር ፡ ውቅያኖስ ፡ ተሻግሮ ፡ የመጣ ።
በገንዘብ ፡ አባብሎ ፡ በኀይል ፡ አስፈራርቶ ፡
እዚህ ፡ የደረሰው ፡ በኛ ፡ ሰው ፡ ተመርቶ ።
በዋዛ ፡ አይመለስ ፡ ባላጋራችን ።
የእንግሊዝን ፡ ዝና ፡ ኀይለኛነቱን ፡
እናንተም ፡ እንደኔ ፡ ስምታችሁታል ፡
አረመኔ ፡ እስላሙን ፡ አስገብሮታል ።
ብዙ ፡ ትዕግሥትና ፡ ችሎታም ፡ አለው ፡
አንዴ ፡ ያሰበውን ፡ ሳይፈጽም ፡ አይተው ።
ሆኖም ፡ አንፈራውም ፡ ምንም ፡ ቢበረታ ፡
በወሬ ፡ በዋዛ ፡ እኛም ፡ አንፈታ ።
ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ያላችሁ ፡
መቶ ፡ ሰባ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ገጥማችሁ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ድል ፡ እየነሣችሁ ፡
ድል ፡ በድል ፡ ስትኖሩ ፡ በድል ፡ ያረጃችሁ ።
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይታይ ፡ ጀርባችሁ ፡ ለጠላት ፡
በክብር ፡ ያደጋችሁ ፡ ውርደትን ፡ ሳታውቋት ።
እንኳንስ ፡ እንግሊዝ ፡ ቢጣላን ፡ ዓለምም ፡
ከቶ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ እጃችን ፡ አይያዝም ።
ጠላትም ፡ አይገባ ፡ ሳይፈስ ፡ ደማችን ፡
መሞት ፡ ይገባናል ፡ ሳይነካ ፡ ክብራችን ።
እኔም ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ አለሁ ፡ አብሬያችሁ ፡
ለማንም ፡ አልገብር ፡ እኔ ፡ ንጉሣችሁ ።
ምቀኛ ፡ በዝቶብኝ ፡ ሥራዬንም ፡ ቢያውክ ፡
በኔ ፡ ላይ ፡ ታድሞ ፡ እንግሊዝም ፡ ቢላክ ፡
ልጂም ፡ ያሳደግሁት ፡ ቢሄድም ፡ ምኒልክ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ተጽፎልኝ ፡ እንደሁ ፡ መቼም ፡ አይቀርልኝ ፡
ክብሬን ፡ ሳላስነካ ፡ መሞት ፡ ብቻ ፡ አለብኝ ።
ወደ ፡ ፊት ፡ ልገዛ ፡ የተጻፈ ፡ ካለ ፡
አይጠረጠርም ፡ ተስፋ ፡ በድል ፡ አለ ።
ዋና ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ ልብ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡
ዕድሉን ፡ ማመን ፡ ነው ፡ መኖር ፡ በተስፋው ።
ድል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ለሰጠው ፡
ከቶ ፡ የማይቀር ፡ ነው ፡ እንደ ፡ የጻፈው ።
ስለዚህም ፡ አሁን ፡ እንጋደላለን ፡
በተስፋና ፡ በምነት ፡ እናሸንፋለን ።

ፊ/ገብርዬ ።

ጌታዬ ፡ ያድምጡኝ ፡ ሐሳቤን ፡ ልናገር ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ስንዞር ፡ አገር ፡ ላገር ።
ድል ፡ በድል ፡ አግኝተን ፡ ሁሉን ፡ አሸንፈን ፡
በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተከብረን ፡ ተፈርተን ፡
ለውጭ ፡ አንገብርም ፡ በድል ፡ እንሞታለን ፡
ምቀኞች ፡ ተማክረው ፡ ጠላት ፡ ቢለቁብን ፡
ሁሉም ፡ አድማ ፡ መትተው ፡ ቢተባበሩብን ።
በኋላ ፡ ይቆጫሉ ፡ በጣሙን ፡ ያዝናሉ ፡
በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ዘለዓለም ፡ ያፍራሉ ።
እኛ ፡ ግን ፡ ለመሞት ፡ ጥቂትም ፡ አንፈራ ፡
ትውልድ ፡ ሲገምት ፡ ያቀድነውን ፡ ሥራ ፡
አይጠረጠርም ፡ በኛ ፡ እንደሚከራ ።

ይ/ዓለሚ ።

እስካሁን ፡ የረዳን ፡ እግዜር ፡ ያውቅልናል ፡
ውርደት ፡ ከመቀበል ፡ መሞት ፡ ይሻለናል ።

ቀጌ

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

ባላባት ፡ መሳፍንት ፡ ነጋሢ ፡ የተባሉ ፡
በትግሬ ፡ በላስታ ፡ በጐጃምም ፡ ያሉ ።
ዘውዳችንን ፡ ቀማን ፡ ብለው ፡ የሚቆጩት ፡
በባዕድ ፡ አዙረው ፡ በቀል ፡ የሚወጡት ።
አሁን ፡ ባይታያቸው ፡ የክፋት ፡ ሥራቸው ፡
ጠላት ፡ አሳልፈው ፡ በኛ ፡ መልቀቃቸው ፡
ታላቅ ፡ ክህደት ፡ ነው ፡ የሚያስወቅሳቸው ።
ተስማምቶ ፡ ለመኖር ፡ እነሱ ፡ ላይችሉ ፡
እርስ ፡ በራሳቸው ፡ አሁን ፡ ይዋጋሉ ።
አንድ ፡ ያደረግነውን ፡ በመለያየት ፡
አገሩ ፡ ሲዳከም ፡ ይመጣልም ፡ ጠላት ፡
ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ በባዕድ ፡ መገዛት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ንግግራችሁን ፡ አዳመጥኩት ፡ በጣም ፡
የንደፊትም ፡ ቢሆን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አያጣም ።
ለመበቀል ፡ ሲሉ ፡ አገርን ፡ መካድ ፡
ከጠላት ፡ ተስማምቶ ፡ ባንድነት ፡ መሄድ ፡
ምንም ፡ ቢበሳጩ ፡ አይሆንም ፡ መንገድ ።

(ክፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ) ።

እንግሊዝም ፡ ይምጣ ፡ ዝናኑን ፡ አስጭኖ ፡
መይሳው ፡ አይሸሽም ፡ ይዋጋል ፡ ጨክኖ ።
አይዟችሁ ፡ ጐበዞች ፡ እንግዲህ ፡ ቁርጥ ፡ ነው ፡
ባንድ ፡ ልብ ፡ ሆነን ፡ ከመጣም ፡ እንበለው ።
የቋራ ፡ ያታክልት ፡ የጐርጐራ ፡ ጀግኖች ፡
በጐጃም ፡ በወሎ ፡ በሸዋ ፡ አሽናፊዎች ፡
በትግሬ ፡ በላስታ ፡ ሁሉን ፡ ድል ፡ አድራጎች ።

Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

ስማችሁ ፡ ተጠርቷል ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡
ለእንግሊዝ ፡ አሳዩት ፡ ያላችሁን ፡ ሙያ ።
መሞት ፡ ያውቃል ፡ በሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡
ለክብሩ ፡ ላገሩ ፡ ላበላው ፡ ጌታው ፡
ጮማ ፡ ለሚያበላው ፡ ጠጅ ፡ ላጠጣው ።
ሺህ ፡ ጊዜ ፡ ሞት ፡ አይቶ ፡ ሞትን ፡ የማይፈራ ፡
በድል ፡ አድራጊነት ፡ ስማችን ፡ ሲጠራ ።
ሽሽትን ፡ ፍርሃትን ፡ አይተናት ፡ አናውቅም ፡
ከቶ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ለውጭ ፡ አንገብርም ፡
በድል ፡ አግኝተናል ፡ ያለድል ፡ አንለቅም ።
በጥበብ ፡ በዘዴ ፡ ፈረንጆች ፡ ቢበልጡን ፡
በመሣሪያ ፡ ብዛት ፡ በኀይል ፡ ቢሜኑን ፡
የጀግንነት ፡ ሙያ ፡ አበሾች ፡ ብዙ ፡ አለን ፡
ላገር ፡ ለክብራችን ፡ መሞት ፡ እናውቃለን ።
ንጉሡን ፡ አገሩን ፡ የሚወድ ፡ ከልብ ፡
ሞትን ፡ የማይፈራ ፡ ወንድነት ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ።
ለክብሩ ፡ እሚሠጋ ፡ የሚሳሳ ፡ በጣም ፡
አይኖርም ፡ ተዋርዶ ፡ ለባዕድ ፡ አይገዛም ።!

መጋረጃ ።

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

(የሽለላና ፡ የመድፍ ፡ የጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እየተንቈራጠጡ ፡ በመነጽር ፡ ያስተውላሉ ፡ ዓለሜ ፡ እየሮጠ ፡ ይገባል) ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ከምሽጉ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ በመነጽር ፡ ሳይሁ ፡
በጫካው ፡ መካከል ፡ ታይቶኛል ፡ ፈረስህ ፡
በጥድፊያ ፡ በግልቢያ ፡ ስትመጣ ፡ ወደዚህ ።

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

መቅደላ ፡ የአሮጌ ፡ ውጊያ ።

፱ኛ ፡ ትርኢት ።

ባኳኋንህና ፡ ባይንህ ፡ የሚታየኝ ፡
በጣም ፡ የደነገጥክ ፡ ያዘንክም ፡ መሰለኝ ።
ተናገር ፡ ዓለሚ ፡ ምንም ፡ አትደብቀኝ ፡
የሆነውን ፡ ነገር ፡ እባክህ ፡ ንገረኝ ።

ደ/ዓለሚ ።

የግርማዊነትዎን ፡ ትእዛዙን ፡ አክብረን ፡
በእርጉ ፡ ሸለቆ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ወርደን ።
ጠላት ፡ ሲጠብቀን ፡ በምሽግ ፡ በሠልፍ ፡
ቁልቁለቱን ፡ ስንወርድ ፡ ተኰሰብን ፡ መድፍ ።
እሳተ ፡ ገሞራ ፡ ጥይት ፡ ዘነበብን ።
እኛም ፡ በነፍጣችን ፡ እየተታኰስን ፡
ተንደርድረን ፡ ወረድን ፡ እየገሠገሥን ።
ጠላት ፡ አስቀድሞ ፡ ምሽጉን ፡ አስክቦ ፡
መድፍና ፡ ጠመንጃ ፡ ግንቡን ፡ አስከብቦ ።
እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ናዳ ፡ ከላይ ፡ ሲንመጣ ፡
መድፉም ፡ እያጓራ ፡ ጥይቱ ፡ ሲንጣጣ ።
ሰዋችን ፡ ተፈክሮ ፡ ቱልቱል ፡ ሲንደረደር ፡
በካብ ፡ ተከልሎ ፡ ሲያዘንብበት ፡ አረር ፡
አልታገድ ፡ ብሎ ፡ የርስዎ ፡ ወታደር ፡
ካቡን ፡ እየጣሰ ፡ ገባ ፡ ከመካከል ።
በሳንጃና ፡ በነፍጥ ፡ ጠላት ፡ ሲከላከል ።
ድብልቅልቁ ፡ ሆኖ ፡ ሞት ፡ በጣም ፡ ረከሳ ፡
በዙሪያችን ፡ ሁሉ ፡ ተረፍርፎ ፡ ሬሳ ።
ጠላት ፡ ተስፋ ፡ ቈርጦ ፡ መድረሻውን ፡ አጥቶ ፡
በብዛት ፡ ተሜኒን ፡ ትነፈስ ፡ ጦር ፡ አምጥቶ ።
ያን ፡ ጊዜም ፡ ልባችን ፡ ተስፋውን ፡ ቈረጠ ፡
ደፋሩም ፡ ገብርዬ ፡ በጣም ፡ ደነገጠ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

ተው ፡ በለው ፡ እያለ ፡ ሰዉን ፡ ሲያበራታ ፡
ጐራዴውን ፡ መዞ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ሲማታ ።
ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ ደም ፡ አቧራ ፡ ለብሶ ፡
ግንባሩን ፡ ቢመታው ፡ በሩቁ ፡ ተዠሶ ።
በርቱ ፡ ይደርሳሉ ፡ አይቀሩም ፡ ጌታዬ ፡
እያለ ፡ ሲናገር ፡ ወደቀ ፡ ገብርዬ ።

እቴ ፡ ቴዎድሮስ ።

ይበቃል ፡ እንግዲህ ፡ ተወኝ ፡ በቃ ፡ ዓለሜ ፡
አሁን ፡ ተረዳሁት ፡ ያየሁትን ፡ በልሜ ።
ገብርዬ ፡ ተሞተ ፡ ምን ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ እኔ ፡?
ገብርዬ ፡ ገብርዬ ፡ የጦር ፡ መኰንኔ ፡
አሽከር ፡ አይደለህም ፡ ጓደኛ ፡ ነህ ፡ ለኔ ።
አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ አንድም ፡ ሳትለየኝ ፡
ምነው ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ እንዲህ ፡ አጋለጥከኝ ።?
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ትእዛዜን ፡ ስታከብር ፡
ዛሬ ፡ ቀድመኸኝ ፡ ሄድህ ፡ በጣም ፡ ብትዳፈር ፡
ስታጅበኝ ፡ ኖረህ ፡ ስትከተለኝ ።
የለም ፡ አይመስለኝም ፡ አንተ ፡ የከዳኸኝ ።
አስበህ ፡ ይሆናል ፡ ልትይዝልኝ ፡ ቦታ ፡
መምጣቴን ፡ አውቀኸው ፡ የማታ ፡ የማታ ።

ደ/ዓለሚ ።

ተስፋ ፡ ቢጠፋ ፡ ነው ፡ የመረጠው ፡ ሞቱን ፡
ጠላትን ፡ እያየ ፡ እንዳይመልስ ፡ ፊቱን ።
እንደ ፡ ኰራ ፡ ሞተ ፡ ሳያስነካ ፡ ክብሩን ።
እኛም ፡ እንከተል ፡ ካሳየን ፡ መንገዱን ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ገብርዬ ፡ ከሞተ ፡ ሰዋችን ፡ ካለቀ ፡
ምንም ፡ ተስፋ ፡ የለን ፡ አለቀ ፡ ደቀቀ ።
በገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ እንጠባበቀው ፡
አንድ ፡ ለሺ.ም ፡ ቢሆን ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ እንለቀው ።

(እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ይገባሉ) ።

እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ።

ጦራችን ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ መበተኑንና ፡
ገብርዬም ፡ መሞቱን ፡ እውነተኛ ፡ ጀግና ።
ወታደር ፡ ነገረኝ ፡ ከሞት ፡ የተረፈ ፡
መላላክ ፡ ይሻላል ፡ እንዴ ፡ ካሸነፈ ።
እስረኞቹን ፡ ይስጡት ፡ እርቁም ፡ ይደርደር ፡
ምንም ፡ ተስፋ ፡ የለን ፡ የሚያግደረድር ።
ደብዳቤ ፡ ይጻፍለት ፡ አሳቡን ፡ ይናገር ፡
ዓለሜ ፡ ይሂድና ፡ ለኛ ፡ ይከራከር ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በማመንታት) ።

ይሁን ፡ አንቺ ፡ እንዳልሺው ፡ ዓለሜ ፡ ይሂድ ፡
መሸነፍን ፡ ማመን ፡ በውድም ፡ በግድ ፡
የማይቀር ፡ ዕዳ ፡ ነው ፡ ለሚከዳው ፡ ገድ ።
ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ይጻፍና ፡
ዓለሜ ፡ ውሰድለት ፡ ከብትም ፡ ጨምርና ፡
መልሱን ፡ ተቀብለህ ፡ ወደዚህ ፡ ቶሎና ።

(ዓለሜ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ይሄዳል) ።

እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ።

ዛሬ ፡ በፋሲካው ፡ በትንሣኤው ፡ ቀን ፡
ክርስቲያን ፡ ሲደሰት ፡ እኛ ፡ ተጨንቀን ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

እንግሊዝ ፡ አይደለም ፡ ዛሬ ፡ ያሸነፈን ፡
ግልጽ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ እግዚር ፡ ነው ፡ የጣለን ።
እኔም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነግሬዎታለሁ ፡
እግዚር ፡ እንደ ፡ ጠላን ፡ ተረድቼዋለሁ ።
ግፍ ፡ እብሪት ፡ ጭካኔ ፡ በጣም ፡ ስላበዙ ፡
ፍርድን ፡ በማጓደል ፡ በግፍ ፡ ስለ ፡ ገዙ ።
ከምድርም ፡ ከሰማይ ፡ በጣሙን ፡ ተጠሉ ፡
አይጨክኑንም ፡ ነበር ፡ ባይበዛ ፡ በደሉ ።
አሁንም ፡ ልብዎን ፡ ወደሱ ፡ ይመልሱት ፡
እርሱ ፡ መሐሪ ፡ ነው ፡ ይቅርታ ፡ ይለምኑት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ከድኅነት ፡ አውጥቶ ፡ ዘውድ ፡ ቢሰጠኝ ፡
አልገዛም ፡ ላሉት ፡ በጣም ፡ ጨከንኩኝ ።
ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ሊኖር ፡ ባንድነት ፡
ቍጥሩም ፡ እንዲበዛ ፡ የክርስቲያናት ፡
ኢትዮጵያን ፡ ደርቡሽ ፡ እንዳያጠፋት ፡
ኢየሩሳሌምን ፡ ነጻ ፡ ለማውጣት ፡
ይህ ፡ ነበር ፡ ጥረቴ ፡ የልቤ ፡ ምኞት ።
አሳቤ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ለተቃወሙኝ ፡
ጥቂትም ፡ አልሳሳሁ ፡ በጣም ፡ ጨከንኩኝ ።
አንቺ ፡ እንደምትይው ፡ የሚረዳኝ ፡ ቢሆን ፡
ባልቸረገኝ ፡ ነበር ፡ ለሱ ፡ ታዛዥ ፡ መሆን ።
ግን ፡ ልቤም ፡ አያምን ፡ ይረዳኛል ፡ ብሎ ፡
ሥቃይ ፡ ሳያበዛ ፡ በገደለኝ ፡ ቶሎ ።!

እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ።

የልብዎን ፡ ምኞት ፡ ተረድቼዋለሁ ፡
ብርታት ፡ በቅንነት ፡ እንዳለው ፡ አውቃለሁ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፱ኛ ፡ ትርኢት ።

ምኞትም ፡ ያማረ ፡ ልብም ፡ ቢሆን ፡ ቀና ፡
እግዜር ፡ ካልደገፈው ፡ መቼም ፡ አይቃና ።
በወጠኑት ፡ አሳብ ፡ ስምዎም ፡ ይጠራል ፡
በመጭ ፡ ትውልዶች ፡ ሲከበር ፡ ይኖራል ።
የምድሩ ፡ አያሠጋም ፡ ዋናው ፡ ነው ፡ የላይኛው ፡
እንበርክክና ፡ ማረን ፡ እንበለው ።
እሱ ፡ ቂም ፡ አያውቅም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ መሐሪ ፡ ነው ።

(እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ተንበርክከው ፡ ይጸልያሉ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አጠገባቸው
ቆመው ፡ ይተከዛሉ ።

እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ።

ፈጣሪ ፡ አምላኬ ፡ ሁሉን ፡ የምትችል ፡
ሁል ፡ ጊዜም ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የምታገኝ ፡ ድል ።
ትዕቢት ፡ ልባችንን ፡ ቢያደርገው ፡ ተራራ ፡
ቍጣህን ፡ ላንችለው ፡ በከንቱ ፡ ስንኮራ ፡
እንጨነቃለን ፡ ሲመጣ ፡ መከራ ።
አምላክ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ለሠራነው ፡ ግፍ ፡
እኛን ፡ ብትጠላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ደግፍ ።
እኛን ፡ ስትቈጣ ፡ እሷን ፡ አታጥፋት ፡
ከመጣባት ፡ ጠላት ፡ አንተው ፡ አድናት ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ጠበቅኻት ፡
እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ እንዳትለያት ።
እጅዋን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እየዘረጋች ፡
አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ ማረኝ ፡ ትላለች ።
እርዳታ ፡ አትፈልግም ፡ ከሰዎቹ ፡ ዘንድ ፡
እምነቷ ፡ ባንተ ፡ ነው ፡ አንተን ፡ የምትወድ ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

(ዓለሚ ፡ ከውጭ ፡ ይገባል) ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በችኮላ ፡ እነጋገር) ።

ታድያስ ፡ ምን ፡ መለሰ ፡ እንግሊዝ ፡?

ዓለሚ ።

እሱ ፡ እሚጠይቅ ፡ እጅዎን ፡ እንዲይዝ ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (በቍጣና ፡ በምሬት) ።

እንዴት ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡ ለመያዝ ፡ የኔን ፡ እጅ ፡ ! !
አይማረከም ፡ በለው ፡ መዩ ፡ ያንበሳው ፡ ልጅ ።!
እንዲህ ፡ ያለውንም ፡ ደፍሮ ፡ መጠየቁ ፡
መገመት ፡ ባይችል ፡ ሰው ፡ ባለማወቁ ።
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በድል ፡ ተመርተን ፡
ተከብረን ፡ ተፈርተን ፡ ስንገዛ ፡ ኖረን ፡
እግዜር ፡ ተለይቶን ፡ ዛሬ ፡ ቀን ፡ ቢጎድል ፡
ከባለዕድል ፡ ገጥመን ፡ ቢበልጠንም ፡ በድል ።
አይፈቀድለትም ፡ እንዲማርከን ፡
እንኖርም ፡ ከቶ ፡ ባለም ፡ ተዋርደን ።
ንገረው ፡ ለእንግሊዝ ፡ የልቢን ፡ አሳብ ፡
እኔን ፡ ለመማረክ ፡ ጭራሽ ፡ አያስብ ።
ጥያቄም ፡ ማቅረቡ ፡ ለኔ ፡ ስድብ ፡ ነው ።
በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከመገሠሪያው ፡
ንጉሡ ፡ ሲማረክ ፡ ማንም ፡ አላየው ።
ይህ ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ የክብር ፡ ልማድ ፡
መጠበቅ ፡ አለበት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዘውድ ።
ዓለሚ ፡ ንገረው ፡ በጣም ፡ አስጠናው ፡
አይማረከም ፡ በለው ፡ ሳይሞት ፡ አንበሳው ።! !
ለማንም ፡ አይገብር ፡ ነግ ፡ መይሳው ፡!
ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ቀጥቅጦ ፡ የገዛው ፡

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

፱ኛ ፡ ትርኢት ።

ስንት ፡ ጐበዝ ፡ ጀግና ፡ አባሮ ፡ የያዘው ፡
አይጨበጥም ፡ እጁ ፡ ይፋጃል ፡ በለው ። ! !

(አቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ዓለሜ ፡ ገልሞ ፡ ሌሎች ፡ አርበኞች ፡ ብዙም ፡ እስረኞች ፡
ተሰብስበዋል ፡ የመድፍ ፡ ተኩስ ፡ ይሰማል) ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

እንታረቅ ፡ ብዬ ፡ ብልከው ፡ ዓለሜን ፡
እንግሊዝ ፡ አሰበ ፡ ሊጨብጠው ፡ ክንዴን ።
እኔ ፡ አልማረክም ፡ እጄን ፡ አላስይዝም ፡
አላስነካም ፡ ክብሬን ፡ ጠላት ፡ አይገዛኝም ።
ከምርኮ ፡ ከውርደት ፡ መርጫለሁ ፡ ሞቴን ፡
እናንተም ፡ አደራ ፡ ሚስቴንና ፡ ልጄን ።

(የተኩስ ፡ ድምፅ ፡ ይቀረባል) ።

ለመጮዎች ፡ ትውልድ ፡ አስጠንቅቁ ፡ ልሙት ፡
ገልሞ ፡ አንብብላቸው ፡ ኑዛዜዬን ፡ ይስሙት ።

(ወረቀት ፡ ከኪሳቸው ፡ መዝዘው ፡ ይሰጡታል) ።

(ገልሞ ፡ ያነባል) ።

በጐንደር ፡ በጐጃም ፡ በትግሬ ፡ ያላችሁ ፡
በላስታ ፡ በወሎ ፡ በሸዋም ፡ ያላችሁ ።
ከሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ምጽዋ ፡ ድረስ ።
ከደቡብ ፡ ሻንቅላ ፡ ነጭ ፡ ዓባይ ፡ መለስ ።
የነአብርሃ ፡ አጽብሃ ፡ የነዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡
የነፋሲል ፡ አገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡
ክርስቲያን ፡ እስላሙ ፡ ባንድ ፡ ተሰብሰብ ።
አንድ ፡ እንድትሆን ፡ ነው ፡ ስታገል ፡ የሞትኩት ፡
ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ ይኸንን ፡ ተረዱት ።

Scanned with CamScanner

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ተባበር ፡
ነፃነትክን ፡ ጠብቅ ፡ ለውጭ ፡ አትገብር ፡
ስንፍና ፡ አስገብተህ ፡ እንዳታጣ ፡ ክብር ።
ለሚያልፈው ፡ ለከንቱው ፡ ብዙ ፡ አትስገብገብ ፡
ለትውልድ ፡ ውለታን ፡ ለመተው ፡ አስብ ።
ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ እስላም ፡ ክርስቲያን ፡
ካንድ ፡ እናት ፡ ተወልደን ፡ ወንድማማች ፡ ነን ፡
ምቀኝነት ፡ ቅናት ፡ መናናቅ ፡ ትተን ፡
ተከብረን ፡ ተፈርተን ፡ ምስጉን ፡ እንሁን ።
ላገር ፡ ለትውልዱ ፡ ቁም ፡ ነገርን ፡ ሥሩ ፡
ባንድ ፡ አሳብ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተመሩ ።
አገር ፡ ለሚያኮሩ ፡ ላገር ፡ ለሚሠሩ ፡
ድጋፍ ፡ ሁኑ ፡ እንጂ ፡ እንቅፋት ፡ አትሁኑ ።
መመቀኘት ፡ ማውከም ፡ ጠላትን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
አይቀናም ፡ ከቶ ፡ በገዛ ፡ አገር ፡ ልጅ ፡
ለራስ ፡ ብቻ ፡ ማሰብ ፡ ለማንም ፡ አይበጅ ።
ባለሙያ ፡ ሲገኝ ፡ ለኛው ፡ ያኰራናል ፡
ጥቅሙም ፡ ሆነ ፡ ክብሩ ፡ ለኛው ፡ ይተርፈናል ።
ስማኝ ፡ አደራህን ፡ አድምጠኝ ፡ አገሬ ፡
ጐጃም ፡ ሸዋ ፡ ጐንደር ፡ ወሎም ፡ ሆነ ፡ ትግሬ ።
አንድነትክን ፡ ጠብቅ ፡ ልብህም ፡ ከፍ ፡ ይበል ፡
ባሰድ ፡ እንዳይገባ ፡ ትውልድ ፡ እንዳይበድል ።
መከራ ፡ ፈተና ፡ አለህ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡
በቅን ፡ ለሚሠራ ፡ እንቅፋት ፡ አይጠፋም ፡
ሀብት ፡ ንብረት ፡ ያለው ፡ ምቀኛ ፡ አያጣም ።
ለዚህ ፡ መድኀኒቱ ፡ ልብን ፡ ማጠንከር ፡
ክብርን ፡ ሃይማኖትን ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ።
ታሪክን ፡ ትውልድን ፡ የሚያስብ ፡ ከልቡ ፡
ከመንገድ ፡ አይቀርም ፡ ይደርሳል ፡ ከግቡ ።

፪ኛ ፡ ትርኢት ፡፡

ለመሪዎቻችሁ ፡ አስቸጋሪ ፡ አትሁኑ ፡
በእምነት ፡ በሃይማኖት ፡ ሁኑ ፡ ልበ ፡ ጽኑ ፡፡
ላገር ፡ ለክብራችሁ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ታገሉ ፡
ጊዜን ፡ በመከተል ፡ እንዳትዋልሉ ፡፡
ስንፈት ፡ እንዳይገባን ፡ እንዳይገዛን ፡ ባዕድ ፡
እምነትን ፡ አጽንቶ ፡ መጓዝ ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡
ላገር ፡ ጥቅም ፡ ለክብር ፡ ልቡናን ፡ ማስገደድ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ አስፈላጊው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለመሄድ ፡፡
አገርን ፡ ንጉሥን ፡ ደግሞም ፡ ሃይማኖት ፡
ምንም ፡ ቢበድሉ ፡ አይገባም ፡ መክዳት ፡፡
በጎ ፡ ሲሠሩለት ፡ የማይረዳ ፡ ሕዝብ ፡
ሙያና ፡ ተግባርን ፡ የማያውቅ ፡ ልብ ፡፡
ልፋትን ፡ ድካምን ፡ ዐውቆ ፡ የማይረዳ ፡
በመጨረሻውም ፡ አጋልጦ ፡ እሚከዳ ፡
ለትውልድ ፡ ያተርፋል ፡ የውርደትን ፡ ዕዳ ፡፡
ይህ ፡ የደረሰብኝ ፡ ፈተና ፡ ክህደት ፡
ኋላ ፡ ለሚመጡት ፡ ይሆናል ፡ ትምህርት ፡
ምክሬን ፡ ተቀበሉኝ ፡ አሳቤ ፡ ይግባችሁ ፡፡
ታማዬ ፡ ታማዬ ፡ ይኸው ፡ ሞትኩላችሁ ፡
ጠላት ፡ አይዘኝም ፡ እኔ ፡ ንጉሣችሁ ፡፡

ገልሞ

እንግዲህ ፡ ካለቀ ፡ ተስፋ ፡ ከጠፋብን ፡
እስረኞቹን ፡ ገድለን ፡ መሞት ፡ ብቻ ፡ አለብን ፡፡
በሰይፍ ፡ ቈራርጠን ፡ ገደል ፡ እንጣላቸው ፡
ንጼትን ፡ በቀልን ፡ እንወጣባቸው ፡፡ ! ! !

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡፡

አገር ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ፡ አስበን ፡ ባቀድነው ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡን ፡ አስጨነቅነው ፡

ክፍል ፡ ስድስተኛ ።

ኅይልና ፡ ጭካኔ ፡ ብዙ ፡ አሳየነው ።
እንዴት ፡ ከሞትን ፡ ወዲህ ፡ ለበቀል ፡ እንስጠው ።?
ተወኝ ፡ በቃ ፡ ገልሞ ፡ እግዚር ፡ ተጣልቶናል ፡
ከፉ ፡ ሳንሠራ ፡ ብንሞት ፡ ይሻለናል ።
እስረኞቹን ፡ ሁሉ ፡ በሉ ፡ ልቀቋቸው ፡
ሁሉም ፡ በነፃነት ፡ ይግቡ ፡ ካገራቸው ።

አንድ ፡ እስረኛ ።

ልቀቃቸው ፡ ብለህ ፡ አሁን ፡ የምታዘው ፡
ቢጨንቅህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ወደህን ፡ ነው ።!
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ስትጫወትብን ፡
አሁን ፡ ትቀጣለህ ፡ አገኘህ ፡ ብድርህን ።!!

አዒ ፡ ቴዎድሮስ ።

እንዴት ፡ ብለሽ ፡ አንቺ ፡ እንዲህ ፡ ታስቢያለሽ ፡!
ምሕረት ፡ ባደርግልሽ ፡ የፈራሁ ፡ መሰለሽ ።?
እንግሊዝ ፡ ቢያሸንፍ ፡ ዕድሉ ፡ እምቢ ፡ ቢለኝ ፡
በቀሉን ፡ ለመውጣት ፡ አሁንም ፡ ጊዜ ፡ አለኝ ፡
በል ፡ እጅዋን ፡ ጉትተህ ፡ ገደል ፡ ጨምርልኝ ።!!

(ገልሞ ፡ ጉትቶ ፡ ከገደል ፡ ይሰደዋል) ።

ሽዬ ፡ ዘረፉ ።

ጌታዬ ፡ ይማሩን ፡ እሱን ፡ አያድምጡ ፡
እንዱ ፡ ስላጠፋ ፡ ሁሉንም ፡ አይቅጡ ።
በዚህ ፡ በክፉ ፡ ቀን ፡ ምሕረትን ፡ ሲሰጡ ፡ ......

አጼ ፡ ቴዎድሮስ ። (በችኮላ ፡ አነጋገር)

በሉ ፡ እናንተ ፡ ሂዱ ፡ በገደሉ ፡ ውረዱ ፡
መጡ ፡ ተቃርበዋል ፡ ሳይዟችሁ ፡ ሂዱ ።!!

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፪ኛ ፡ ትርኢት ።

ገልሞ ፡ (እንባውን ፡ እየጠረገ) ።

በቃን ፡ ተለያየን ፡ አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ፈረስህ ፡ ሳይገታ ።
መሬት ፡ ብትከዳህ ፡ ብቻህን ፡ ቀረህ ።?
እኔ ፡ አልለይህም ፡ ጌታዬ ፡ እኮ ፡ ነህ ።
ሥቃይህን ፡ አላይም ፡ እሞታለሁ ፡ እኔ ፡
ከቶ ፡ ሌላን ፡ ገዥ ፡ አያየውም ፡ ዐይኔ ።
ጥይት ፡ አለኝ ፡ ድረስ ፡ ተኩሼ ፡ ተኩሼ ፡
ደግሞም ፡ በጐራዴ ፡ በጦርም ፡ መልሼ ።
እስከትወጣ ፡ ነፍሴ ፡ እኔ ፡ እጋደላለሁ ፡
ጌታዬ ፡ ስትሞት ፡ ወዴት ፡ እቀራለሁ ።

(እየሸለለ ፡ ይወጣል) ።

ስንቱን ፡ ጋራ ፡ ወጥቶ ፡ ስንቱን ፡ ሜዳ ፡ ሲያልፈው ፡
የመቅደላን ፡ ዳገት ፡ ለመውጣት ፡ አቃተው ፡
በቃኝ ፡ ልረፍ ፡ አለ ፡ ዓለም ፡ ቢታክተው ።
በጐጃም ፡ በላስታ ፡ በትግሬ ፡ ተባረን ፡
በወሎ ፡ በሸዋ ፡ ስንሄድ ፡ ኖረን ፡
ታክተን ፡ ዓለሙ ፡ ዛሬ ፡ ዕረፍት ፡ አማረን ።
ወንድ ፡ ልጅ ፡ መውለዱ ፡ ደስ ፡ አላት ፡ እናቱን ፡
ማንም ፡ አልነገራት ፡ መከራውን ፡ ሞቱን ።
ዕድል ፡ ከተቃና ፡ ይገኛል ፡ ታማኝ ፡
በከፋ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ወዳጅ ፡ አይገኝ ።
በጌታው ፡ በንጉሡ ፡ ያኖረው ፡ እምነት ፡
ዕድሉን ፡ ዕጣውን ፡ በርሱ ፡ ጥሎበት ፡
ተለይቶ ፡ አይቀርም ፡ ቀን ፡ የከዳለት ፡
ጮማውን ፡ የበሉት ፡ ጠጁንም ፡ የጠጡት ፡
ቁርጠኛው ፡ ሲመጣ ፡ እንዲህ ፡ ካጋለጡት ፡
ራሱን ፡ ተማምኖ ፡ እንደ ፡ ኮራ ፡ ይሙት ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ክፍል ስድስተኛ ።

ሙያ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ምን ፡ ይረባል ፡ ዕውቀት ።
ዕድል ፡ ያስፈልጋል ፡ ዋጋ ፡ እንዲገኝበት ።
ላገሩ ፡ ሲሠራ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡
ሁሉም ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ ብቻውን ፡ ተውት ፤
በቃኝ ፡ ልረፍ ፡ አለ ፡ አንበሳው ፡ ደከሞት ።

• • • • • • • • • • • • • • • • • • • •

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ።

ካፋፉ ፡ ላይ ፡ ቆሜ ፡ አገሬን ፡ ልየው ፡
በቃ ፡ ተለያየን ፡ ልሰናበተው ። . . . .

(ከፍ ፡ ካለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቁመው ፡ ያስተውላሉ) ።

ያው ፡ በስተቀኝ ፡ ሸዋ ፡ ይፋትና ፡ መንዝ ፡
በሩቁ ፡ ይታያል ፡ ጋራው ፡ መገዘዝ ።
ይኸው ፡ ከታች ፡ ወሎ ፡
ከግርጌ ፡ ተንጣሎ ።
ዋድላና ፡ ደላንታ ፡ በጣም ፡ የታወቁ ፡
ፊት ፡ ለፊትም ፡ ትግሬ ፡ ይታያል ፡ በሩቁ ።
ዋግ ፡ ላስታ ፡ በጌምድር ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡
የጐጃም ፡ አቅጣጫው ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ሲያዩት ። . . . . .

(በትካዜ) ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ አገር ፡ ስንቴ ፡ ረገጥኩት ፡
አንድ ፡ እንዲሆን ፡ ነበር ፡ እኔ ፡ የደከምኩት ።
የታል ፡ የበቀለው ፡ የዘራሁት ፡ ሁሉ ፡?
ምድረ ፡ በዳ ፡ መሰሏል ፡ ሰዎችም ፡ የሌሉ ።
አስቢልሽ ፡ ነበር ፡ በጣሙ ፡ ከልቢ ፡
እንስማማም ፡ አሉ ፡ ልጆችሽ ፡ ካሳቢ ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

፫ኛ ፡ ትርኢት ።

ምኞቴን ፡ ሳልፈጽም ፡ ዕድሌ ፡ እምቢ ፡ ካለ ፡
ይግዛሽ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከኔ ፡ የተሻለ ።
እኔስ ፡ እሞታለሁ ፡ ክብሬን ፡ ሳላስነካ ፡
ዕድላሙን ፡ ይስጥሽ ፡ በኔ ፡ የሚተካ ።
ከክፉ ፡ ያድንሽ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡
ተራራ ፡ ሸለቆሽ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይለምልሙ ።
ዘላለም ፡ ልጆችሽ ፡ ተባብረው ፡ ይኑሩ ፡
ዘላለም ፡ ተከብረው ፡ ዘላለም ፡ ይፈሩ ።
ከምቀኛ ፡ ጠላት ፡ እግዜር ፡ ይጠብቅሽ ፡
ከመለያየትም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያድንሽ ።
ኢትዮጵያ ፡ አገሬ ፡ ነሽ ፡ ምድረ ፡ ገነት ፡
ማንም ፡ አይደፍርሽም ፡ የወንዶች ፡ እናት ።
ደኅና ፡ ሁኚ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገረ ፡ ሰላም ፡
ኑሪ ፡ በነፃነት ፡ እስከ ፡ ዘላለም ።

የመድፍና ፡ የጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ ጩኸትም ፡ እየተቃረበ ፡ ይሰማል ፡ ገልሞ ፡ ሲፎክር ፡ ይሰማል ፡ የገልሞ ፡ ፉከራ) ።

ቋራ ፡ ላይ ፡ ገዳይ ፡ ድንጋይ ፡ ለድንጋይ ፡
ጐርጐራ ፡ ገዳይ ፡ በየሚዳው ፡ ላይ ።
በሸዋ ፡ ገዳይ ፡ ዋሻ ፡ ለዋሻ ፡
የንጉሥ ፡ ወታደር ፡ የጦር ፡ ወጌሻ ።
የታጠቅ ፡ አሽከር ፡ የባለ ፡ ዘውዱ ፡
መግደል ፡ መማረክ ፡ የዕለት ፡ ልማዱ ።

(ድምጡ ፡ እየተዳከመ ፡ የዚያ ፡ ተኩስ ፡ እየበረታ ፡ ሲሄድ ፡ ይሰማል) ።

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ (ሽጉጣቸውን ፡ መዘው) ።

አንተው ፡ ከሰጠኸኝ ፡ አንተው ፡ ከነሳኸኝ ፡
ውርደት ፡ ከመቀበል ፡ ራሴን ፡ ልግደላት ፡
አምላክ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ላደረግሁት ፡ ጥፋት ፡
ፈቃድህ ፡ ይፈጸም ፡ ነፍሴን ፡ ተቀበላት ።

(በሽጉጥ ፡ ራሳቸውን ፡ ይገድላሉ) ።

Scanned with CamScanner

ክፍል ስድስተኛ ።

(የእንግሊዝ ፡ ወታደሮች ፡ ወዲያው ፡ ይደርሳሉ ፡ ጀኔራል ፡ ናፒዬር ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ ሬሳውን ፡ አልብሰው ፡ በዙሪያው ፡ ይቆማሉ ፡ ካሜሮን ፡ መጥቶ ፡ሬሳውን ፡ ያያል) ።

፩ኛ ፡ ትርኢት ።

ጀኔራል ፡ ናፒዬር ፡ (በትካዜ ፡ አነጋገር) ።

ትልቅ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ይህ ፡ የወደቀው ፡
የሚያስደንቅ ፡ ሙያ ፡ ብዙ ፡ ነበረው ።
ጭካኔና ፡ ኵራት ፡ እንደዚህ ፡ ጣለው ።
ያባቶቹን ፡ ታሪክ ፡ ጠብቆ ፡ ሳይረሳ ፡
አይማረኩም ፡ ብሎ ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ።
በገዛ ፡ እጁ ፡ ሞተ ፡ እንዳይነካው ፡ ውርደት ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጀግና ፡ መከበር ፡ አለበት ።
ትዕግሥትን ፡ ትቶ ፡ በኀይል ፡ ሲሠራ ፡
ራሱን ፡ ተማምኖ ፡ በራሱ ፡ ሲኮራ ፡
እንደ ፡ ኰራ ፡ ሞተ ፡ ተከብሮ ፡ ሲፈራ ።

(እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ እያለቀሱ ፡ ይገባሉ ፡ ልጃቸው ፡ ተከትሏቸዋል) ።

እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ (በለቅሶ ፡ ዜማ) ።

እዬ ፡ ጉድ ፡ እዬ ፡ ጉድ ፡ አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡
እምቢተኛን ፡ ሁሉ ፡ ሲቀጣ ፡ ሲመታ ።
የሚመታው ፡ ቢያጣ ፡ ዛሬ ፡ ራሱን ፡ መታ ።
.. .. አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ።
በትግሬ ፡ በጐጃም ፡ በሸዋም ፡ ያላችሁ ፡
አንበሳው ፡ እንዳያዝ ፡ ብዙ ፡ የደከማችሁ ፡
እሱ ፡ ራሱን ፡ ያዘል ፡ አትፍሩ ፡ በቃችሁ ።
.. .. አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ።

Scanned with CamScanner

፮ኛ ትርኢት ።

አያችሁልኝ ፡ ወይ ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ ግፍ ፡
ተጉዘን ፡ ተጉዘን ፡ ስንደርስ ፡ ካፋፍ ፡
እኔ ፡ ሴቷ ፡ ቆሜ ፡ ወንዱ ፡ ደክሞት ፡ ሲያርፍ ።
.. .. አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ።
ብመክርህ ፡ ብመክርህ ፡ አልሰማም ፡ ብለህ ፡
ከምትወደው ፡ ልጅህ ፡ ካለም ፡ ተለየህ ።
.. .. አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ።
ይበላናል ፡ ብሎ ፡ ዓለሙ ፡ ሲሠጋ ፡
አንበሳው ፡ መቅደላ ፡ አላገኘም ፡ ሥጋ ።
በጣም ፡ ሆዳም ፡ ነበር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ራብተኛ ፡
የሚበላው ፡ አጥቶ ፡ እንደራበው ፡ ተኛ ።
.. .. አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ።
አሞራ ፡ አንጃበበ ፡ ልማደኛ ፡ ነው ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሰብሮ ፡ ሲያበላው ፡
ዛሬስ ፡ ተዳከመ ፡ ጉልበት ፡ አነሰው ፡
ሥጋ ፡ አልበላም ፡ ብሎ ፡ ጥይቱን ፡ ጠጣው ።
.. .. አወይ ፡ የኔ ፡ ጌታ ።
ይብላኝ ፡ ይብላኝ ፡ ለኛ ፡ እዚህ ፡ ለቀረነው ፡
አንተማ ፡ ምን ፡ አለ ፡ በጅተህ ፡ ወጣኸው ፡ (በጅህ ፡ተወ
ጣኸው) ።

.. ..

፯ኛ ፡ ትርኢት ።

ጄኔራል ፡ ናፒዬር ።

እንሰለፍና ፡ ሰላምታ ፡ እንስጠው ፡
እጓለ ፡ አንበሳ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

(ጥሩንባ ፡ ይነፋል ፡ ሰላምታ ፡ ይሰጣሉ) ።

ክፍል ስድስተኛ ።

ወገኖቻችንን ፡ ነፃ ፡ ካወጣን ፡
እንሂድ ፡ እንግዲህ ፡ ሕዝቡ ፡ ሳይጣላን ።
ያፄ ፡ ቴዎድሮስን፡ልጅ ፡ በክብር ፡ እናኑረው ፡ (*)
አገራችን ፡ ወስደን ፡ ጥበብ ፡ እናስተምረው ።
ዘውዱንም ፡ አክብረን ፡ እናስቀምጠው ።
አገርና ፡ ክብርን ፡ ወዶ ፡ ለሞተው ፡
ዘውዱን ፡ እኛ ፡ ወስደን ፡ ከቶ ፡ አናስቀረው ።
ምግባርና ፡ ሙያ ፡ እንግሊዝ ፡ ያከብራል ፡
ኋላም ፡ ለሚነግሠው ፡ ዘውዱን ፡ ይመልሳል ።
ዘውዱንም ፡ መልሶ ፡ የሚያመጣው ፡ ንጉሥ ፡ (**)
ምስጋና ፡ ያገኛል ፡ ክብርን ፡ በማስመለስ ።

መጋረጃ ።

ተፈጸመ ።

* ያፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ቈይተው በወጣትነት ፡ ዕድሜያቸው ፡ እዚያው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ በእንግሊዝ ፡ መስፍኖች ፡ መቃብር ፡ በክብር ፡ ተቀብረዋል ።

** በ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ሎንዶን ፡ ሄደው ፡ የአፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘውድ ፡ መልሰው ፡ አምጥተውታል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ስለ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በዘመናቸውና ፡ ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ ከሕዝብ ፡ የተገጠሙላቸው ፡ ብዙዎች ፡ ግጥሞች ፡ እንደሚገኙ ፡ ይልቁንም ፡ በበገና ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። ስለ ዚህ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ለመታሰቢያ ፡ ያኽል ፡ ከቴያትሩ ፡ መጨረሻ ፡ አገባኋቸው ።

(በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የተገጠሙ) ።

አንበሳው ፡ መቅደላ ፡ ተኝቶ ፡ አየሁት ፡
ሰው ፡ እያዩ ፡ መሸሽ ፡ ነውር ፡ ሆኖበት ።
መቅደላ ፡ አፋፉ ፡ ላይ ፡ ጩኸት ፡ በረከተ ፡
የሴቱን ፡ አላውቅም ፡ ወንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሞተ ።
የትግሬንም ፡ ንጉሥ ፡ የሸዋንም ፡ ንጉሥ ፡ ሲንቁ ፡ ሲንቁ ፡
የጐጃምን ፡ ንጉሥ ፡ የላስታንም ፡ ንጉሥ ፡ ሲንቁ ፡ ሲንቁ ፡
ወንድ ፡ ያለራስዎ ፡ ገድለውም ፡ አያውቁ ።
እኔ ፡ ብቻ ፡ ልግዛ ፡ ነውና ፡ ነገሩ ፡
እዚያ ፡ ላይም ፡ ሄደው ፡ እንዳያስቸግሩ ።
ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይዞ ፡ የገዛው ፡ ንጉሥ ፡
እንዲህነ ፡ ስሱ ፡ ነው ፡ ጥይት ፡ የሚጕርስ ፡
ዳማ ፡ ጕራች ፡ ቡሎ ፡ የቴዎድሮስ ፡ ፈረስ ፡
አንድ ፡ ጥርኝ ፡ ሆነ ፡ መቅደላ ፡ ሲደርስ ።
መላው ፡ የጐጃም ፡ ሰው ፡ መላው ፡ የትግሬ ፡ ሰው ፡ ተይዞ ፡
በምጥ ፡
የእንግሊዝ ፡ ሐኪሞች ፡ መጥተው ፡ ቢይዙት ፡
ተገላገለ ፡ አሉ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረት ።
ገዶልን ፡ እንዳይሉ ፡ ሙተው ፡ አገኟቸው ፡
ማረከን ፡ እንዳይሉ ፡ ሰው ፡ የለ ፡ በጃቸው ፡
ምን ፡ አሉ ፡ እንግሊዞች ፡ ሲገቡ ፡ አገራቸው ።
ለወሬ ፡ አይመቹም ፡ ተንኰለኛ ፡ ናቸው ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

አምላክን ፡ መስሎ ፡ ቴዎድሮስ ፡
ንዑና ፡ ሖሩ ፡ ሲል ፡ ዋለ ፡ ኀሙስ ።

(እራሳቸው ፡ የገጠሙዋቸው) ።

ተገፍቶ ፡ ተገፍቶ ፡ ሸፍቶ ፡ ቢወጣ ፡
አሁን ፡ ቅቢ ፡ ሆነ ፡ ላለም ፡ የሚበቃ ።
ወንድሞቹ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተው ፡
ደበደቡት ፡ አሉ ፡ ብቻውን ፡ አግኝተው ።
አንድ ፡ ወንድም ፡ ነበረ ፡ ሲጮኽ ፡ የሚረዳ ፡
እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁ ፡ አገርም ፡ ተጐዳ ።
ፍርሃትን ፡ ለጐንደር ፡ ፍርሃት ፡ ለጐጃም ፡ ፍርሃትን ፡
ለትግሬ ፡ ፍርሃትን ፡ ለወሎ ፡ ፍርሃትን ለሸዋ ፡
እኔ ፡ አላስተምርም ። ሽጉጤን ፡ ጠጥቼ ፡ እለዋለሁ ፡
ዞርትም ።

(በጭካኔያቸው ፡ ምክንያት ፡ የተገጠሙ) ።

አንድ ፡ እግር ፡ በርበሬ ፡ መንቀል ፡ አቅቷችሁ ፡
እየለበለበ ፡ አቃጥሎ ፡ ይፍጃችሁ ።
ሺሕ ፡ ፈረስ ፡ ከኋላው ፡ ሺሕ ፡ ፈረስ ፡ ከፊቱ ፡
ይህን ፡ ሳታዩ ፡ ሞተች ፡ ኮሶ ፡ ሻጭ ፡ እናቱ ።
ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እጅግ ፡ ተዋረዱ ፡
የሸዋን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ነስተውት ፡ ሄዱ ።
ሞጣ ፡ ቀራንዮ ፡ ምነው ፡ አይታረስ ፡
በሬሳ ፡ ላይ ፡ መጣሁ ፡ ከዚያ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ።
አንጠረኛው ፡ ብዙ ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡
ባላልቦ ፡ አደረጉት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሴት ።

Scanned with CamScanner
Scanned with CamScanner

ተፈጸመ

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner